

# ለማገልገል መነሳት



ሩሂ ተቋም





መጽሐፍ 2

# ለማገልገል መነሳት

ሩሂ ተቋም

ተከታታይ መጻሕፍት፡-

ከዚህ በታች ያሉት በሩሂ ተቋም የተዘጋጁ ተከታታዮቹ የመጻሕፍት ርዕሶች ዝርዝር ናቸው። መጻሕፍቱ ወጣቶች እና አዋቂዎች ማኅበረሰባቸውን ለማገልገል የሚያስችላቸውን አቅም ለማዳበር በሚደረግ ስልታዊ ጥረት ውስጥ እንደ ዋና ተከታታይ ትምህርቶች/ኮርሶች ለመጠቀም ዓላማ የተዘጋጁ ናቸው። በተጨማሪም የሩሂ ተቋም የባሃኢ ህጻናት ትምህርት አስተማሪዎችን ለማሰልጠን ከሚጠቅም ከተከታታይዎቹ መጻሕፍት ውስጥ ከሦስተኛው መጽሐፍ ቅርንጫፍ ሆነው የሚወጡ ሌሎች የትምህርት/ኮርስ ስብስቦችን፣ እንዲሁም ከመጽሐፍ 5 የታዳጊ ወጣት ቡድኖች አነቃቂዎችን ለማፍራት ሌላ ስብስብ እያዘጋጀ ነው። እነዚህም ከሥር በዝርዝሩ ውስጥ ተመልክተዋል። በመስኩ ላይ ያለው ልምድ እየዳበረ ሲሄድ ዝርዝሩ ይለወጥ ይሆናል፥ እንዲሁም በዝግጅት ላይ የሚገኙ የሥርዓተ ትምህርት ክፍሎች ቁጥር በስፋት ተደራሽ መሆን የሚችሉበት ደረጃ ላይ ሲደርሱ አዳዲስ ርዕሶች ሊጨመሩ እንደሚችሉ መገንዘብ አለብን።

| | |
|---|---|
| መጽሐፍ 1 | በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ እስብታዎች |
| መጽሐፍ 2 | ለማገልገል መነሳት |
| መጽሐፍ 3 | የሕፃናት ትምህርት ማስተማር፣ 1ኛ ክፍል |
| | የሕፃናት ትምህርት ማስተማር፣ 2ኛ ክፍል (ቅርንጫፍ ኮርስ) |
| | የሕፃናት ትምህርት ማስተማር፣ 3ኛ ክፍል (ቅርንጫፍ ኮርስ) |
| መጽሐፍ 4 | መንትያ ክስተቶች |
| መጽሐፍ 5 | የታዳጊ ወጣቶችን ኃይሎች ማጎልበት |
| | መነሻ ፍላጎት፡- የመጽሐፍ 5 የመጀመሪያ ቅርንጫፍ ኮርስ |
| | እየሰፋ የሚሄድ ምህዳር፡- የመጽሐፍ 5 ሁለተኛ ቅርንጫፍ ኮርስ |
| መጽሐፍ 6 | እምነቱን ማስተማር |
| መጽሐፍ 7 | በአገልግሎት ጎዳና ላይ አብሮ መጓዝ |
| መጽሐፍ 8 | የባሃኦላህ ቃል-ኪዳን |
| መጽሐፍ 9 | ታሪካዊ አተያይን/ምልከታን ማግኘት |
| መጽሐፍ 10 | ሕይወታማ ማኅበረሰቦችን መገንባት |
| መጽሐፍ 11 | ቁሳዊ ሀብቶች |
| መጽሐፍ 12 | (በሂደት ላይ) |
| መጽሐፍ 13 | በኅብረተሰባዊ ተግባር ውስጥ መሳተፍ |
| መጽሐፍ 14 | (በሂደት ላይ) |

*የማባዛት መብት © 1987፣1995፣2020 - ሩሂ ተቋም፣ ኮሎምብያ*
*ኅትመት 1.1.1 PE በኦክተበር 1995 የታተመ*
*ኅትመት 2.1.1 PE በሴብተምበር 2020 የታተመ*
*ISBN 978-958-59880-9-5*

ትርጉም - በአዘጋጁ ፈቃድ ከእንግልዘኛ ወደ አማርኛ በኢትዮጵያ ባሃኢዎች ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባዔ የስልጠና ተቋም የሂደት ዴስክ ተተርጉሞና ታርሞ ለሦስተኛ ግዜ፣ 2.1.1. PE *ጥቅምት*፣ 2021 *ታተመ*::

- አዲስ አበበ፣ ኢትዮጵያ
ፖ. ሣ. ቁ. 102 አዲስ አበበ

Ruhi Institute
Cali, Colombia
Email: instituto@ruhi.org
Web site: www.ruhi.org

# ማውጫ

ጥቂት ሃሳቦች ለአስጠኚው ......................................V

የማስተማር ደስታ ...................................................1

አነቃቂ ጭውውቶች .............................................19

የጥልቀት ትምህርት ጭብጦች ..................................41

# ጥቂት ሃሳቦች ለአስጠኚው

በሩሂ ተቋም ከቀረቡት ዋና ተከታታይ ስልጠናዎች/ኮርሶች ውስጥ ሁለተኛ የሆነው ይህ መጽሐፍ፣ ለትርጉም አዘልና አነቃቂ ንግግር አስተዋፅዖ እንድናደርግ የሚያስችለን ችሎታዎች ላይ ትኩረቱን ያደርጋል። መጽሐፉ የሚያተኩርበት የተለየ የአገልግሎት ተግባር በሦስተኛው ክፍል ውስጥ ተገልጿል። የነውጥ ኃይሎች የጋራ ትሥሥርን እየበጣጠሱ ባሉባት ዓለም ውስጥ፣ ለኅብረተሰብ ሕይወት ማዕከል የሆኑ ጭብጦችን ለመመርመር ወዳጆችንና ጎረቤቶችን በቤታቸው የመጎብኘት ልምድ የታወቀ የባህል ገጽታ ከሆነ፣ እየጨመረ በመጣ ብቸኝነት መንስዔነት ለመጡ አንዳንድ ህመሞች ፈውስ ሊሆን ይችላል። ክፍሉ እንደሚጠቁመው የሚፈጠረው የወዳጅነት ትሥሥር፣ ሕይወታማ እና መስተጋብራቸው ያማረ ማኅበረሰቦችን የመገንባት ሒደት ለማጠናከር ያገለግላል።

በሠፈር ወይም በመንደር ውስጥ የሚኖር ዘላቂ የቤቶች ጉብኝቶች ፕሮግራም አግባብነት ባለው አስተዳደራዊ ተቋማት ወይም ኤጀንሲዎች/ባለድርሻ አካላት የሚታገዙ እራሳቸውን የሰጡ ወዳጆች አስኳል ያካተተ አደረጃጀትን የግድ ይላል። አንድን ቡድን በመጽሐፉ ውስጥ ለማስኬድ፣ ተሳታፊዎች እንዲህ ያለውን ቀጣይ ጥረት ለመቀላቀል እየተዘጋጁ እንደሆኑ አስጠኚው ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል። የጥናታቸው አንድ አካል ተደርገው የተደራጁት ጉብኝቶች የአገልግሎት ሕይወት ዋነኛ አካል በሆኑት በነዚህ ጥረቶች ከዓመት ዓመት ለመሳተፍ ቁርጠኛ እንዲሆኑ መንገድ ሊያሳያቸው ይገባል።

የመንፈሳዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ጭብጦች ለመፈተሽ/ለመመርመር በሚል ግልጽ ዓላማ ቤቶችን የመጎብኘት ልምድ የማኅበረሰብን ባህል በዕርግጥ ያዳብራል። በዚህ ረገድ በተመሳሳይ ወሳኝ የሆኑት በቤትና በሥራ ቦታ፣ በትምህርት ቤትና ገበያ ውስጥ የሚፈጠሩ ብዛት ያላቸው ኢመደበኛ ውይይቶች ናቸው። ስለዚህ በየዕለቱ በሚደረግ ንግግር ውስጥ መንፈሳዊ መርሆዎችን ማካተት፣ ትኩረት የሚሻ ችሎታ ነው። ይህን ማጎልበት የሁለተኛው ክፍል ትኩረት ነው፣ በዚህ መንገድ በሦስተኛው ምዕራፍ ለሚከናወነው ጥናት መሠረት ይጥላል።

ከወዳጆችና ጎረቤቶች ጋር የምናደርጋቸው ንግግሮች አነቃቂ/ከፍ ያለ መሆን ካለባቸው፣ ከእነርሱ ጋር በሚኖረን ግንኙነት ደስታ ማምጣት መቻል አለብን። ይህ በመጀመሪያው ክፍል የሚዳሰሰው ርዕስ "የማስተማር ደስታ" ነው። በመሠረቱ፣ በሩሂ ተቋም የሚመከሩት ሁሉም የአገልግሎት ተግባሮች፣ በባሃኦላህ ግልጸት ውቅያኖስ ውስጥ የምናገኛቸውን የመለኮታዊ ጥበብ ዕንቁዎች ከሌሎች ጋር መካፈልን ያካትታል። የመጀመሪያው ክፍል ጥናት የተወጠነው በዚህ ተግባር ውስጥ የሚገኘውን ደስታ ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ ነው። ተሳታፊዎች ስለ አምላክ ቃል እና ይህንንም ከሌሎች ጋር መካፈል ምን ዓይነት መባረክ እንደሆነ እንዲያጤኑ ብዛት ባላቸው ክፍሎች ላይ ይጠየቃሉ። ከዚህ ተግባር፣ የአገልግሎት ጎዳና ስንጓዝ እርምጃዎቻችንን የሚያነቃቃው ደስታ እንደሚከሰት፣ ክፍሉ ሃሳብ ይሰነዝራል። ሆኖም ይህን ጥልቅ መንፈሳዊ እውነታ ሙሉ ለሙሉ ካመንበት በኋላም፣ የአገልግሎት መለያ መሆን ላለባቸው ባህርያትና አመለካከቶች ትኩረት መስጠት ካቃተን የማስተማር ደስታን ልናጣ እንችላለን። እነዚህ በመጪዎቹ ብዙ ተከታታይዎቹ መጻሕፍት ውስጥ የመወያያ ግብ ናቸው፣ ጥቂቶቹ ብቻም እዚህ በምዕራፍ 7 ውስጥ በሚጀምረው መላቀቅ የሚጤኑ ናቸው። ውጫዊ ተፅዕኖዎች የአገልግሎት ደስታን ካላደበዘዙት መቅረት የማይችል ባሕርይ ላይ ለማሰላሰል መሠረት የሚሆኑ አንዳንድ የተመረጡ ጥቅሶች ከባሃኢ ቅዱሳን ጽሑፎች ይወጣሉ። አስፈላጊ የሆነው ጉዳይ ተሳታፊዎች ጥናታቸው ሲገባደድ መላቀቅ

ማለት ገለልተኝነትን ወይም ምንም አያገባኝም ማለትን እንደሚያመለክት ዓይነት የተሳሳተ ዕይታ ይዘው መውጣት የለባቸውም። ሁሌም የተሻለ ውጤት ለመቀዳጀት ስንጥር ኃይላችንን ለማጎልበት እና የአገልግሎታችንን ውጤታማነት ለማሳደግ በቀጣይነት መታገል አለብን። ይህ ስለጥረት ባሕርይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረን ይፈልጋል፣ በምዕራፍ 8 የሚጤን ርዕስ ይሆናል። ለአገልግሎት ጎዳና መሠረታዊ የሆኑት ሁለት ባህርያት፣ ቀና ነገርን መጠበቅና አመስጋኝነት በቀጣዩና የመጨረሻው ምዕራፍ በአጭሩ የሚዳሰሱ ናቸው።

የመጽሐፉ ሁለተኛው ክፍል፣ "አነቃቂ ንግግሮች"፣ የኢመደበኛ ንግግር ደረጃን ሁኔታዎች ሲፈቅዱ መንፈሳዊ መርሆዎችን በማጣቀስ ከፍ የማድረግ ችሎታ ላይ ያተኩራል። ቃል በቃል ጥቅስ ባይሆኑም፣ በአብዱል-ባሃ ንግግሮች ላይ በመመርኮዝ እና እርሱ የተጠቀመባቸውን በዛ ያሉ ቃላትና ሐረጎች በማካተት፣ በተለያዩ ርዕሶች ላይ በዛ ያሉ አጫጭር ንግግሮችን ይይዛል። ሁሉን አቀፍ ተጽዕኗቸው፣ በሁሉም ፊርጅ ስላሉ ሰዎች እሾቶችና ጉዳዮች ይናገራሉ። ንግግሮቹን በማጥናት ተሳታፊዎች አብዱል-ባሃ መንፈሳዊ መርሆዎችን ካብራራበት አቀራረብ መነቃቀትን እንደሚያገኙ እና የባሃኦላህ ግልጸት ውቅያኖስ ውስጥ የሚገኙትን ዕንቁዎች ለማሰስ ጥረት ሲያደርጉ ወደ እርሱ የመመልከትን ልምድ እንዲቀዳጁ፣ የአባቱን አስተምህሮዎች ትርጉምና አንደምታዎች መገንዘብ እና ከሌሎች ጋር በለጋስነት እንደሚያካፍሉ ተስፋ ይደረጋል።

የክፍሉን ዓላማ ለማሳካት፣ ተሳታፊዎች እያንዳንዱን ንግግሮች ለብዙ ጊዜ እንዲከልሱዋቸው፣ የሃሳብ ቅደም ተከተልን እንዲለዩ፣ ሃሳቡን ከመላበሳቸው የተነሳ ተፈጥሮአዊ በሆነ መልኩ መግለጽ እስኪችሉ ድረስ መናገር እንዲለማመዱ ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል። በመጀመሪያ አንዳንዶች በመሠረቱ ንግግሮችን በቃል ሊደገሙ እና ከሞላጎደል በክፍሉ ውስጥ በሚታየው መልኩ  ይደግሙታል። ይህ የሚጠበቅ ነው። ስለ እምነቱ ያላቸው ዕውቀት ሲጠልቅና ልምዳቸው ሲያድግ፣ ከሌሎች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነቶች/መስተጋብሮች ውስጥ የሚንጸባረቅ ሰፋ ያለ የይዘትና ይበልጥ የዳበረ ቃላት የመጠቀም አቅም ይኖራቸዋል። በዚህ ደረጃ፣ ኣስጠኚው ያንን መገንዘብ የሚኖርበት፣ የሚፈለገውን ሁለት ገፅታ ነው፦ ትምህርቶችን በማስረዳት ረገድ ቀላል መሆን እና ከአብዱል-ባሃ አስተሳሰብ ጋር መጣጣምን።

የእያንዳንዱን ንግግር ይዘት ለማቅረብ የቡድኑ አባላት ከተማሩ በኋላ፣ ያጠኑዋቸውን ሃሰቦች ለቤተሰቦቻቸው፣ ለጓደኞቻቸው፣ እና ለሥራ አጋሮቻቸው አሳሳቢ ከሆኑባቸው ጉዳዮች ጋር እንዲያዛምዱ ወደሚበረታቱበት ሌላ ተግባር ይሸጋገራሉ። ከዚህ አኳያ፣ በጭውውት ውስጥ ስለሚነሱት አንዳንድ ርዕሶችና ጥያቄዎች እንዲያስቡ ይጠየቃሉ እንዲሁም የትኞቹ ሃሳቦች ወደ ውይይት የማስገባት ዕድል እንደሚሰጧቸው ይወስናሉ። ለተወሰኑ ንንግግሮች፣ በሁሉም ስፍራ ላሉ ሰዎች አሳሳቢ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በአብዱል-ባሃ የተገለጹት መንፈሳዊ መርሆዎች እንዴት ብርሃን እንደሚፈነጥቁ ለማብራራት አንድ ወይም ሁለት ምሳሌዎች ተጠቅሷል። ይህ ልምምድ ፍሬያማ የሚሆነው፣ የመጽሐፍ ጥናቱ በሒደት ላይ እያለ፣ አስጠኚው እያንዳንዱ አባል ከንግግሮቹ አንዱን እና በያዘው ሃሳብ ላይ የሚያናግራቸው ሁለት ግለሰቦች እንዲመርጥ የሚያግዘው ከሆነ ነው። በዚህ መንገድ፣ በጋራ ሲገናኙ፣ ስለተጠመዱበት/ ስለያዙት የጭውውቶች ውጣውረድ አንዱ ለሌላው ለመግለጽ ለተሳታፊዎች ጊዜ ሊመደብላቸው ይችላል።

በክፍሉ ውስጥ ላለ እያንዳንዱ ንግግር፣ ከባሃኦላህ ቅዱሳን ጽሑፎች ጥቂት ምንባቦች በቃል እንዲጠኑ ተካተዋል። ከተከታታይዎቹ መጻሕፍት ውስጥ በአንደኛው መጽሓፍ እንደታየው የሩሂ ተቋም በቃል መያዝ ላይ የሰጠው ትኩረት፣ በመጽሐፍ 2 ውስጥ ይበልጥ ጎልቶ ይመጣል። በዚህ ደረጃ፣ ተሳታፊዎች ከቅዱሳን ጽሑፎች ምንባቦች በተደጋጋሚ ወደ አዕምሮአቸው ከማምጣት ስለሚያገኙት

መንፈሳዊ ምግብ ግንዛቤው እንዳላቸው፣ ታሳቢ ተደርጓል። ስለዚህ፣ በዚህ መጽሐፍ፣ የአምላክ ቃል በሰው ልጅ ልብ ላይ ያለውን ተጽዕኖ ያሰላስላሉ፣ እንደ ሁለተኛው በሦስተኛውም ክፍል ውስጥ፣ በቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ የሚገኙትን መርሆችና ሃሳቦች በንግግሮቻቸው ውስጥ ለማቅረብ እንዲሁም፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ምንባቦችን በቀጥታ መጥቀስን ይማራሉ። በአገልግሎት ጎዳና ስንጓዝ ትምህርቶቹን በትክክል ለመግለጽ፣ ለሌሎች ንፁሕ በሆነ መልኩ /እንዳሉ/ ለመስጠት፣ ሁላችንም ልናዳብረው ከምንሻው ችሎታዎች መካከል ነው። ያን ለመጀመር የላቀው ሁኔታ የአብዱል-ባሃን ገለፃዎች በማጥናት እና እርሱ ባደረገው መልክ ለመግለጽ መሞከር ሁለተኛው ክፍል የተዋቀረበት መሠረታዊ መርህ ነው።

ከላይ እንደተመለከተው፣ "የጥልቀት ጭብጦች" የተሰኘው ሦስተኛው ክፍል፣ለማኅበረሰቡ ሕይወት ወሳኝ በሆኑ ውይይቶች ውስጥ ለማሳተፍ/ለመጥመድ ግልጽ ዓላማ ወዳጆችን እና ጎረቤቶችን መጎብኘት፣ ወደሚለው በዚህ መጽሐፍ ወደተዳሰሰው የአገልግሎት ተግባር ይዞራል። በክፍሉ ውስጥ ሦስት ዓይነት ጭውውቶች ተወጥኗል፣ ለእያንዳንዱም የተወሰነ ይዘት ቀርቧል። የመጀመሪያው ዓይነት ስልታዊ በሆነ የጉብኝት ፕሮግራም የመንደር ወይም አጎራባች ሠፈር ነዋሪዎች ጋር የሚዳሰሱ ተያያዥነት ባላቸው ጭብጦች ዙሪያ ያጠነጥናሉ። የተዘረዘረው ይዘት በተለያዩ መንገዶች ፍላጎት ካላቸው ታዳሚዎች ጋር በአግባቡ ሊካፈል የሚችል ቢሆንም፣ የቤተሰቡን አባላት ስለ እምነቱ ያላቸውን ዕውቀት ለማጥለቅ ዕድል ለመስጠት - የሚለው የጭብጡ ቀዳሚ ዓላማ - እጅግ በጣም ጠቃሚ ይሆናል። ስለዚህ፣ ክፍሉ በአብዛኛው፣ በዚህ ዓይነት ጭውውት ላይ ትክረቱን አድርጓል።

ሆኖም በቅርብ ዓመታት ቤቶችን የመጎብኘት ልምድ አዲስ አቅጣጫዎችን ይዟል፣ በተለይም አነስ አነስ ባሉ ወደ መንደርና ከተማ ቀመስ አጎራባች ሠፈሮች ደረጃ ድረስ ባነሱ መልክዓ ምድራዊ ክፍሎች፣ እንደ አስጠኚ፣ የታዳጊ ወጣት ቡድን አነቃቂዎች፣ እና የሕፃናት ክፍል አስተማሪዎች ሆነው ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ የግለሰቦች ቁጥር እያደገ መምጣቱ ታይቷል። በተለይም ተግባሩ የእምነቱን ዕውቀት ከማስራጨት ዓላማ ጠቃሚነቱ ባሻገር፤ የታዳጊ ወጣቶችን በመንፈስ የማጎልበት እና የሕፃናት መንፈሳዊ ትምህርት ፕሮግራሞች ውጤታማነት ገሃድ መውጣትም ወሳኝ መሆኑን አሳይቷል። በዚህም ውስጥ፣ግልፅ እየሆነ የመጣው ነገር በሁለቱም ፕሮግራም ውስጥ ካሉ ወጣቶች ወላጆች ጋር ቅርፅ ስለሰጧቸው ጽንሰ-ሃሳቦችና አቀራረቦች ለመወያየት በአነቃቂዎችና አስተማሪዎች ቋሚ ጉብኝቶች መካሄድ ይኖርበታል። እንዲህ ያሉት ውይይቶች በክፍል 14 እና 15 የተዳሰሱትን ሁለተኛውን ዓይነት ጭውውት ያካትታሉ። ተሳታፊዎቹ ከሁለቱ ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ጋር ይበልጥ እየተዋወቁ የሚመጡት ወደፊት በሚመጡ ኮርሶች/ስልጠናዎች ስለሆነ፣ በእነዚህ ምዕራፎች የታቀፈው ይዘት ሁሉን አቀፍ አይደለም። ነገር ግን በዚህ የመጀመሪያ ደረጃ የዚህን ዓይነት ጭውውትን እና የሕፃናት አስተማሪዎችን እንዲሁም የታዳጊ ወጣት ቡድኖች አነቃቂዎችን ወደ ወላጆች በሚያደርጉት ጉብኝት አብሮ መጓዝ አስፈላጊነት ማወቁ በጣም ውጤታማ ሊያደርግ ይችላል።

በክፍሉ ውስጥ የተወጠነው ሦስተኛው ዓይነት ጭውውት በጣም ለተለየ ዓላማ ያገለግላል። በጣም ብዙ ወጣት ወንዶችና ሴቶች ለዓለም መሻሻል አስተዋፅዖ ለማበርከት ያላቸው የጋለ ፍላጎት መገለጫ የሚያገኙበትን ጎዳና እየፈለጉ ናቸው። እነርሱ ያን የኅብረተሰብ መለወጥ እየጠበቀ፣ አልፎ ተርፎም ማውጣት የሚችለውን እየተመኘ ያለ ታላቅ የአቅም ማከማቻን/ቋትን ይወክላሉ። ለወጣትነት ዘመን የተለዩ በሚሆኑት ዕድሎችና ኃላፊነቶች ላይ ለማሰላሰል በሚያስችሉ በአቻዎች መካከል የሚካሄድ ጭውውት፣ ከመላ ኃይሉና የተለየ ዕምቅ አቅሙ ጋር፣ በአብዛኛው ጊዜ በዓለም ዙሪያ ባሉ መንደሮችና አጎራባች ሠፈሮች እየተካሄዱ ያሉት ሥራዎች ውስጥ ባሉ አገልግሎቶች ዙሪያ ወደ ውይይት ይመራል ፍላጎትንም ያጭራል። ይህን ተከትሎም፣ ብዙዎች እየመጡ ላሉ ትውልዶች እንደ የሕፃናት ክፍል አስተማሪዎችና የታዳጊ ወጣት ቡድኖች አነቃቂዎች ሆኖ መንፈሳዊ ትምህርት ለማቅረብ

የሚያስችላቸውን አቅም የሚያገኙበትን መፍትሔ የሚሰጣቸውን የተቋም ስልጠና/ኮርስ ለመቀላቀል የሚቀርብላቸውን ግብዣ በደስታ ይቀበላሉ። ምዕራፍ 9 እና 10 በዚህ ዓይነቱ ጭውውት ሊዳሰሱ የሚችሉ አንዳንድ ሃሳቦችን ያቀርባሉ።

ግለሰቦች ትርጉም አዘል ጭውውቶች ለማስጀመርና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የሚያበቃቸውን ችሎታዎች ለማዳበር፣ በዕርግጥ ክፍሉ ሰፋ ያሉ ጭብጦችንና ተያያዥ ይዘትን ከመጠቀም በላይ መጓዝ አለበት። ሃሳቦችን በጥራት ከመግለፅ ችሎታ በተጨማሪ፣ ተሳታፊዎች ተገቢውን አመለካከቶችና መንፈሳዊ ባህርያት ማዳበር ይኖርባቸዋል። እነዚህ በክፍሉ ለሚገለጡት አብዛኞቹ ማብራሪያዎች መነሻ ይሆናሉ፣ ነገር ግን ለተነሱት ችሎታዎች አስፈላጊነታቸው ግልጽ የሚሆነው በምዕራፍ 4፣ ማለትም ተሳታፊዎች ለጉብኝት ስንዘጋጅ ልቦቻችንና አዕምሮአችን ሊሞላ የሚገባው በምን ዓይነት ስሜቶችና አስተሳሰቦች እንደሆነ የምናስብበት ሲሆን፣ በምዕራፍ 5 ውስጥም በትህትና ባህርይ ላይ የሚያሰላስሉበት ነው። ምንም ያህል ብዙ ዕውቀት ቢኖረን፣ ምንም ያህል ሃሳቦችን በጥራት መግለፅ ብንችል፣ የጭውውቶቻችን ውጤታማነት የሚወሰነው ወደነሱ በምናመጣው ባህርያትና አመለካከቶች በመሆኑ፣ አስጠኚው እነዚህ ምዕራፎች በተሳታፊዎች በቂ ትኩረት ማግኘቱን ለማረጋገጥ ይፈልጋል።

በዚህ ተከታታይ መጽሐፍት ውስጥ የተገለጹት የአገልግሎት ተግባሮች፣ ለአንድ ማኅበረሰብ ዕድገትና ዕመርታ ማዕከል ቢሆኑም፣ ከምንም ነገሮች በላይ የግለሰብ ችሎታን በጥናትና ተግባር አማካይነት ለማሳደግ የሚፈልግ ሂደት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። እያንዳንዱ አስጠኚ ሊያጤን የሚገባው ነገር ቢኖር እነዚህ ተግባሮች አንዳቸው በሌላው ላይ የሚገነቡ፣ ከውስብስብነት ረገድ ከመጽሐፍ ወደ መጽሐፍ እያደጉ እንደሚሄዱ ነው። እያንዳንዱን የአገልግሎት ተግባር ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን መማር እነዚያን የሚከተሉትን ለመፈጸም ለሚያስፈልገው ችሎታ ወሳኝ ይሆናል። በዚህ መጽሐፍ እንደ ሃሳብ እንደቀረበው፣ ወደ አንድ ቤት በሚደረጉ በዛ ያሉ ጉብኝቶች ላይ ቀጣይነት ያለውን ጭውውት ለማስቀጠል፣ በመጽሐፍ 1 ውስጥ ከሚበረታታው በራስ ብቻ ወይም ከጥቂት ሌሎች ጋር በመተባበር ከሚስተናገድ ቋሚ ጸሎተ ሱታፌ ተግባር ይበልጥ ፈታኝ መሆኑ ግልጽ ነው። እናም ወደፊት የሚመጡትን ይበልጥ የተወሳሰቡ የአገልግሎት ተግባሮች ለማከናወን፣ ተሳታፊዎች እዚህ የተገለጹትን ችሎታዎች ማዳበር እንዴት ጠቃሚ እንደሆነ ለመመልከት አስቸጋሪ አይሆንም።

በመጽሐፍ 1 በመግቢያ ሃሳቦች ውስጥ እንደተጠቀሰው፣ በመላው ዓለም በተቋሙ ኮርሶች ውስጥ ያሉ ተሳታፊዎች ከተለያዩ ዳራዎች የመጡና፣ ሲጀምሩ፣ ከባሃኢ ትምህርቶች ጋር የተለያየ የትውውቅ ደረጃ ነበራቸው። ይህንን ሁለተኛ መጽሐፍ በሚጀምሩበት ግዜ፣ በዕርግጥ እያንዳንዱና ሁላቸውም በኮርሶቹ አማካይነት በተከፈተው የአገልግሎት ጎዳና ላይ ይገባሉ። ነገርግን አንዳንድ ልዩነቶች ይኖራሉ። ለምሳሌ፣ ከወጣቶች አኳያ፣ በልጆችና ታዳጊ ወጣቶች ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ውስጥ ካላለፉ በቀር፣ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት አብዛኞቹ ንግግሮችና ጭብጦች አዲስ ይሆንባቸዋል፣ ጥናቱም ስለእምነቱ ያላቸውን ዕውቀት ማጥለቂያ መንገድ ሆኖ ያገለግላል። አስጠኚው የኮርሱ ዋና ግብ የሆነውን ተሳታፊዎች በትርጉም አዘልና አነቃቂ ጭውውት እንዲጠመዱ ለማስቻል የሚለውን ማሳካቱን እያረጋገጠ፣ በእያንዳንዱ የቡድን አባል ግንዛቤን ለማስረጽ አስፈላጊውን ተጣጣፊነትና ፈጠራ ለማሳየት ዝግጁ ሊሆን ይገባል። ከዚህም በላይ መጽሐፉ ጥቅም ላይ እየዋለ ባለበት በሺዎች በሚቆጠሩ አካባቢዎች፣ ሦስቱ ምዕራፎች አስተዋፅዖ ሊያበረክቱ የተነሱበት የማኅበረሰብ ግንባታ ሂደት በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ አይደለም። ስለዚህ፣ እየተማርን ያለውን ወደ ተግባር መለወጥ፣ ከአንድ አካባቢ ወደሚቀጥለው የተለየ አቀራረብ ሊፈልግ ይችላል፣ ይህም ደግሞ፣ አንድ አስጠኚ አንድን ቡድን በእነዚህ ገጾች ውስጥ ሲያስኬድ የእያንዳንዱ አባል ፍላጎቶች በምን ያህል ጥንቃቄና ጥልቀት ምላሽ መስጠት እንዳለበት ማመላከቻ ያቀርባል።



# የማስተማር ደስታ

## ዓላማ

የማስተማር ደስታ የሚገኘው የአምላክን ቃል
ከሌሎች ጋር በመካፈል ተግባር
መሆኑን ለማድነቅ

# ምዕራፍ 1

ለማገልገል መነሳት ጥናትና ተግባርን ለማቀናጀት የሚፈልግ በሩሂ ተቋም የሚቀርብ በተከታታይ ኮርሶች/ሥልጠናዎች ውስጥ ሁለተኛው ነው፡፡ ዓላማው ሁለት እጥፍ ዓላማችሁን ለማሳካት ጥረት ስታደርጉ ወደገባችሁበት የአገልግሎት ጎዳና ላይ ይበልጥ ዕመርታ እንድታሳዩ ለመርዳት ማለትም የገዛ ራሳችሁን መንፈሳዊና አዕምሮአዊ ዕድገት ለመዳሰስ እና ለኅብረተሰብ ለውጥ አስተዋፅዖ ለማበርከት ነው፡፡ ከመጀመሪያው ኮርስ ተሳትፎአችሁ፣ እያመላከትን ያለነው ጎዳና በተያያዥ የአገልግሎት ተግባሮች የሚገለጽ፣ በባሃኦላህ ቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ እንደተተለመው ዓይኖቻችን የአዲሱ ዓለም ሥርዓት ግብ ላይ አትኩረን የምናከናውናቸው ተግባሮች መሆናቸውን አስቀድሞ ተገንዝባችሁ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ፣ "በአገልግሎት ጎዳና መንዝ" ብለን በአብዛኛው የምንጠራው የእርሱን ትምህርቶች በገዛ ራሳችን ሕይወት እና በማኅበረሰቡ ሕይወት ላይ ለመተግበር የምናደርገውን ጥረቶች ያካትታል፡፡ እርሱ ራሱ ስለግልጸቱ በእነዚህ ቃላት ይናገራል፦

> **"አገልጋዮቼ ሆይ! ቅዱሱና በመለኮታዊ ኃይል የታዘዘው ግልፀቴ፤ በጥልቀቱ ውስጥ ሊቆጠሩ የማይቻሉ ታላቅ ዋጋና የላቀ አንጸባራቂነት ያላቸው ዕንቁዎች በተደበቁበት ውቅያኖስ ሊመሰል ይችላል፡፡ ከፍለጋው ጉጉትና ከአደረጋቸው ጥረቶች ጋር ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ በማይሻረውና በድብቁ የአምላክ ጽላቶች ውስጥ አስቀድሞ ከታዘዙት ጥቅሞች ይካፈል ዘንድ፤ ወደዚህ ውቅያኖስ ዳርቻዎች ለመድረስ ራሱን ማነሳሳትና ጥረት ማድረግ የእያንዳንዱ ተመራማሪ ተግባር ነው፡፡"[1]**

በዚህ የመጀመሪያ ክፍል፣ በባሃኦላህ ግልፀት ውቅያኖስ ውስጥ የሚገኙትን ዕንቁዎች ስናገኝ እና ከሌሎች ጋር ስንካፈላቸው ሃሳቦቻችን ልቦቻችንን ወደሚሞላ ደስታ ይዞራል፡፡ ቀድሞውኑ ከመጽሀፍ 1 ጥናታችሁ በእርሱ ቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ የሚገኙ የመለኮታዊ መርሆ ዕንቁዎች እንዴት ፍፁም ውብ እንደሆኑ ተገንዝባችኋል፡፡ በጥቂት በተውጣጡ ጽሑፎች ላይ ይበልጥ እናሰላስል፦

**"የአምላክ ልሳን ብርሃኑ፣ እነዚህ ቃላት የሆኑት መብራት ነው፦ እናንተ የአንድ ዛፍ ፍሬዎች፣ የአንድ ቅርንጫፍም ቅጠሎች ናችሁ፡፡"[2]**

**"በእኔ ዘንድ ከሁሉም ይበልጥ ተወዳጅ ፍትሕ ናት፤ እኔን የምትሻ ከሆነ ፊትህን አታዙርባት፣ ምሥጢሬንም አካፍልህ ዘንድ ቸል አትበላት፡፡"[3]**

**"ለምትኖሩበት ዘመን ፍላጎቶች የኃላፊነት ስሜት የተመላበት ሃሳብ ይኑራችሁ፣ ምክክራችሁም በአጣዳፊና አስፈላጊ ጉዳዮችዋ ላይ እንዲያተኩር አድርጉ፡፡"[4]**

**"ሰው ሁሉ የተፈጠረው ያለማቋረጥ እያደገ የሚሄደውን ሥልጣኔ ወደፊት ለማራመድ ነው፡፡"[5]**

**"ዓለም አላፊ ነው፣ እና ዘለዓለማዊ የሆነው የአምላክ ፍቅር ነው፡፡"[6]**

**"አንተ ፋኖሴ ነህ ብርሃኔም በውስጥህ አለ፡፡ ከእርሱም ብሩህነትን አግኝ ከእኔም በቀር ሌላ አትሻ፡፡ ባለ ፀጋ አድርጌ ፈጥሬህ በረከቴንም በብዛት በላይህ አዝንቤአለሁና፡፡"[7]**

እነዚህን አጭር ምንባቦች በግዜ ሂደት በቃላችሁ ለመያዝ ትፈልጉ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ 2

የዚህ ክፍል ዋና ጭብጥ ላይ ውይይቶቻችሁን ለመጀመር፣ በቀደመው ክፍል ውስጥ የተጠቀሰውን ምንባብ ደግማችሁ አንብቡና ተከታዮቹን መልመጃዎች ሥሩ፦

1. ከሥር ያሉትን ዓረፍተነገሮች አሟሉ።

   ሀ. ወደ ባሃኦላህ ግልፀት ውቅያኖስ ______________________

   እራሳችንን ______________ እና ______________

   የእኛ ተግባር ነው።

   ለ. በማይሻረውና በድብቁ የአምላክ ጽላቶች ውስጥ አስቀድሞ ከታዘዙት ________ እንካፈል ዘንድ ወደ ባሃኦላህ ግልጸት ውቅያኖስ ዳርቻዎች ለመቅረብ ጥረት ማድረግ አለብን።

   ሐ. ከባሃኦላህ ግልጸት ውቅያኖስ የምንካፈላቸው ጥቅሞች ከ ______________ ______________________ ጋር ተመጣጣኝ ይሆናሉ።

2. ራስን "ማነሳሳት" ማለት ምን ማለት ነው? ______________________

   ______________________________________________

   ______________________________________________

3. ወደ አንድ ነገር "ለመድረስ ጥረት ማድረግ" ማለት ምን ማለት ነው? ____________

   ______________________________________________

   ______________________________________________

4. እያንዳንዱ ተመራማሪ ምን ለመቀዳጀት ጥረት ማድረግ አለበት? ______________

   ______________________________________________

   ______________________________________________

5. አንድ ነገር ከሌላው ነገር ጋር "ተመጣጣኝ መሆን" ማለት ምን ማለት ነው? ________

   ______________________________________________

   ______________________________________________

6. የእርሱን ግልጸት ውቅያኖስ ጥቅሞች የምንቀበለው ባደረግናቸው ጥረቶች ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ እንደሆነ ባሃኦላህ ይነግረናል።

ሀ. የእነዚህ ጥቅሞች ተቀባዮች እንድንሆን ከምናደርጋቸው ጥረቶች አንዳንድ ምሳሌዎችን ስጡ፦

ለ. ከምንቀበላቸው ጥቅሞች አንዳንድ ምሳሌዎች ስጡ:-

## ምዕራፍ 3

የባሃኦላህ ግልጸት ልክ በጥልቀቱ ውስጥ በዋጋ የማይተመኑ ዕንቁዎች እንደሚገኙበት ውቅያኖስ መሆኑን ካወቅን፣ እያንዳንዳችን ያለውን ድርሻ ለመካፈል እና ሌሎች ወደ ዳርቻው እንዲቀርቡ ለማገዝ የተቻለንን ሁሉ ጥረት እናደርጋለን:: ነገርግን የዚህ ውቅያኖስ ዳርቻዎች ከኛ ምን ያህል ሩቅ ናቸው? ብለን ራሳችንን ልንጠይቅ እንችላለን:: ባሃኦላህ እንዲህ ያውጃል፦

**"አገልጋዮቼ ሆይ! አንዱና እውነተኛው አምላክ ምስክሬ ነው! ይህ እጅግ በጣም ታላቅ፣ ይህ ለጥልቀቱ መጨረሻ የሌለውና የሚተምመው ውቅያኖስ ቅርብ፣ በሚያስገርም ሁኔታ ቅርባችሁ ነው:: ተመልከቱ ከሕይወት ደም ሥራችሁ ይበልጥ ቅርባችሁ ነው! ብትፈልጉት እንደ ዓይን ጥቅሻ በሆነ ፍጥነት ልትደርሱበትና ከዚህ ከማይጠፋው ልግስና ከዚህ ከአምላክ ከተሰጠው ፀጋ፣**

**ከዚህ ከማይበላሽ ሥጦታ፣ ከዚህ ከእጅግ በጣም ፍቱንና ሊነገር ከሚቻል በላይ ከሆነው ክቡር ችሮታ ለመካፈል ትችላላችሁ።"**[8]

1. "ይህ እጅግ በጣም ታላቅ፣ ይህ ለጥልቀቱ መጨረሻ የሌለውና የሚተምመው ውቅያኖስ" የሚለው ሐረግ ምንን ያመለክታል?______________________________________

____________________________________________________________

2. ይህ ውቅያኖስ ለኛ ምን ያህል ቅርብ ነው? ___________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

3. ይህንን ውቅያኖስ በምን ያህል ፍጥነት ልንደርስበት እንችላለን? _________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

4. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች አሟሉ፦

ሀ. የባሃኦላህ ግልጸት እጅግ በጣም ታላቁ ውቅያኖስ ለእኛ ቅርብ፣ ________________________

___________________________________________ነው።

ለ. የባሃኦላህ ግልጸት ውቅያኖስ ከሕይወት ደም ሥራችን ይበልጥ ____________________ነው።

ሐ. ብንፈልግ፣ ከእርሱ ግልጸት ውቅያኖስ እንደ______________________________________

በሆነ ፍጥነት ____________________________እና __________________________________

__________________________________________________________

__________________________________________________________እንችላለን።

መ. ______________________________ ከእርሱ ግልጸት ውቅያኖስ እንደ ዓይን ጥቅሻ በሆነ ፍጥነት ልንደርስበትና ልንካፈል እንችላለን።

## ምዕራፍ 4

የባሃኦላህ ግልፀት ውቅያኖስ ዳርቻዎች ከደረስን በኋላ፣ በገዛ ራሳችን ጥናት፣ ጸሎትና ሱባዔዎች እንዲሁም የእርሱን እምነትና የሰው ዘርን ለማገልገል በምናደርገው ጥረቶች፣ ከሐብቶቹ እንቋደሳለን እንዲሁም ከመለኮታዊ መርሆ ዕንቁዎች በነፃነትና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከሌሎች ጋር እንካፈላለን። የዚህ የተቀደሰ ተግባር ቋሚ ማሳሰቢያ የሆነውን፣ ተከታዩን ምንባብ በቃል ለመያዝ ትንሽ ግዜ መውሰድ ትፈልጉ ይሆናል፦

**"በአምላክ መንገድ ተጓዥ ሆይ! ከእርሱ የፀጋ ውቅያኖስ ድርሻህን ውሰድ፣ በጥልቀቶቹም ውስጥ ተሸሽገው ከሚገኙት ነገሮች ራስህን አትንፈግ። ከእነዚያ ሐብቶቹን ከተካፈሉትም ሁን። ከዚህ ውቅያኖስ አንድ የጤዛ ጠብታ፣ በሰማያትና በምድር በሚገኙት ሁሉ ላይ ቢረጭ፣ በፍፁም ኃያሉ፣ በሁሉን አዋቂው፣ በፍፁም ጠቢቡ አምላክ በረከት ሊያበለፅጋቸው በቂ ይሆናል። ከሰው ሰራሽ ውስንነት ሁሉ እንዲነጹና ወደ ኃያሉ የአምላክ መንበር፣ ወደዚህ የተቀደሰና አንፀባራቂ ወደሆነው ነጥብ እንዲቀርቡ፣ በመላቀቅ እጆች ከሕይወት ሰጭ ውሃዎቹ ቀድተህ፣ በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ላይ አርከፍክፍ።"[9]**

## ምዕራፍ 5

የሚፈልጉትን ጥናትና ተግባር በማከናወን በተቋም ኮርሶች ውስጥ ስንዘልቅ፣ ለአገልግሎት ያለን አቅም ያድጋል፣ ለልቦቻችንም ታላቅ ደስታ የሚያመጣ እና ሁለት እጥፍ ዓላማችንን ለማሟላት የሚረዳንን የአገልግሎት ተግባሮች ማለትም የሕጻናት መንፈሳዊ ትምህርት ማስተማሪያ ክፍሎች፣ ታዳጊ ወጣቶችን በመንፈሳዊ ጉልብትና ፕሮግራም ውስጥ ማሳተፍ፣ እንዲሁም አንድ የወዳጆች ቡድን የዋናውን ተከታታይ መጽሐፍት እንዲያጠኑ ማገዝ የመሳሰሉትን ተግባሮች ለማከናወን እንችላለን። በዚህ ሁሉ ጉዞ ውስጥ፣ ከሌሎች፣ ወጣትም ሆኑ የዕድሜ ባለፀጎች ጋር የምንካፈለው፣ የአምላክ ቃል፣ የመነቃቃታችን ቋሚ ምንጭ ይሆናል። ስለዚህ በሰው ልብ ላይ ስላለው ኃይልና ተፅዕኖ ማሰላሰላችን ተገቢ ይሆናል። በቀጣዩ ጥቅስ፣ ባሃኦላህ ስለዚህ ኃይል ይናገራል፦

**"የአምላክ ቃል፣ ሥሮቹ በሰዎች ልቦች ውስጥ በተተከለ ችግኝ ሊመሰል ይችላል። ሥሮቹ ጠንክረው ይይዙ፣ ቅርንጫፎቹም እስከ ሰማይና ከዚያም በላይ ይዘረጉ ዘንድ፣ በጥበብ ሕያው ውሃ፣ በተባረኩና በተቀደሱ ቃላት፣ አማካይነት ዕድገቱን የመንከባከብ ግዴታ አለባችሁ።"[10]**

1. የአምላክ ቃል ከምን ጋር ነው ሊወዳደር የሚችለው? ______________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

2. የአምላክ ቃል ዛፍ ሥሮቹ የተተከሉት የት ነው? ______________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

3. የዚህን ዛፍ ዕድገት የምንከባከበው እንዴት ነው? ______________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

4. ይህ ዛፍ እስከ ምን ያህል ከፍታዎች ያድጋል? ______________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

5. የአምላክን ቃል ከሌሎች ጋር መካፈል ለምን የላቀ ጠቀሜታ እንዳለው በጥቂት ዓረፍተ ነገሮች ግለጹ።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

## ምዕራፍ 6

እስቲ በዕለት ተለት ሕይወቶቻችን የሚጠምዱንን የተለያዩ ዕንቅስቃሴዎች እናጢን። አካሎቻችንን እንመግባለን። አዲስ ዕውቀት ለማግኘት እና የአዕምሮአችንን አቅም ለማስፋት እናጠናለን። የኅብረተሰብ ምርታማ አባላት ሆነን ለመኖር የሚያስችሉንን ክህሎቶች እየሠራን እናዳብራለን። በስፖርትና መዝናኛ እንሳተፋለን። ለአዕምሮ ዕድገትና ቁሳዊ ደህንነት አስፈላጊ የሆኑት ሁሉም እንደዚህ ያሉ የበዙ ዕንቅስቃሴዎች የግዜያችንን ሰፋ ያለ ክፍል ይይዛሉ። ነገርግን በእያንዳንዱ ዕለት በመንፈሳዊነት የተሞሉ ማለትም በጸሎት ስንሳተፍ፤ የመለኮታዊ ትምህርቶች ዕውቀታችንን፣ለብቻችን ወይም ከወዳጆች ጋር ስናጠልቅ፤ ወይም ከብዙ መንገዶች በአንዱ፣ እነዚያ በዙሪያችን ያሉትን በባሃኦላህ ግልጸት ውቅያኖስ ውስጥ የተሸሸጉትን ዕንቁዎች እንዲያገኙ ስናግዝ፤ እነዚያ የተለዩ ጊዜያት አሉ። እነዚህ ጊዜያት ከልክ በላይ ውድ አይደሉምን? እንዚህን መንግሥተ ሰማያዊ ቡራኬዎችን ከመቋደስ የተሻለ ምን ደስታ አለ?

አብዱል-ባሃ ለሰው ዘር ልዕልና ራሳችንን እንድንሰዋ እንዴት እንዳበረታታን ሁሌም ማስታወስ ይገባናል።

> **“ሁላችንም በአንድ መለኮታዊ ዓላማ ተዋህደናል፣ ቁሳዊ ዓላማ የኛ አይደለም፣ የእኛ እጅግ የተወደደ እሾት የአምላክን ፍቅር በመላው ዓለም ማሠራጨት ነው።”**[11]

ለአብነት ከምዕራፍ 1 በቃላችሁ ከያዛችሁት ጥቅሶች መካከል አንዱን ከአንድ ወዳጃችሁ ጋር የመካፈል አጋጣሚ ተፈጠረ እንበል። በልባችሁ ውስጥ የሚሰማችሁ ደስታ ከየት የሚመጣ ነው? ተፈጥሮአዊ በሆነ መልኩ ወዳጃችሁ በባሃኦላህ ቃላት እንደሚነቃቃ ተስፋ ታደርጋላችሁ። ነገርግን ስትጠብቁት የነበረው ጉጉት ባያሳይ ወይም ባታሳይስ? በልባችሁ ውስጥ ያለው ደስታ በቀላሉ የሚጠፋ ነው? ለምን አይሆንም?

## ምዕራፍ 7

በሕይወቶቻችን ከምናከናውናቸው ተግባራት ሁሉ፣ የአምላክን ቃል ከሌሎች ጋር በመካፈል የምናሳልፋቸው ጊዜያት በልዩ ፀጋ የተሞሉ እንደሆኑ ስንገነዘብ፣ እጅግ ወሳኝ ወደሆነ ድምዳሜ እንደርሳለን፦ ይኸውም ከአገልግሎት የምናገኘው ደስታ በተግባሩ በራሱ ውስጥ ይገኛል። በዕርግጥ፣ የምናከናውነው የአገልግሎት ተግባር ተገቢዎቹን ውጤቶች እንዲያመጣ ተስፋ እናደርጋለን፣ ነገር ግን ከውጤቶቹ ጋር በጣም ከተጣበቅን፣ በውዳሴና ነቀፌታ የተጋነነ ተፅዕኖ ከደረሰብን፣ የማስተማርን ደስታ እናጣለን። ለማገልገል የሚያነሳሳን የአምላክ ፍቅር ሊሆን ይገባል እንጂ ስኬት ለመቀዳጀት በመፈለግ፣ ጥቅማጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ዕውቅናን ለማትረፍ መሆን የለበትም። በደስታ ለተመላ አግለግሎት ከእነዚህ ሁሉ መላቀቅ ወሳኝ ነው። የሚከተሉትን ጥቅሶች ማጥናት በዚህ ጭብጥ ላይ ለማሰላሰል ይረዳችኋል፦

> **"ባለሁለት ዕይታዎች ሰው ሆይ! አንዱን ዓይን ጨፍነህ ሌላውን ግለጥ። አንደኛውን ለዓለምና በውስጧም ላሉት ሁሉ ጨፍን፣ እንዲሁም ሌላውን ለተወዳጁ የተቀደሰ ውበት ግለጥ።"[12]**

> **"ወዳጆች ሆይ! ዘለዓለማዊውን ውበት መሞት ባለበት ውበት አትለውጡ፣ ፍቅራችሁንም በዚህ ጠፊ የትቢያ ዓለም ላይ አታኑሩ።"[13]**

> **"የልሳን ልጅ ሆይ! ፊትህን ወደኔ መልስ ከእኔም በስተቀር ሁሉንም ተው፤ ልዕልናዬ ነዋሪ ግዛቴም አይጠፋምና። ከእኔ በስተቀር ሌላ ብትሻ፣ አዎን፣ እስከ ዘለዓለምም በፍጥረተ-ዓለም ውስጥ ብትፈልግም እንኳ፣ ፍለጋህ ከንቱ ይሆናል።"[14]**

> **"የተወዳጀሁህ ባይተዋር ሆይ! የልብህ ሻማ በኃይሌ እጅ በርቷል፣ በእኔነትና በኃይለኛ ስሜት ተፃራሪ ነፋሶች አታጥፋው። የሕመሞችህ ሁሉ ፈውስ እኔን ማስታወስ ነው፣ አትርሳው። ፍቅሬን ሀብትህ አድርገውና ልክ እንደ ዓይንህ ብርሃንና እንደ ሕይወትህ ተንከባከበው።"[15]**

> **"መላቀቅ እንደ ፀሐይ ነው፤ በሚያበራበት በማንኛውም ልብ ውስጥ ስግብግብነትና የራስ ወዳድነትን እሳት ያጠፋል። እርሱ ዓይኑ በመገንዘብ ብርሃን የበራ በዕርግጥ ከዓለምና ከከንቱዎችዋ ራሱን ያላቅቃል።... ዓለምና የእርሷ ክፋት አያሳዝናችሁ። እርሱ ሀብት በከንቱ ክብር የማይሞላው፣ ድህነትም የማያሳዝነው ደስተኛ ነው።"[16]**

1. ከዚህ ዓለም መላቀቅ ማለት እንደባህታዊ መኖር ማለት ነውን? ____________________

______________________________________________

2. ከዚህ ዓለም መላቀቅና በተመሳሳይ ሁኔታ ቁሳዊ ነግሮች ማካበት ይቻላልን? ________________

________________________________________________________________________________

3. እያንዳንዱን የሕይወትን ሰዓት ለሥራው የሰጠ ሰው ከዚህ ዓለም ነገሮች የተላቀቀ ነውን?_____

________________________________________________________________________________

4. መሠረታዊ ፍላጎቶቹን ለማሟላት ያክል ብቻ ሠርቶ ቀሪ ግዜውን ያለምንም ሥራ የሚያሳልፍ ሰው ከዚህ ዓለም የተላቀቀ ነውን? ________________________________________________

5. የአገልግሎት መስክ ውስጥ ቁሳዊ ምቾት ማጣትን ለመቋቋም የማይችል ሰው ከዚህ ዓለም የተላቀቀ ነውን? ________________________________________________________________

6. ከቁሳዊ ይዞታዎች ባሻገር ብዙ ልንጣበቅባቸው የሚችሉ ነገሮች አሉ። ከምን ጋር ልትቀራኙ ትችላላችሁ፡-

- አንድ የአገልግሎት ተግባር ስታከናውኑና ማንም ዕውቅና ሳይሰጠው ቢቀር ለማቋረጥ የሚፈልግ ሰው ብትሆኑ?_______________________________________________________

- አንድ ሰው የምታካፍሉትን ሃሳብ ካልተቀበለው ስሜታችሁ የሚነካ ሰው ብትሆኑ? ________

________________________________________________________________________________

- በሌሎች መገለልን/ውግዘትን በመፍራት እምነቱን/አስተሳሰቡን የሚደብቅ ሰው ብትሆኑ?______

________________________________________________________________________________

7. መላቀቅ ገለልተኝነትን ወይም ግድየለሽነትን አያመላክትም። ከሚከተሉት የትኛው የአንድ ሰው ያለመላቀቅ ምልክት ሊሆን ይችላል?

_____ የሌሎችን ዕመርታ በመመልከት ደስታን ማግኘት

_____ ጥቂት ሕፃናት ከሥርዓት ውጪ ሲሆኑ ክፍሉን ማስተማር ማቆም

_____ ስለራስ ስኬቶች መፎከር/መመካት

_____ ጠንክሮ ማጥናትና አንድ ሰው ባመጣው ዕመርታ ዕርካታ መሠማት

_____ የጋራ ደህንነትን ለማገልገል እንዲቻል የራስን ችሎታ ለማሳደግ ጠንክሮ መሥራት

_____ በራስ የሥራ ዘርፍ ለልቀት ጥረት ማድረግ

_____ ንጽህናን መለማመድ እንዲሁም ቤትን ንጹህና የተስተካከለ ማድረግ

_____ የራስን ንብረቶች በአግባቡ መያዝ

_____ ለሌሎች ደህንነት መጨነቅ

_____ አንድ ሰው ላደረጋቸው ጥረቶች ምስጋና ካልተሰጠ ማዘን

8. መላቀቅ ለእያንዳንዳችን በጣም አስፈላጊ ስለሆነ በዚህ ምዕራፍ ያሉትን ጥቅሶች በሙሉ በቃል ለማጥናት ሃሳብ ቀርቧል።

## ምዕራፍ 8

ለሰው ልጅ የማገልገል አስደሳች ሕይወት ቡራኬዎችን ለመቀበል፣ ጥረት ለማድረግ ፈቃደኞች መሆን አለብን፣ ጥረቶቻችንም የተወሰነ ደረጃ መስዋዕትነት ይፈልጉ ይሆናል። "መስዋዕትነት" የሚለውን ቃል በዕለት ተለት ሕይወታችን በተደጋጋሚ እንጠቀምበታለን። ጎህ ሲቀድ፣ ጓደኞችን ከጉዞ እየተመለሰች ከሆነ፣ እሷን ለመቀበል በሌሊት ልንነሳ እንችላለን። ጥቂት የእንቅልፍ ሰዓታት መስዋዕት አደረግን ልንል እንችላለን። አንድ የምንወደው ሰው ይታመማል፤ እርሱን ለመንከባከብ ከምንወደው መዝናኛ ሰዓታችን ጥቂቱን እናሳልፋለን። በሕይወት ውስጥ እጅግ ጠንክረን መሥራት ያለብን አጋጣሚዎች አሉ፣ ግባችንን ለማሳካት ስንልም ምቾታችንን መስዋዕት እያደረግን ነው ብለን ልናስብ እንችላለን።

ሁላችንም ጊዜያችንንና ጉልበታችንን የቻልነውን ያህልም ከቁሳዊ ሐብቶቻችን በልግስና በማቅረብ፣ እምነቱን ለማገልገል የላቀ ፍላጎት አለን። ይህን ስናደርግ፣ በአገልግሎት ጎዳና ላይ የዚህን ዓለም ነገሮች ልንሰጥ እንደምንችል፣ ነገርግን በመንፈስ ስንገለብት እውነተኛ ደስታ እንደምናገኝ ማስታወስ ይገባናል። ወደፊት በሚመጡት ኮርሶች ውስጥ በመስዋዕትነት ተፈጥሮ ላይ ይበልጥ ለማሰላሰል አጋጣሚው ይኖረናል። ገና ከጅምሩ መገንዘብ ያለብን አስፈላጊ ነገር ለከፍተኛው ሲባል ዝቅተኛውን መተው እንደሚያካትት ነው፣ ልክ ዛፉ እንዲወለድ ዘሩ ራሱን መስዋዕት እንደሚያደርገው። መስዋዕትነት ደስታን አምጪ ነው፣ ይህም ደስታ ቀጣይነት ያለው ጥረት ለማድረግ ፍቃደኞች ካልሆንን የኛ ሊሆን አይችልም።

ባሃኦላህ እንዲህ ይገልፃል፡-

**"እርሱን የምንሻ ከሆነ፣ ጥረት ያስፈልጋል፤ ከእርሱ ጋር የመገናኘትን ወለላ ማር ለመጠጣት ከፈለግን፣ ፅኑ ፍላጎት ያስፈልጋል፤ ከዚህ ፅዋ ከቀመስንም፣ ዓለምን እርግፍ አድርገን እንተዋለን።"[17]**

**አብዱል-ባሃም እንዲህ ይመክረናል፡-**

**"...አትረፉ፣ ምንም ዕርጋታ አትፈልጉ፣ ራሳችሁን ከዚህ በቅጽበት አላፊ ከሆነው ዓለም የቅንጦት ነገሮች ጋር አታጣብቁ፣ ራሳችሁን ከእያንደንዱ ቁራኛነት ነፃ አውጡ፣ በአምላክ መንግሥት ውስጥ ሙሉ በሙሉ የተደላደላችሁ ለመሆን በሙሉ ልባችሁና በሙሉ ነፍሳችሁ ጥረት አድርጉ። የመንግሥተ ሰማይን የከበሩ ሀብቶች ተቀዳጁ። ዕለት በዕለት ይበልጥ የምታንፀባርቁ ሁኑ። ወደ አንድነት ደጀሰላም ያለማቋረጥ ይበልጥ እየቀረባችሁ ሂዱ።"[18]**

ግባችንን ለማሳካት፣ ጥረት ማድረግ እንዳለብን ሁላችንም እናምናለን። ነገርግን ይህ ቀላል እምነት በተግባር ልንዘነጋው የማይገባ የተወሰነ እንደምታዎች አሉት። አንድም፣ በሚያስፈልገው የጉልበት መጠን እና በግቡ ወይም እየተሠራ ባለው ሥራ የክብደት ደረጃ መካከል ተዛማጅነት እንዳለ ማስታወስ አስፈላጊ ነው። በቀላሉ ሊከናወን ይችላል ብለን ካሰብን ራስችንን እያታለልን ነው። ነገር ግን የሚደረገው ጥረት መጠንም ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት ብቸኛ ምክንያት/ መንሳኤ አይደለም። ቀጣይነትና ቁርጠኝነት አስፈላጊ ነው። ትኩረት ያስፈልጋል። ሥራዎችን የመፈጸም ልምድ፣ ከአንዱ

ወደ ሌላው አለመዝለል እና ሥራን ሳያጠናቅቁ አለመተው ጠቃሚ ነው። ከልብ ያልሆኑ ጥረቶች ፍሬ አይሰጡም። ሳምንታዊ የሕፃናት መንፈሳዊ ትምህርት ክፍል በምናባችሁ ሳሉ። አስተማሪው ለእያንዳንዱ ክፍል ለመዘጋጀት የተወሰኑ ሰዓቶች መስዋዕት ለማድረግ፣ ተማሪዎቹ የትምህርቱን ይዘት እንዲገነዘቡ ለመርዳት በቆይታው ውስጥ ሙሉበሙሉ ትኩረት መስጠት፣ ወደ ወጣቶቹ ወላጆች ቋሚ ጉብኝቶች ማድረግ፣ የእያንዳንዳቸውን ዕድገት ከሳምንት እስከ ሳምንት መከታተል አለበት። አስተማሪው አልፎ አልፎ የሚዘጋጅ፣ ሲሰለች ክፍለ ጊዜውን ገና ከጅምሩና በፍጥነት የሚቋጭ፣ እንዲሁም ስለእያንዳንዱ ሕፃን ለማሰብ እና ዕድገቱን ወይም ዕድገቷን ከወላጆች ጋር ለመወያየት አስፈላጊውን ግዜ መስዋዕት ለማድረግ የሚሳነው ከሆነ፣ የክፍሉ ዕጣ-ፈንታ ምንድን ነው? አስተማሪው አንዳንድ ሌላ መካፈል ያለበት አስገዳጅ ጉዳይ ማለትም ከከተማ ውጭ የሆነ ጓደኛ ለጉብኝት ሲመጣ አብሮ ለመሆን ሲፈልግ ትምህርቱን በቀላሉ የሚሰርዘው ቢሆንስ?

እነዚህ ጥቂት ሃሳቦች እያንዳንዱ የምናከናውነው ሥራ የሚጠይቀውን ሁለቱንም የጥረት መጠን እና ጥራት ትኩረት መስጠት እንዳለብን የሚያሳምኑን ናቸው። ይህ ለምንሰማራበት የአገልግሎት ተግባሮች ብቻ የሚሆን አይደለም፤ ይልቁንም ለገዛ ራሳችን ዕድገትም በዕኩል ያገለግላል። በዚህ ተከታታይ መጽሐፍ የመጀመሪያው ውስጥ የተመለከትናቸው መንፈሳዊ ልምዶችም ቢሆኑ፤ ማለትም ዘወትር መጸለይ፣ ቅዱሳን ጽሑፎችን በየዕለቱ ማንበብ፣ ሕይወቶቻችን ከትምህርቶቹ ጋር እንዴት እንደምናጣጥም ለማሰላሰል፣ በጸሎተ ሱታፌዎች በሙሉ ልብ ለመሳተፍ - ቀጣይነት ባለው ጥረት ላይ ይመረኮዛሉ። ከሥር ያሉት ከጥረት ጋር የተያያዙ በዛ ያሉ ገለፃዎች ናቸው። የትኞቹ እውነት እንደሆኑ መወሰን በዚህ ጉዳይ ላይ የበለጠ ለማሰላሰል ይረዳችኋል፦

_____ ብልህ ከሆንክ ጠንክረህ መሥራት አይስፈልግህም።

_____ ለምን ዙሪያ ጥምጥም ትሄዳለህ፤ ሁሌም አቋራጭ መንገድ ተመልከት።

_____ እስኪያልፍ ያለፋል።

_____ ትልቅ ህልም ይኑርህ፤ ምኞቶችህ እውን ይሆናሉ።

_____ ሽልማቱ ትልቅ የሆነ፣ ጥረቱም የዚያኑ ያህል ነው።

_____ ጥረቱ ከፍ ሲል፣ ሽልማቱም የበለጠ ጣፋጭ ነው።

_____ በመጀመሪያው ካልተሳካልህ፣ ደግመህ፣ደጋግመህ ሞክር።

_____ ሌሎች ላንተ እንዲሠሩልህ ማድረግ ከቻልክ ለምን ትሠራለህ?

_____ በጣም ብዙ ጥረት የሚጠይቅ ከሆነ፣ የሚሆን አይደለም ማለት ነው።

_____ ትናንሽ እርምጃዎች - ቀጣይና ወጥ ከሆኑ - ረጅም መንገድ መጓዝ ይቻላል።

_____ ዋጋ ያለው ምንም ነገር በቀላሉ የሚመጣ የለም።

_____ ልቀት በሙሉ ልብ መሰጠትን ይጠይቃል።

_____ የአንድ ሺህ ማይሎች ጉዞ በአንድ እርምጃ ይጀምራል።

_____ ፍፃሜ ላይ መድረስ ብቻ በራሱ በቂ አይደለም።

_____ ነገሮች እንዲከሰቱ መጠበቅ የለብንም፤ ይልቁንም ልንከታተላቸው ይገባል።

_____ ስኬት የዕድል ጉዳይ ነው።

_____ ሁለት እጥፍ ዓላማችንን በአስማት ልናሳካ አንችልም።

_____ ራሳችንን በየዕለቱ መቆጣጠር አለብን።

የገዛ ራሳችንን መንፈሳዊና አዕምሮአዊ ዕድገት ለመጎናጸፍ እና ለኅብረተሰብ ለውጥ የበኩላችንን ለማበርከት በመጣር የአገልግሎት ጎዳናን እንጓዛለን። የዚህ ሁለት እጥፍ ዓላማ ተግባር ከእኛ በኩል ትልቅ ጥረት እንደሚፈልግ ግልጽ ነው። ባሃኦላህ እንዲህ ይነግረናል፦

**"ወደር የሌለው ፈጣሪ ሁሉንም ሰዎች ከአንድ ዓይነት ነገር ፈጠራቸው፣ እውነታቸውንም ከቀሩት ፍጡሮቹ በላይ ከፍ አደረገው። ስለዚህ፣ ስኬታማነት ወይም ውድቀት፣ ማትረፍ ወይም ክስረት በሰው በራሱ ጥረቶች ላይ የተመሠረቱ መሆን አለባቸው። እርሱ የበለጠ ሲጥር፣ ዕድገቱም የበለጠ ይሆናል።"[19]**

የላይኛውን ምንባብ እስካሁን በቃላችሁ ይዛችሁ ካልሆነ፣ ለመያዝ ትፈልጉ ይሆናል።

## ምዕራፍ 9

ከአገልግሎት ደስታን ማግኘት እንድንችል በራሳችን ውስጥ የተወሰኑ አመለካከቶችን ማዳበር ይገባናል። ለምሳሌ፣ አምላክ ላጎናጸፈን የአገልግሎት ፀጋ አመስጋኞች መሆን አለብን፤ የእርሱን እምነት ስናገለግል ለአምላክ ውለታ እየዋልን እንደሆነ አድርጎ ማሰብ የማይታሰብ ነው። ጨለምተኛ አስተሳሰብን ማስወገድ መማር ሕይወትንም በጎን በመጠበቅ አመለካከት መቅረብ አለብን። በፈተናዎች መካከል ሆነንም፣ መጪውን በእምነት ተስፋ እንመለከታለን። ተከታዮቹ የአብዱል-ባሃ ቃላት ጥረቶቻችን ሊገለጹበት የሚገባቸውን ተስፋና በጎን የመጠበቅ አመለካከት ያሳያሉ፦

**"ሲጀመር፣ ዘሩ እንዴት አነስተኛ ነው፣ ሆኖም በስተመጨረሻ ግዙፍ ዛፍ ነው። ዘሩን አትመልከቱ፣ ይልቁንም ዛፉን፣ እና አበባዎቹን፣ ቅጠሎቹን እንዲሁም ፍሬዎቹን ተመልከቱ።"[20]**

**"ስለዚህ የዚህችን ቅንጣት ዘር ወሳኝ አንደምታ ያ እውነተኛው ባለቤት በምህረት እጆቹ፣ የጌታ የታረሱ መስኮች ውስጥ እንደዘራት፣ በሥጦታዎቹና ፀጋዎቹ ዝናብ እንዳጠጣት አሁን ደግሞ በእውነት ፀሐይ የቀኑ ኮከብ ሙቀትና ብርሃን እንደተንከባከባት እወቁ።"[21]**

**"የሚበቅልና የሚያድግ ዛፍ ስትመለከቱ፣ ስለውጤቱ ባለሙሉ ተስፋ ሁኑ። በመጨረሻ ያብባል ፍሬም ይሰጣል። ደረቅ እንጨት ወይም ያረጁ ዛፎች ካያችሁ፣ ፍሬ የመስጠት ምንም ዓይነት ተስፋ የለውም።"[22]**

**"የአምላክ ተወዳጆች ደከመኝ ሳይሉ ይህን የተስፋ ዛፍ በጥረታቸው ውሃዎች መንከባከብና መመገብ እንዲሁም ማሳደግ አለባቸው።"[23]**

**"ልብ አምላክ ከሚሰጣት ቡራኬዎች ከዞረች ደስተኝነትን እንዴት ተስፋ ልታደርግ ትችላለች? ተስፋዋንና እምነት ማሳደሯን በአምላክ ምህረት ላይ ካላኖረች፣ ዕረፍት ከየት ልታገኝ ትችላለች?"[24]**

በላይኞቹ ምንባቦች ላይ ለማሰላሰል የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች አሟሉ፡-

1. ሲጀመር፣ ዘሩ እንዴት አነስተኛ ነው፣ ሆኖም በስተመጨረሻ ______________________________ ______________________________________________________::

2. ቅንጣትዋን ዘር መመልከት የለብንም፣ ይልቁንም ________________________________________ ____________________________________________________________________::

3. ስለዚህ የዚህችን ቅንጣት ዘር ወሳኝ አንደምታ አምላክ በምህረት እጆቹ፣ __________________ ____________________________________________________________________ ____________________________________________________________________ ____________________________________________________________________ _____________________________________________________________ልናውቅ ይገባል::

4. የሚበቅልና የሚያድግ ዛፍ ስንመለከት፣________________________________________________ _____________________________________________________________ ልንሆን ይገባል::

5. የሚበቅልና የሚያድግ ዛፍ ስንመለከት፣ ______________________________________________ ____________________________________________________ ባለሙሉ ተስፋ ልንሆን ይገባል::

6. በጥረታችን ውሃዎች፣____________________________________________________________ _______________________________________________________________________ይገባናል::

7. ልብ አምላክ ከሚሰጣት ቡራኬዎች ከዞረች ________________________________________ _____________________________________________________?

8. ልብ ተስፋዋንና እምነት ማሳደሯን በአምላክ ምህረት ላይ ካላኖረች፣ ________________________ ____________________________________________________________________ ?

አሁን፣ ለትንሽ ጊዜ አሰላስሉ፦ ደስተኛና በተስፋ የተሞላ መንፈሳችን ትህትና ከተላበሰ የምስጋና ሁኔታ ጋር ለሌሎች የደስታ ምንጭ ነው በሚለው ላይ ትስማማላችሁ? በመሆኑም፣ እምነቱን ለማገልገል ስንነሳ የአዲስ ቀን ንጋት፣ የሰው ዘር መሰባሰብያ ቀንን አስደሳች ዜናዎችን እንደተሸከምን ሁሌም በአዕምሮአችን እንያዝ:: የባሃኡላህ ቃላት በልባችን እንዲያስተጋባ ፈቃዱ ይሁን፦

"እነዚያ የሚከውኑ ደስተኞች ናቸው፤ እነዚያ የሚገነዘቡ ደስተኞች ናቸው፤ በሰማያት ውስጥ ካሉት ሁሉ በምድርም ላይ ካሉት ሁሉ የተላቀቀ፣ ከእውነቱም ጋር የሙጥኝ ያለ ሰው ደስተኛ ነው::"[25]

## ማጣቀሻዎች


1. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 1983፣2017 ኅትመት)፣ 153፣አንቀጽ 5፣ ገጽ 369፡፡

2. ዝኒ ከማሁ፣ 132፣ አንቀጽ 3፣ ገጽ 326፡፡

3. ባሃኦላህ፣ *ኀቡዓተ ቃላት* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2003፣ 2012 ኅትመት)፣ ዓረብኛው ቁጥር 2፣ ገጽ 3፡፡

4. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣* 106፣አንቀጽ 1፣ ገጽ 241፡፡

5. ዝኒ ከማሁ፣ 109፣ አንቀጽ 2፣ ገጽ 243፡፡

6. *ባሃኦላህ፣ስለ ሴቶች፣ ከባሃኦላህ ጽሑፎች፣ ከአብዱል-ባሃ፣ ከሾጊ ኤፌንዲ እና ከአለም ዓቀፍ ቤት-ፍትህ የተውጣጡ፣ በአለም ዓቀፍ ቤት-ፍትህ የጥናት ምርምር ክፍል የተጠናቀረ* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 1986፣1997 ኅትመት)፣ ቁጥር 53፣ገጽ 26፡፡

7. *ኀቡዓተ ቃላት፣* ዓረብኛው ቁጥር 11፣ ገጽ 6፡፡

8. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣* 153፣አንቀጽ 5፣ ገጽ 370፡፡

9. ዝኒ ከማሁ፣ 129፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 316፡፡

10. ዝኒ ከማሁ፣ 43፣ አንቀጽ 9፣ ገጽ 109፡፡

11. በ 19 ኖቬምበር 1911 ከተደረገ ንግግር፣ *በፓሪስ የተደረጉ ንግግሮች ውስጥ የታተመ፡- በ 1911 በአብዱል—ባሃ የተደረጉ ንግግሮች* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2006፣ 2016 ኅትመት)፣ ቁጥር 32.2፣ ገጽ 121፡፡

12. *ኀቡዓተ ቃላት፣* ፋርስኛው ቁጥር 12፣ ገጽ 26፡፡

13. ዝኒ ከማሁ፣ ፋርስኛው ቁጥር 14፣ ገጽ 26፡፡

14. ዝኒ ከማሁ፣ ዓረብኛው ቁጥር 15፣ ገጽ 7፡፡

15. ዝኒ ከማሁ፣ ፋርስኛው ቁጥር 32፣ ገጽ 33፡፡

16. ባሃኦላህ፣ *በባሃኢ ዓለም ጥራዝ አንድ፣1925—1926* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 1926፣ 1980 ኅትመት)፣ ገጽ 42፡፡

17. *የመለኮታዊ ተወዳጅ ጥሪ /The Call of the Divine Beloved/፡- ከባሃኦላህ መንፈሳዊ ተመስጦ ሥራዎች ውስጥ የተመረጡ* /Selected Mystical Works of Baha'u'llah/ (ሃይፋ፡- ባሃኢ ዓለም ማዕከል፣ 2018)፣ ቁጥር 2.12፣ ገጽ 17።

18. *የመለኮታዊ ዕቅድ ፅላቶች፡- በአብዱል-ባሃ ለሰሜን አሜሪካ ባሃኢዎች የተገለጹት* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 1993፣ 2006 ኅትመት)፣ ቁጥር 13.6፣ ገጽ 95-96።

19. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት*፣34፣አንቀጽ 8፣ ገጽ 91።

20. *ከአብዱል-ባሃ ጽሑፎች የተመረጡ* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2010፣2015 ኅትመት)፣ ቁጥር 40.3፣ ገጽ 118-19።

21. ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 40.3፣ ገጽ 119።

22. በ 11 ሜይ 1912 ከተደረገ ንግግር፣ በ*ሁለንተናዊ የሠላም ማስፋፋት ውስጥ የታተመ፡- በ 1912፣አብዱል-ባሃ አሜሪካንና ካናዳን በጎበኘበት ወቅት በእርሱ የተደረጉ ንግግሮች* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2012)፣ አንቀጽ 2፣ ገጽ 153።

23. *ከአብዱል-ባሃ ጽሑፎች የተመረጡ*፣ ቁጥር 206.13፣ ገጽ 356-57።

24. በ 21 ኖቬምበር 1911 በአብዱል-ባሃ ከተደረገ ንግግር፣ በ*ፓሪስ ንግግሮች* ውስጥ የታተመ፣ ቁጥር 34.8፣ ገጽ 133።

25. ባሃኦላህ፣ *ይድረስ ለተኩላው ልጅ* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 1988፣2016)፣ ገጽ 139።



# አነቃቂ ጭውውቶች

**ዓላማ**

መንፈሳዊ መርሆዎችን በጭውውት
ውስጥ የማካተት ችሎታ ለማዳበር

## ምዕራፍ 1

በዚህ መጽሐፍ አንደኛ ክፍል ውስጥ፣ የአምላክን ቃል ከሌሎች ጋር በመካፈል ተግባር ስለምናገኘው ሊለካ የማይችል ደስታ ተነጋግረናል። የአገልግሎት ጎዳናን ስንጓዝ፣ ከባሃኦላህ ግልጸት የምንቀስመውን ጥልቅ ዕይታዎች ከወዳጆችና ከምናውቃቸው ጋር ለመወያየት በዛ ያሉ ዕድሎች ይገኛሉ። ስለዚህ፣ ሁላችንም ልናጎለብት የሚያስፈልገን እጅግ ጠቃሚ ችሎታዎች መካከል፣ እነዚያ ትርጉም አዘልና አነቃቂ ጭውውቶች/ንግግሮች ላይ የበኩላችንን አስተዋፅዖ ለማበርከት የሚያስችሉን ናቸው። የዚህ ክፍልና የሚቀጥለው ዓላማ በዚህ ረገድ እናንተን ለማገዝ ነው። እዚህ ሁኔታዎች ሲፈቅዱ፣ መንፈሳዊ መርሆዎችን በማጣቀስ የጭውውት ደረጃን እንዴት ከፍ እንደምታደርጉ ልታስቡበት ይገባል። በቀጣዩ ክፍለ ውስጥ፣ በመንደራችሁ ወይም በአጎራባች ሰፈሮች የተጋጋሉ ወይም ሕይወታማ ማኅበረሰቦችን ለመገንባት በሚደረግ ስልታዊ ጥረት እንደ አንድ አካል እንዴት በተወሰኑ ጭብጦች ላይ ቀጣይነት ያለው ጭውውቶች እንደምትቀሰቅሱና እንደምታስቀጥሉ ታጤናላችሁ።

በሚከተሉት ምዕራፎች ውስጥ የምናከናውነው በተለያዩ ርዕሶች ላይ፣ ቃል በቃል ባይሆኑም በአብዱል-ባሃ ንግግሮችና ፅላቶች ላይ ሙሉ ለሙሉ የተመረኮዙ እና እርሱ የተጠቀመባቸውን በዛ ያሉ ሐረጎችን የሚያጠቃልሉ ብዛት ያላቸው መግለጫዎችን/ንግግሮችን መመልከት ነው። እያንዳንዱን ንግግር ብዙ ግዜ ማንበብ፣ የሃሳቦች ቅደም ተከተልን መለየት፣ ከቡድናችሁ ሌሎች አባላት ጋር ተፈጥሮአዊ በሆነ መልኩ መግለጽ እስክትችሉ ድረስ ተራ በተራ ጮክ ብላችሁ መናገር ይኖርባችኋል። ይህ ልምምድ ውይይት ለማካሄድ ስትሹ የእምነቱን አስተምህሮቶች ተገቢ ሆኖ ስታገኙት ለመጠቀም በቀላሉ ለመናገር እንድትዘጋጁ ይረዳችኋል።

በዕርግጥ፣ በዚህ ክፍል ውስጥ በንግግራችሁ ውስጥ ሲሸመኑ/ሲቀናጁ በአድማጩ ላይ ጥልቅ ተፅዕኖ ያላቸውን ምንባቦች ከቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ በቃላቹ ለመያዝ ትቀጥላላችሁ፣ ምክንያቱም የሰው ልጅን ልብና ፈቃድ ዘልቆ የሚገባ ልዩ ኃይል አላቸውና። ሆኖም በጭውውት ውስጥ ከቅዱሳን ጽሑፎች በቀጥታ መጥቀስ ጥበብ ይፈልጋል። አስፈላጊ የሚሆነው ልከኝነት፣ ይኸውም የእምነቱን አስተምህሮቶች ለመግለጽ በቀጥታ ከመጥቀስ እና የራስን አባባል በመጠቀም መካከል ሚዛናዊነት ነው። ይህን ሚዛናዊነት ለማሳካት ቅዱሳን ጽሑፎችን ለማጥናት እና አስተሳሰባችሁንና ስሜታችሁን እንዲቀርጹ በመፍቀድ ብዙ ግዜያችሁንና ጉልበታችሁን መስዋዕት ማድረግ ይኖርባችኋል።

## ምዕራፍ 2

እንድታጠኑ የምትጠየቁት የመጀመሪያ ምንባብ የሰው ልጅ መምህር/አስተማሪ የሚያስፈልገው መሆኑ ላይ ያተኩራል።

> ኑባሬውን ዓለም ስንመለከት የማዕድን፣ የአትክልት፣ የእንስሳት ግዛቶች አንዳቸውም ሳይቀሩ ሁሉም አስተማሪ እንደሚያስፈልጋቸው እናስተውላለን። የአትክልት ስፍራ አትክልተኛ ያስፈልገዋል። የተትረፈረፈ ምርት እንዲሰጥ መሬት ገበሬ ያስፈልገዋል። ሰው በዱር ውስጥ ብቻውን ከተተወ የእንስሳትን መንገድ ይከተላል። ከተማረ እጅግ ከፍተኛ ስኬት ላይ ሊደርስ ይችላል። በአስተማሪዎች ባይሆን ኖሮ ምንም ሥልጣኔ አይኖርም ነበር።
>
> ትምህርት ሦስት ዓይነት ነው፦ ቁሳዊ፣ሰብአዊ፣እና መንፈሳዊ። ቁሳዊ ትምህርት የአካላዊ መዳበርን የሚመለከት ነው። ሰብአዊ ትምህርት ስለ ሥልጣኔ እና ዕድገት ነው። አስተዳደር፣

የኅብረተሰብ ሥርዓት፣ የሰው ልጅ ደኅንነት፣ ንግድና ኢንደስትሪ፣ ሥነ-ጥበባትና ሳይንሶች፣ ወሳኝ ግኝቶች፣ እና ታላላቅ ክንውኖች የመሳሰሉትን ያካሂዳል። መንፈሳዊ ትምህርት ደግሞ መለኮታዊ ፍጽምናዎች መጎናጸፍን ያካትታል። በእርሱ ዕርዳታ የሰው ልጅ መንፈሳዊ ተፈጥሮ፣ ከፍ ያለው ተፈጥሮ፣ ስለሚጎለብት ይህ እውነተኛ ትምህርት ነው።

ለማደግ ከፈለገ፣ የሰው ልጅ ቁሳዊ ሰብአዊና መንፈሳዊ መምህር ስለመሆኑ ግልጽ ማረጋገጫ ያለው መምህር ያስፈልገዋል። አንድ ሰው፣ "እኔ ምሉዕ የሆነ ዕውቀት አለኝ፣በመሆኑም እንዲህ ያለው መምህር አያስፈልገኝም፣" ቢል ግልፅና የማያሻማ የሆነን ነገር እየካደ ነው። ልክ "እኔ ትምህርት አያስፈልገኝም፤ እንደራሴ አስተሳሰብና ዕውቀት እተገብራለሁ እንዲሁም ልቀትንም በገዛ ራሴ እቀዳጃለሁ" እንደሚል ህፃን ሆነ ማለት ነው።

የሰው ልጅ ሁልግዜ እንዲህ ዓይነት ፍፁም የሆነ መምህር፣ አካሉን ከመመገብና ጤንነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እንዲያጤን የሚረዳው፣ በዕውቀት፣ በፈጠራና በግኝት፣ እንዲራመድ እንዲሁም ሊያነቃቃው የሚችል፣ ከሁሉም በላይ የመንፈስ ሕይወቱ ውስጥ እስትንፋስ ሊዘራበት የሚችል መምህር ሲያስፈልጉት ቆይቷል። ማንም ተራ ሰው እነዚህን ፈታኝ ሥራዎች ሊያሳካ አይችልም። እነርሱን ለማሳካት ኃይል ያላቸው የአምላክ ክስተቶች/መልእክተኞች ብቻ ናቸው። እነዚህ ሁለንተናዊ የሰው ልጅ መምህራን በመሆን ከግዜ ወደ ግዜ በአምላክ የሚላኩ የተመረጡ ነፍሶች ናቸው።

1. በቡድናችሁ ውስጥ ምንባቡን በዛ ላለ ጊዜ አንብቡና ይዘቱን በደንብ ለመማር አንዳችሁ ከሌላችሁ ጋር ተረዳዱ። ከቀረቡት ሃስቦች ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን እርስበርስ መጠያየቅ እና ተፈጥሮአዊ በሆነና በቀላሉ ለመግለጽ መለማመድ ይኖርባችኋል።

2. ቀጥሎ፣ እዚህ ቁልጭ አድርጎ ለመናገር የተማራችሁትን ሃሳቦች እንዴት በጭውውት ውስጥ እንደሚካተቱ በቡድናችሁ ውስጥ ተወያዩበት። በግልጽ እንደሚጠበቀው በአንዴ ተነስታችሁ ለጓደኞቻችሁ/ወዳጆቻችሁ ትምህርት ሦስት ዓይነት ነው አትሏቸውም። ስለዚህ፣ የላይኞቹ ሃሳቦች ጠቃሚነታቸው የሚጎላበትን ሁኔታ ስላላቸው የግንኙነት ዓይነት ብታስቡበት ጠቃሚ ይሆናል። ምናልባት በጭውውት ውስጥ ያለው ጉዳይ የኅብረተሰብ ስነ-ምግባር/ሞራል መዝቀጥ ወይም ለዓለም መሻሻል እንዴት መሥራት እንዳለብን ነው። ከጓደኞቻችሁ/ወዳጆቻችሁ፣ ከቤተሰብ አባላት፣ እና ከምታውቋቸው ጋር በምታካሂዱት የተለያዩ ጭውውቶች ላይ አሰላስሉ። አዕምሮአቸውን ከያዛቸው ጉዳዮች መካከል፣ በዚህ ምንባብ ባሉ ሃሳቦች ዙሪያ ለጭውውት የሚጋብዙ ማናቸውም ነገሮች ይኖራሉን?

3. በጭውውቶች ውስጥ ያጠናችሁትን የሚመስሉ ርዕሶች ላይ ብዙ ግዜ ጥያቄዎች ይነሳሉ። አንድ ሰው፦ "እያወራችሁ ያላችሁት ከእነዚህ መምህራኖች መካከል አንዳንዶቹ እነማን ናቸው?" ብሎ ቢጠይቅ መልሳችሁ ምን ይሆናል?

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

4. ከሥር ለሰው ዘር የመምህር/የአስተማሪ አስፈላጊነት ጋር የተያያዙ ከባሃኦላህ ቅዱሳን ጽሑፎች የተውጣጡ ጥቂት ጥቅሶች ናቸው። በእነርሱ ላይ አሰላስሉ እንዲሁም ቢያንስ አንድ በቃል ያዙ። በዚህ መንገድ፣ ከቅዱሳን ጽሑፎች ምንባቦች ተገቢ በሆነ ወቅት በንግግራችሁ ውስጥ ልታቀናጁ ትችላላችሁ።

**"ሰዎች ሁሉ የተፈጠሩት የለማቋረጥ እያደገ የሚሄደውን ሥልጣኔ ወደፊት ለማራመድ ነው።"[1]**

**"አንዱ እውነተኛው አምላክ፣ ክብሩ ይስፋና፣ እራሱን ለሰዎች የመግለጹ ዓላማ እነዚያን በራሳቸው ውስጥ በሚገኘው እውነተኛና ጥልቅ ማዕድን ውስጥ ተደብቀው የሚገኙትን ዕንቁዎች ለሰዎች ገልጾ ለማሳየት ነው።"[2]**

**"አምላክ የእርሱን ነቢያት ወደ ሰዎች በሚልክበት ግዜ ዓላማው ሁለት ዕጥፍ ነው። የመጀመሪያው የሰዎችን ልጆች ካለማወቅ ጨለማ ነፃ ለመውጣት፣ እና ወደ እውነተኛው የመገንዘብ ብርሃን ለመምራት ነው። ሁለተኛው የሰውን ዘር ሰላምና መረጋጋት ለማረጋገጥና ሊመሠረቱ የሚችሉበትንም ማናቸውንም ነገሮች ሁሉ ለመስጠት ነው።"[3]**

**"ሰዎች በሁሉ ግዜያትና በሁሉም ሁኔታዎች የሚመክራቸው፣ የሚመራቸው፣ የሚያሰለጥናቸውና የሚያስተምራቸው ያስፈልጋቸዋል።"[4]**

## ምዕራፍ 3

የሚከተሉት አንቀጾች አምላክ በክስተቶቹ አማካኝነት ብቻ እንዴት ሊታወቅ እንደሚችል እና ከጓደኞቻችሁ/ከወዳጆቻችሁ ጋር ለምታደርጓቸው ጭውውቶች ጠቃሚ መሆናቸውን ይገልፃሉ።

ወሰን የሌለውን አፅናፍ ዓለም አስተዉሉ። ያለ አንድ ፈጣሪ ሊፈጠር የሚችልበት ሁኔታ ይኖራልን? ወይም የፈጣሪ እውነታ በዚያ እርሱ በፈጠረው ሊታወቅ ይችላልን? መላውን ፍጥረት ከተመለከትን፣ ከበታች ያለ ማንኛውም ነገር ከበላዩ ያለውን ኃይል ለመገንዘብ አይችልም። ስለዚህ ድንጋይና ዛፍ፣ ምንም ያክል ቢያድጉ/ቢለወጡ፣ የማየትንና የመስማትን ኃይሎች ፈፅሞ ሊያስቡት አይችሉም። እንስሳት የሰውን ልጅ እውነታ ሊገነዘቡ እንዲሁም የሰውን መንፈስ ኃይሎች ሊያውቁ አይችሉም። ስለዚህ እንዴት እኛ ፍጡር ሆነን የፈጣሪያችንን እውነታ ልንገነዘብ እንችላለን?

የመረዳት ችሎታችን አምላክ ዘንድ ሊደርስ ፈፅሞ ባይችልም፣ እርሱን ማወቅ ግን አልተነፈግንም። ከግዜ ወደ ግዜ የአምላክ ክስተት የሆነ አንድ ልዩ ስብዕና በምድር ላይ ይታያል። በአንድ በተወለወለ፣ ንጹህ መስታወት ውስጥ የፀሐይ ጭረሮች እንደሚታዩ ሁሉ፣ የአምላክ የሆኑት ሁሉም ፍጹምና፣ በረከት፣ እና ግርማ በእነዚህ ቅዱሳን ክስተቶች/ ግልፀቶች ውስጥ ይታያሉ። መስታወቱ ፀሐይን ያንፀባርቃል ማለት ፀሐይ ካለችበት ከፍታዎቿ ወርዳ መስታወቱ ውስጥ ተካታለች ማለት አይደለም። በተመሳሳይ መልኩ፣ አምላክም ከቅድስና መንግሥተ ሰማይ ወደዚህ ምድራዊ ሕይወት አይወርድም። ለማለት የተፈለገው ይህ ነው፦ የሰው ልጅ ስለ አምላክ ስሞች እና ባሕርያት እንዲሁም ፍፁምነቶች የሚያውቀው፣ የሚማረው፣ እና የሚረዳው ሁሉ የእርሱን ቅዱስ ክስተቶች ያመላክታሉ።

1. ይህን ምንባብ በቡድናችሁ ውስጥ ለተደጋጋሚ ጊዜያት ካነበባችሁ እና ስለ ይዘቱ እርስበርስ የሚነሱትን ጥያቄዎችን ከመለሳችሁ በኋላ፣ ሃሳቦቹን ቀለል ባለ መልኩ መናገር መለማመድ ይኖርባችኋል።

2. አሁን፣ እዚህ የተማራችኋቸውን ሃሳቦች ወደ ተፈጥሮአዊ ጭውውት እንዴት መለወጥ እንደምትችሏቸው በቡድናችሁ ውስጥ ተወያዩበት። ይህ ለምሳሌ፣ ስለ ፈጣሪ መኖር ወይም ስለ ሕይወት ዓላማ በሚነሳ ውይይት ውስጥ በቀላሉ ሊተገበር ይችላል። እነዚህን ሃሳቦች ከቤተሰቦቻችሁና ወዳጆቻችሁ ጋር በሚነሱ ጭውውቶች ውስጥ ለመካፈል አጋጣሚውን የሚሰጧችሁ አንዳንድ የተለዩ ርዕሶችና ጥያቄዎች ምንድን ናቸው?

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

3. ለምሳሌ፣ ከጓደኞችሁ ጋር በሚደረግ ጭውውት ውስጥ፣ ልክ ያጠናችሁትን ሃሳብ የማስተዋወቅ ዕድል አገኛችሁ እንበል። ከእነርሱ ውስጥ አንዱ ተከታዩን ጥያቄ፦ "በክስተቶቹ አማካይነት ስለ አምላክ የምናውቀው አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው?" ብሎ ቢጠይቃችሁ እንዴት ምላሽ ትሰጣላችሁ?

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

4. በዚህ ርዕስ ላይ ከወዳጆቻችሁ ጋር በምትነጋገሩበት ወቅት ልትጠቅሷቸው ትችሉ ዘንድ ከባሃኦላህ ቅዱሳን ጽሑፎች የሚከተሉትን ምንንባቦች አንድ ወይም ከዚያ በላይ በቃላችሁ ለመያዝ ትፈልጉ ይሆናል፦

**"የእርሱ የሁሉ ነገሮች ምንጭ የሆነው ዕውቀት፣ ወደ እርሱም መድረስ፣ በእነዚህ ከእውነቱ ፀሐይ በሚወጡት አንፀባራቂ ሕልውናዎች ዕውቀትና ወደ እነርሱም በመቅረብ አማካይነት በቀር በሌላ በምንም ዓይነት አይቻልም።"[5]**

**"የክስተቱ ስብዕና ምንጊዜም የአምላክ ወኪልና አፈቀላጤ ነበር። እርሱ፣ በእውነቱ፣ የአምላክ ፍፁም የላቁ ስያሜዎች የቀን ምንጭ፣ የተከበሩ ባሕርያቱም የንጋት ቦታ ነው።"[6]**

**"ከዚህም በላይ፣ የእነዚህ የአምላክ ክስተቶች፣ አንዳቸውም ሳይቀሩ የሁላቸው ሥራዎችና ተግባሮች፣ እንዲያውም ማንኛውም ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ያለው፣ እንዲሁም ማንኛውም እነርሱ ወደፊት የሚገልጹት፣ ሁሉም በአምላክ የታዘዙ፣ የፈቃዱና የዓላማውም ነፀብራቅ ስለመሆናቸው፣ ዕርግጠኞች ሁኑ።"[7]**

## ምዕራፍ 4

የሃይማኖት አንድነት ብዙዎች የሚፈልጉት ርዕስ ነው፣ ተከታዮቹ ሃሳቦችም በዛ ባሉ አጋጣሚዎች ሊያግዟችሁ ይችላሉ፦

ከምንም ዓይነት ኩራዝ ቢበራ የብርሃን አፍቃሪ መሆን አለብን። በየትኛውም የአትክልት ሥፍራ ቢያብብ የፅጌሬዳ አፍቃሪዎች መሆን አለብን። ከማንኛውም ምንጭ ቢመጣ የእውነት ፈላጊዎች መሆን አለብን። ከአንድ ኩራዝ ጋር መቆራኘት ብርሃኑ በሌላ ውስጥ ሲንፀባረቅ ከማስተዋል ሊያግደን ይችላል። እውነትን ስንፈልግ፣ እራሳችንን ቀድሞ ካዳበርናቸው ከግትር አመለካከቶች ማላቀቅ እና ከንቱ ጥላቻችንን መግታት ይኖርብናል። ፅዋችን በእኔነት ከሞላ፣ ለሕይወት ውሃ ምንም ቦታ በውስጡ አይኖረውም።

ሃይማኖት የዓለም ብርሃን ነው። እርምጃዎቻችንን ይመራል የማያቋርጥ የደስታ በሮችንም ይከፍትልናል። ከቀኖናዊ እምነቶችና ጭፍን ቅዢ ገደቦች ነፃ ሆነን የሁሉንም ታላላቅ ሃይማኖቶች አስተምህሮቶች ስንመረምር፣ በአንድ መሠረት ላይ እንዳረፉ መሆናቸውን መገንዘብ እንጀምራለን። ሁላቸውም የአምላክን ዕውቀት ይገልፃሉ። የሰው ዘርን ዓለም ዕመርታ ይሻሉ።

በዕርግጥ ግዜውና ቦታው በሚፈልጓቸው መጠን በእያንዳንዱ ሃይማኖት የተሰጡት ማኅበራዊ ሕጎችና ደንቦች መካከል ልዩነቶች አሉ። ነገር ግን በውስጣዊ ሕልውናቸው ሁሉም ሃይማኖቶች አንድ ናቸው። እነርሱ እምነት፣ ዕውቀት፣ ዕርግጠኝነት፣ ፍትሕ፣ ቅድስና፣ አርቆ አሳቢነት፣እምነት የሚጣልበት፣ የአምላክ ፍቅር፣ እና ለጋስነትን ያበለፅጋሉ። ንጽህናን፣ መላቀቅን፣ ትህትናን፣ መቻቻልን፣ ትዕግስትን፣ እና ዕርጋታን ያስተምራሉ። እነዚህ የሰው መልካም ባህርያት በእያንዳንዱ የግልፀት ዘመን ይታደሳሉ።

እንዳለመታደል ሆኖ፣ በከንቱ ጥላቻዎችና ጭፍን ቅዢዎች ምክንያት፣ ብዙዎች የሃይማኖት መሠረታዊ አንድነትን ሊያስተውሉ አልቻሉም። ለሰው ዘር የአምላክ መመሪያ እውነት ነው፣ እውነትም ክፍፍሎች የላትም፤ እሷ አንድ ናት። ቀድሞ ያዳበርናቸውን ግትር ሃሳቦች ወደጎን

ትተን እውነትን በራሳችን ለራሳችን ብንመረምር፣ ፍለጋችን ወደ አንድነት ይመራናል። ሃይማኖት አንድ ሊያደርገን ይገባል፤ በሰዎች መካከል የፍቅር ቁርኝት መመሥረት አለበት። የጠላትነትና የፀብ ምክንያት ከሆነ፣ ያለመኖሩ ይመረጣል።

1. እንደቀደመው ምዕራፍ፣ ይህን ምንባብ በዛ ላለ ጊዜ በቡድናችሁ ውስጥ ልታነቡት ይገባል፣ ከሃሳቦቹ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን አንዳችሁ ሌላችሁን ጠይቁ፣ ከዚያም በደንብ እንድትገል ጿቸው ተለማመዱ።

2. እስካሁን ያጠናችሁትን ሃሳቦች ወደ አንድ ጭውውት እንዴት ልትሸምኑት እንደምትችሉ፣ ለምሳሌ በሰዎች አዕምሮዎች ላይ ብዙ ጊዜ ስላለ ሃይማኖታዊ ግጭት በቡድናችሁ ውስጥ ትኩረት ስጡ። ከዚያ ባሻገር እውነትን የመመርመር አስፈላጊነት የሚወያዩ እንጂ በቅስቀሳ /ፕሮፓጋንዳ መጠምዘዝ የማይፈልጉ ብዙ ወዳጆች መሃል እራሳችሁን ልታገኙ ትችላላችሁ። ከቅርብ ግዜ ወዲህ ከጓደኞቻችሁ እና ከጎረቤቶቻችሁ፣ ከሥራ ባልደረቦቻችሁ እና ከሚታው ቋቸው ሰዎች ጋር ስላደረጋችሁት ውይይት እንደገና መለስ ብላችሁ አስቡ። በእነዚህ ሃሳቦች ዙሪያ ከተደረጉ ጭውውቶች አዕምሮአቸው ሊጠቀሚባቸው የሚችላቸው አንዳንድ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

______________________________________________________

______________________________________________________

______________________________________________________

______________________________________________________

______________________________________________________

______________________________________________________

3. ከላይ ያሉትን ሃሳቦች በጭውውታችሁ ውስጥ ካካፈላችሁ በኋላ፣ አንድ ሰው፣ "በሁሉም ሃይማኖቶች ውስጥ የጋራ የሆኑ አንዳንድ እውነቶች ምንድን ናቸው?" ብሎ ቢጠይቃችሁ እንዴት ብላችሁ ትመልሳላችሁ?

______________________________________________________

______________________________________________________

______________________________________________________

______________________________________________________

4. ከባሃኦላህ ቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ የተወሰዱትን የሚከተሉት ምንባቦች አንድ ወይም ሁለቱን በቃላችሁ እንድትይዙ ሃሳብ ቀርቧል፦

**"የዓለም ሕዝቦች፣ ከማናቸውም ዘር ሆነ ሃይማኖት ቢሆኑ፣ የመንፈስ መነቃቃታቸውን የሚያገኙት፣ ከአንድ መንግሥተ ሰማያዊ ምንጭ እንደሆነ፣ የአንድ አምላክም ተገዢዎች ለመሆናቸው ምንም ዓይነት ጥርጥር ሊኖር አይችልም።"[8]**

**"ከሁሉም ሃይማኖቶች ተከታዮች ጋር በጓደኝነትና በወዳጅነት መንፈስ ተቀላቀሉ።"[9]**

**"የአምላክን እምነትና የእርሱን ሃይማኖት የሚያንቀሳቅሰው ኃይል መሠረታዊ ዓላማ የሰውን ዘር ፍላጎቶች ለመጠበቅና አንድነቱንም ለማራመድ ነው።"[10]**

**"የአምላክ ሃይማኖት ለፍቅርና ለአንድነት ነው፤ የጠላትነትና የመቃቃር ምክንያት አታድርጉት።"[11]**

## ምዕራፍ 5

በሳይንስ እና ሃይማኖት መካከል ያለ ግንኙነት ቀጥሎ እንድታጠኑ የምትጠየቁት ርዕስ ነው።

ሃይማኖት ከሳይንስ ጋር ስምም ሊሆን ይገባል። እውነት የሆነውን መረዳት እንድንችል አምላክ ምክንያታዊ መሆንን አጎናጽፎናል። ሳይንስ እና ሃይማኖት ሁለቱም ምክንያታዊ የመሆን መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ይጠበቃሉ። ስለዚህ፣ እርስበርስ ስምም ሊሆኑ ይገባል። የሰው አዕምሮ ኃይል ወደ ላቀ ከፍታዎች እንዲመጥቁ የሚያስችሉ ሁለት ክንፎች፣ የሰው ልጅ ሊበር የሚችልባቸው ሁለቱ ክንፎች ናቸው። አንድ ክንፍ በቂ አይደለም።

ሳይንስ የአምላክ ሥጦታ ነው። የቁሳዊውን ዓለም ሕጎች ያገኘል እንዲሁም ተፈጥሮ በእኛ ላይ የጫነችብንን ገደቦች እንድናሸንፍ ያስችለናል። በሳይንሳዊ መሣሪያዎች ዕገዛ፣ ለዓይን የማይታዩ ነገሮችን እንመለከታለን ፤ በሰፊው ርቀቶች መካከል በቅጽበት እንገናኛለን። ሳይንስ የአሁኑንና ያለፈውን ያዋህዳል የወደፊቱንም ምስጢሮች ዘልቆ ያያል። የአንድ ሕዝብ ዕድገት በሳይንሳዊ ስኬቶች ላይ የተመሠረተ ነው።

የአምላክ ሃይማኖት የእውነት አራማጅ፣ የዕውቀት ደጋፊ፣ እና የሰው ዘርን ሥልጣኔ አጎናጻፊ ነው። ሳይንስ ያለ ሃይማኖት የቁስአካላዊነት ማራመጃ መሣሪያ ይሆናል፣ በሒደትም ወደ ተስፋ መቁረጥ ይመራዋል። ሃይማኖት ከሳይንስ ጋር ሲቃረን ግልጽ ከንቱ አምልኮ ይሆናል። ሃይማኖትና ሳይንስ ተጣጥመው በጋራ ከሄዱ፣ አሁን ለሰው ዘር መከራን እያመጣ ያለው ጥላቻና ምሬት ማብቂያው ይሆናል።

1. እንደተለመደው፣ ምንባቡን አንቀጽ በአንቀጽ በዛ ላለ ጊዜ በቡድናችሁ ውስጥ አንብቡት፣ ከዚያም ይዘቱን በተፈጥሮአዊ መልኩ በደንብ ለመግለጽ በሚያስችል ሁኔታ እስክትችሉት ድረስ አንዳችሁ ሌላችሁን ጠይቁ።

2. ተከታዩን፦ "ሃይማኖት ያለፈ ግዜ ነገር ነው፤ ሳይንስ ሁሉንም የሰው ልጆች ችግሮች ይፈታል" ብሎ ለሚናገር አንድ ሰው እንዴት መልስ ትሰጣላችሁ? ሃይማኖት ከከንቱ አምልኮ ጋር ተመሳሳይ አይደለም፣ ነገር ግን ያለ ሳይንስ እንደዚያ ይሆናል፣ ሳይንስ ያለ ሃይማኖትም ከቁስ አካላዊነት ወደተወለደ ተስፋ መቁረጥ ያመራል የሚለውን ማብራራት ይረዳችሁ ይሆን? ይህ እንዴት እንደሚፈጠር ምሳሌዎች መስጠት ትችላላችሁ?

3. ከባሃኦላህ ቅዱሳን ጽሑፎች ከሆኑት ከሚከተሉት ምንባቦች አንድ ወይም ሁለቱን በቃላችሁ እንድትይዙ ሃሳብ ቀርቧል፦

**"ፍፁም ኃያሉ ሰውን ካጎናጸፋቸው ከእነዚህ ችሮታዎች መካከል የመጀመሪያውና ቀዳሚው፣ የመገንዘብ ሥጦታ ነው። ... ይህ ሥጦታ ሰው በሁሉም ነገሮች ውስጥ ያለውን እውነት ለማየት የሚያስችለውን ኃይል ይሰጠዋል፤ ትክክለኛ ወደሆነው ነገር ይመራዋል፣ የፍጥረትን ምስጢሮችም መርምሮ እንዲያገኝ ይረዳዋል።"[12]**

**"ዓለምን ተመልከቱና ለአንድ አፍታ አሰላስሉበት። ከአይናችሁ ፊት የገዛ ራሷን መጽሐፍ ይፋ ታደጋለች እንዲሁም የጌታችሁ ብዕር፣ የሚያበጀው፣ ሁሉን አዋቂው፣ በውስጡ የከተበውን ትገልፃለች።"[13]**

**"ዕውቀት ለሰው ሕይወት እንደ ክንፎች ነው፣ ወደ ከፍታውም መውጫ መሰላሉ ነው። እሱን መቀዳጀት በሁለም ላይ የተደነገገ ነው።"[14]**

## ምዕራፍ 6

የሰው ልጅ አንድነት በዚህ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሰዎች ልቦች ውስጥ የሚያስተጋባ ርዕስ ነው፣ እናም ከሥር የቀረቡትን ሃሳቦች መወያየት ብዙዎች በደስታ ይቀበሉታል።

ብዛት ያላቸው ቀለማትና መዓዛዎች ያላቸው አበቦች ጎን ለጎን የሚያድጉበት የአትክልት ስፍራ ለዓይን ሐሴትን ይሰጣሉ። የተለያዩ ቢሆኑም፣ እያንዳንዱ አበባ በአንድ ዓይነት ዝናብ ይታደሳሉ የአንድ ፀሐይንም ሙቀት ይቀበላሉ። ይህ ለሰው ልጅም እውነት ነው። ከብዙ ዘሮችና ቀለማት የተሠሩ ናቸው። ነገር ግን ሁሉም ከአንድ አምላክ መጥተዋል፣ ሁሉም ተመሳሳይ መነሻ አላቸው። በሰው ልጅ ቤተሰብ ውስጥ ያለው ብዝኃነት የውህደቱ ምንጭ መሆን ይገባዋል፣ ልክ በሙዚቃ ውስጥ የተለያዩ ኖታዎች በአንድነት ተዋህደው እንደሚፈጥሩት ፍፁም የሆኑ ቅንብሮች ዓይነት።

አንድነት ለህልውና አስፈላጊ ነው። ፍቅር የሕይወት ዋና መንስዔ ነው። በቁሳዊው ዓለም ውስጥ፣ የሁሉም ነገሮች ንጥረ ነገሮች በአንድ ላይ የተቆራኙት በመስህብ ሕግ ነው። የመስህብ ሕግ አንዳንድ ንጥረ ነገሮችን በውብ የአበባ መልክ አንድ ላይ ያሰባስባል። ነገር ግን ያ መስህብ ሲወሰድ፣ አበባው ይፈራርስና መኖሩን ያቆማል። በሰው ልጅም እንዲሁ ነው። መስህብ፣ ውህደት፣ እና አንድነት የሰው ልጅን በጋራ የሚያቅፉ ኃይሎች ናቸው።

ባሃኦላህ መላውን የዓለም ሕዝቦች የሚያዋሃድ ንድፍ/ዲዛይን ሠርቷል። ወደዚህ የአንድነት ክበብ ለመሳብ ማንኛውንም ጥረት ማድረግ ይገባናል። ከእኛ ከራሳችን የተለየ የዘር፣ የብሔሮች/አገሮች፣ ሃይማኖቶች እና አመለካከቶች ያላቸው ሰዎች ስናገኝ፣ እነዚህ ልዩነቶች

በመካከላችን መሰናክሎች እንዲሆኑብን መፍቀደ የለብንም። እነርሱን በሰው ልጅ ውብ የአትክልት ሥፍራ እንደሚያድጉ የተለየ ቀለም እንዳላቸው ፅጌረዳዎች ልናስባቸው እና በእነርሱም መካከል በመሆናችን ደስተኞች ልንሆን ይገባል።

1. ከዚህ ቀደም እንዳደረጋችሁት የላይኛውን ምንባብ ካጠናችሁ በኋላ፣ በዙሪያችሁ ስለሚነሱት ብዙ ጭውውቶች አስቡ። እነዚህን ሃሳቦች ለማካፈል ዕድል የሚከፍቱ በሰዎች አዕምሮዎች ውስጥ የሚመላለሱ አንዳንድ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

2. በሰው ልጅ አንድነት ላይ የሚደረግ ጭውውት በራሱ ማኅበረሰብ ውስጥ ስላለው አንድነት አስፈላጊነት ወደ ውይይት ሊያመራ ይችላል። እያንዳንዳችን ለዚህ እንዴት አስተዋፅዖ ለማበርከት እንደምንችል ጥቂት ቃላት ልትናገሩ ትችላላችሁ?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

3. በዚህ ርዕስ ላይ ከወዳጆቻችሁ ጋር ስትነጋገሩ ለማጣቀስ እንድትችሉ ከሚከተሉት ጥቅሶች አንድ ወይም ከዚያ በላይ በቃል ለመያዝ ትፈልጉ ይሆናል፦

**"የአንድነት ድንኳን ተተክሏል፤ እርስ በርሳችሁ እንደ ባዕዳን አትተያዩ። እናንተ የአንድ ዛፍ ፍሬዎች፣ የአንድ ቅርንጫፍም ቅጠሎች ናችሁ።"**[15]

**"የአንድነት ብርሃን በከፍተኛ ኃይል የተመላ ስለሆነ መላዋን ምድር ለማብራት ይችላል።"**[16]

**"ፊቶቻችሁን ወደ አንድነት መልሱ፣ የብርሃኑም ነፀብራቅ በእናንተ ላይ እንዲያበራ አድርጉ። በአንድ ላይ ተሰባሰቡ፣ ለእምላክ ብላችሁም በመካከላችሁ የፍልሚያ ምንጭ የሆነውን ማንኛውንም ነገር ነቅላችሁ በመጣል ፍቱት።"**[17]

**"ሰው ያን ወዳጅነትን፣ ደግነትንና አንድነትን የሚያራምደውን በጥብቅ መያዝ ይገባዋል።"** [18]

## ምዕራፍ 7

የሚከተለው ምንባብ ለአብዛኛው ሕዝብ ትልቅ አሳሳቢ ጉዳይ ስለሆነው የፍትሕ ርዕስ ላይ በሚደረጉ ውይይቶች አስተዋፅዖ ለማበርከት ይረዳችኋል፦

በግለሰቦች መካከል የችሎታ ልዩነት ለሰው ህልውና መሠረታዊ ነገር ነው:: ስለሆነም፣ ለሁሉም ሰው በሁሉም ረገድ ዕኩል መሆን የማይቻል ነው:: ሆኖም የሰው ልጅ ጉዳዮች፣ ሙሉ ለሙሉ፣ በፍትሕ መመሪያ መተዳደር ይኖርባቸዋል:: ፍትኅ የተቀደሰ መሆን አለበት፣ የእያንዳንዱ ሰው መብቶችም መጠበቅ አለበት::

ፍትሕ የተገደበ አይደለም፤ ሁሉን አቀፍ ባህርይ ነው:: በሁሉም የሰው ሕይወት ክፍሎች ውስጥ መተግበር አለበት:: ሁሉም የኅብረተሰብ አባል የሥልጣኔን ጥቅሞች ሊቋደስ ይገባል፣ ምክንያቱም ሁላችንም የሰው ልጅ አካል ውስጥ እንመደባለን:: የዚህ አካል አንድ አባል በጭንቀት ወይም ስቃይ ውስጥ ከሆነ፣ ሌሎች ሁሉም አባላት መሰቃየታቸው አይቀሬ ነው:: እንዴት አንዱ እየተሰቃየ ሌሎች ደግሞ በምቾት ላይ ይሆናሉ? የዛሬ ኅብረተሰብ ተፈላጊ የሆነው የጋራ ተጠቃሚነትና ተመጣጣኝነት ያጥረዋል፤ በደንብ የተደራጀ አይደለም:: መላውን የሰው ዘር ቤተሰብ ደህንነትና ደስታ የሚያረጋግጡ ሕጎችና መመሪያዎች አስፈላጊ ናቸው::

ፍትሕ በሽልማት እና ቅጣት ምሰሶዎች ላይ የተመሠረተ ነው:: እነዚያ እምነት በሌላቸው፣ የመለኮታዊ ቅጣት ፍርሃት በሌላቸው መንግሥታት የሚመሩ ኢፍትሐዊ ሕጎችን ያስፈጽማሉ:: ጭቆና እንዲወገድ ከተፈለገ ለሽልማት ተስፋ እና የቅጣት ፍርሃት ሁለቱም ያስፈልጋሉ:: ሕግ አውጪዎች እና አስፈጻሚዎች የውሳኔዎቻቸውን መንፈሳዊ ውጤቶች ሊያውቁት ይገባል:: የተግባሮቻቸው መዘዞች ከዚህ ምድራዊ ሕይወት ባሻገር እንደ ሚከተላቸው የሚያምኑ እና ፍርዶቻቸው በመለኮታዊ ፍትሕ ሚዛን እንደሚመዘኑ የሚያውቁ መሪዎች/ገዢዎች በዕርግጠኝነት ግፍና ጭቆናን ያስወግዳሉ::

1. የላይኞቹን ሃሳቦች ተፈጥሮአዊ በሆነ መልኩ መግለጽ አንዴ ከተማራችሁ በኋላ፣ ምንባቡ ከሚያቀርበው ጥልቅ ዕይታዎች ምን ዓይነት የጭውውት ርዕሶች ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ተመልከቱ::

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

2. ኢፍትሓዊነት መቼም አያበቃም ብሎ ለሚያምን አንድ ሰው እንዴት ምላሽ ትሰጣላችሁ?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

3. ከሥር ከፍትሕ ጋር የተያያዙ ጥቂት ጥቅሶች ከባሃኦላህ ቅዱሳን ጽሑፎች የተወሰዱ ናቸው በመሆኑም በቃላችሁ እንድትይዙ ትበረታታላችሁ::

**"የሰዎች ብርሃን ፍትሕ ነው። በጭቆናና በግፍ ተፃራሪ ነፍሶች አታጥፉት። የፍትኅ ዓላማ በሰዎች መካከል አንድነት መከሰት ነው።"[19]**

**"ከፍትኅ ብርሃን ጋር ምንም ብርሃን ሊወዳደር አይችልም። የዓለም አደረጃጀትና የሰው ልጅ ዕርጋታ በእርሱ ላይ የተመሠረተ ነው።"[20]**

**"ዓለምን የሚያስለጥነው ፍትኅ ነው፣ በሽልማትና በቅጣት፣ በሁለት ምሰሶዎች ተደግፎ የቆመ ነውና። እነዚህ ሁለቱ ምሰሶዎች ለዓለም የሕይወት ምንጮች ናቸው።"[21]**

## ምዕራፍ 8

በእያንዳንዱ የሚያልፍ ቀን በሀብታሞች እና በድሆች መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ ይሄዳል፣ ከሥር ያለውም ምንባብ በዚህና ተያያዥ ርዕሶች ላይ ከወዳጆች ጋር ለምታደርጉት ጭውውት ያግዛችኋል።

በዛሬ ግዜ፣ የጋራ ተጠቃሚነትና የተጣጣመ/የተዋሃደ ግንኙነቶች ባለመኖሩ ምክንያት፣ አንዳንድ የኅብረተሰብ አባላት በታላቅ ምቾትና ቅንጦት ውስጥ በመኖር የረኩ ናቸው፣ ሌሎች ደግሞ ምግብና መጠለያ ፈላጊዎች ናቸው። አንዳንዶቹ ከልክ በላይ ሀብታሞች ሲሆኑ፣ ሌሎች ደግሞ የመጨረሻው ድህነት ውስጥ ይኖራሉ።

ለጥቂቶች ከልክ በላይ የሆነ ሀብት ለማከማቸት እና ሌሎች በጣም የደኸዩ እንዲሆኑ በማያስችል ሁኔታ የኅብረተሰብ ሕጎች ሊደነገጉና ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል። ይህ ማለት ሁሉም ዕኩል መሆን አለባቸው ማለት አይደለም፣ የደረጃና ችሎታ ልዩነቶች የፍጥረት አካላት ናቸውና። አሳዛኝ የሐብት መትረፍረፍ እሱን ተከትሎም መጣጭ ቅስም ሰባሪ ድህነት ግን ሊወገድ ይችላል። ለካፒታሊስቱ የሀብት ባለቤት መሆን ትክክል ከሆነ፣ ሠራተኛው በቂ የህልውና መሠረት ሊኖረው ይገባል የሚለው ዕኩል ፍትሃዊ ነው። ከልክ ያለፈ ድህነት ስንመለከት፣ የሆነ ቦታ የጭቆና አገዛዝ እናገኛለን።

የጉዳዩ ፍሬ ነገር መለኮታዊ ፍትህ በሰዎች ሁኔታዎች ውስጥ መታየት አለበት የሚለው ነው። የመላው ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ መሠረታዊያን በተፈጥሮአቸው መለኮታዊ ናቸው ከልብና መንፈስ ዓለም ጋርም የተሳሰሩ ናቸው። ሀበታሞች የተትረፈረፋቸውን መስጠት አለባቸው፤ ልቦቻቸውን ማለስለስ እና ርኅሩኅ ህሊና ማዳበር አለባቸው። ልቦች ባንድ ላይ መቆራኘት አለባቸው፣ ሀብታሞች በሙሉ ፈቃደኝነት የኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን በዘላቂነት ለመመሥረት እርምጃ እንዲወስዱ ፍቅር በጣም የበላይ መሆን አለበት። እነርሱ ራሳቸው በማኅበረሰቡ ውስጥ ሥር የሰደደ ድህነት እያለ ትልቅ ሀብት ይዞ መገኘት ፍትሓዊም ሕጋዊም አይደለም የሚለውን መገንዘብ አለባቸው። በዚህ መንገድ፣ እነርሱን በምቾት ሊያኖራቸው የሚያስችላቸውን ያህል በመያዝ፣ ሐብታቸውን በፈቃደኝነት ይሰጣሉ።

1. ምንባቡን አንብቡትና በተለመደው መንገድ በቡድናችሁ ውስጥ አጥኑት። ከሀብትና ድህነት ጋር የሚያያዙ በሰዎች አዕምሮዎች የሚመላለሱ ብዙ ጉዳዮች -ጥቂቶቹን ለመግለጽ ቅጥር፣ ደሞዝ / ክፍያ፣ መጠለያ አሉ። ከዚህ ምንባብ ውስጥ ካሉ ሃሳቦች ውይይቶች ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚያስችሉ ሌሎች ርዕሶች ልታስቡ ትችላሁ?

2. የላይኛውን ሃሳቦች ስትጠቅሱ የሰማችሁ አንድ ሰው የሚከተለውን ቢጠይቃችሁ፦ “ሀብታሞች ጥብቅ የታክስ ሕጎችን መረዳትና መደገፍ ይጀምራሉ፣ እንዲሁም በዕርግጥ መክፈል ያለባቸውን በፈቃደኝነት ይከፍላሉ እያላችሁ ነው? ይህ ይቻላል ብላችሁ እንድታስቡ ያደረጋችሁ ምንድን ነው?” መልሳችሁ ምን ይሆናል?

3. ከባሃኦላህ ቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ የተወሰዱትን እነዚህን ጥቅሶች አንድ ወይም ሁለት በቃላችሁ እንድትይዙ ሃሳብ ቀርቧል፦

**“… እናንተ እራሳችሁና ሌሎች ከዚያ ይጠቀሙ ዘንድ፣ መልካምና ግሩም ፍሬዎችን ማፍራት አለባችሁ:: ስለዚህ በዕደ-ጥበባትና በሙያ ዘርፎች መሠማራት የእያንዳንዱ ግዴታ ነው፣ የማስተዋል ሰዎች ሆይ! የብልጽግና ምሥጢር ያለው በእነዚህ ውስጥ ነውና::”[22]**

**“ዓይኖቻችሁ ወደ ምህረት ከዞሩ፣ እናንተን የሚጠቅመውን ትታችሁ የሰው ዘርን የሚጠቅመውን አጥብቃችሁ ያዙ:: ዓይኖቻችሁም ወደ ፍትሕ ከዞሩ፣ ያን ለራሳችሁ የመረጣችሁትን ለጎረቤታችሁም ምረጡ::”[23]**

**“እርሱ ወንድሙን ከራሱ የሚያስቀድም የተባረከ ነው::”[24]**

**“መልካም ተግባር ጠፍቶ አያውቅም ወይም ምንግዜም አይጠፋም፣ ለእነዚያ ለሚተገብሩት ጥቅም ሲባል በጎ ድርጊቶች በአምላክ ዘንድ የሚከማቹ ሀብቶች ናቸው::”[25]**

**“የመጠነኝነት ገደቦች አልፋችሁ አትሂዱ፣ ከአባካኞችም ጋር እንዳትቆጠሩ ተጠንቀቁ::”[26]**

## ምዕራፍ 9

ከሥር በከንቱ/ጭፍን ጥላቻ ርዕስ ላይ በውይይቶች ለመሳተፍ የሚያግዟችሁ አንዳንድ ሃሳቦች አሉ::

ከንቱ ጥላቻ በሁሉም መልኩ - ማለትም የሃይማኖት፣ የዘር፣ የፆታ፣ የጎሳ፣ የኢኮኖሚ በሉት - የሰው ልጅን እሳቤ ያወድማል እንዲሁም ከአምላክ ትዕዛዛት ጋር ይፃረራል:: ለሺዎች ዓመታት የሰው ልጅ በእነዚህ ከንቱ ጥላቻዎች በአንዱ ወይም በሌላ መንስዔነት

በጦርነትና ደም መፋሰስ ተሰቃይቷል። እስከቀጠሉበትም ድረስ የሰው ልጅ ዕረፍት አይኖረውም።

አምላክ ነቢያቱን የላከበት ብቸኛው ዓላማ ፍቅር እና አንድነት ለመፍጠር ነው። ሁሉም መንግሥተ ሰማያዊ መጻሕፍት የተፃፉ የፍቅር ቃላት ናቸው። የመለያየት ምክንያት ከሆኑ ፍሬ-ቢስ ሆነዋል ማለት ነው። ስለዚህ፣ ሃይማኖታዊ ከንቱ ጥላቻ በተለይ ከአምላክ ፈቃድና ትዕዛዝ ጋር የሚፃረር ነው።

ብሔራዊ/አገራዊ ከንቱ ጥላቻ ፈፅሞ ተገቢ አይደለም። ምድር አንድ መሬት፣ አንድ አገር ናት። አገራትን የሚለያዩዋቸው መስመሮችና ድንበሮች ምናባዊ ናቸው፤ በአምላክ የተፈጠሩ አይደሉም። ሰዎች ወንዞን በሁለት አገሮች መካከል ያለ የድንበር መስመር አድርገው አወጁ፣ በእያንዳንዱ በኩል ስም በመስጠት፣ሆኖም ወንዙ ለሁለቱም የተፈጠረ እና ለሁሉም የተፈጥሮ ቦይ ነው። ሰዎች የሕይወትን ፀጋዎች የጦርነትና ውድመት መንስዔ እንዲሆን የሚገፋፋው ምናብና ድንቁርና አይደሉምን?

የዘር ከንቱ ጥላቻ ምንም ሳይሆን ከንቱ አምልኮ ነው። የሰው ቆዳ ቀለም የእርሱ/ሷ ቀደምት አያቶች የአየር ንብረትና  አካባቢን በግዜ ሂደት የመላመድ ውጤት ነው። መልካም ባህርይ የሰው ልጅ እውነተኛ መስፈርት ነው። ልቀት በዘር እና በቀለም ላይ አይመረኮዝም። እምነት፣ የልብ ንጽህና፣ መልካም ተገባሮችና አስመስጋኝ ንግግር ናቸው በአምላክ መንበር ተቀባይነት ያላቸው።

ለረጅም ጊዜያት፣ ሴቶች የወንዶች የበታችና ተጎጂ ሆኗል። በወንድና በሴት መካከል ያለ ልዩነት የቁሳዊው ዓለም መስፈርት ነው፤ በመንፈስ ዓለም ውስጥ ዕኩል ናቸው። በአምላክ ዕይታ፣ በወንድና በሴት መካከል ምንም ልዩነት የለም። ሁሉም የሰው ልጅ በእርሱ የማሰብ ችሎታና ጥልቅ ግንዛቤን ተቸሮታል። ሁሉም መንፈሳዊ ባህርያትን ለመጎናጸፍ ችሎታ አላቸው። በዚህ ዘመን የሰው ፆታ ለማግለያ የሚውልበት ምንም መሠረቶች የሉትም።

በብሉይ ኪዳን ቃላት መሠረት፣ አምላክ እንዲህ ብሏል፣ “ሰውን እንደመልካችን፣ በአምሳላችን፣ እንፍጠር።” ይህ በግልጽ ለሴቶችም ጭምር ይሠራል። የሰው ልጅ በአምላክ አምሳል ተፈጥሯል፤ ሲባል በሰው እውነታ ውስጥ መለኮታዊ ባህርያት ይንፀባረቃሉ እንዲሁም ይገለፃሉ ለማለት ነው። ይህ ለሁሉም የሰው ልጅ እውነት ነው። እነዚያ የአንድ ቀለም፣ ጎሳ ወይም ዜግነት ያላቸው ብቻ ናቸው በአምላክ አምሳል የተፈጠሩት ብሎ መናገሩ እንዴት ፈፅሞ የማይጨበጥ ነው። ሀብታሞችን ብቻ በእርሱ አምሳል የተፍጠሩ ናቸው ብሎ ማመላከት ወይም ወደ አምላክ ለመቅረብ መስፈርቱ በኅብረተሰብ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ላይ መሆን ነው ብሎ ማሰብ እንዴት የማይመስል ነው። የሰው ልጅ ከንቱ ጥላቻዎችን ዕርግፍ አድርጎ በመተው እና የመንግሥተ ሰማያዊውን ስነምግባሮች በማግኘት አማካይነት በቀር ብሩህነትን ሊቀዳጅ አይችልም።

1. ቀደም ሲል እንዳደረጋችሁ ይህንን ምንባብ አጥኑ እና ከዚያ ጓደኞቻችሁ እንዲሁም ጎረቤቶቻችሁ ከንቱ ጥላቻ እንዲወገድ በሚጠይቅ ውይይት ውስጥ ያመጡአቸውን አንዳንድ ተግዳሮቶች አስቡ።

______________________________________________

______________________________________________

2. ከላይ የተጠቀሱትን ሃሳቦች ስታካፍሉ የሰማ አንድ ሰው:- "ከንቱ ጥላቻ እያለን ላናውቀው እንችላለን?" ብሎ ቢጠይቃችሁ ምን መልስ ትሰጣላችሁ?

3. በውይይቶቻችሁ ውስጥ በእነዚህ ሃሳቦች ላይ ከሚከተሉት ከባሃኦላህ ቅዱሳን ጽሑፎች ጥቅሶች ለማካተት አጋጣሚ ልታገኙ ትችላላችሁ፦

**"ምድር አንድ አገር ናት፣ የሰው ልጆችም ዜጎቿ ናቸው"[27]**

**"የዓለም ቡቃያዎች በሙሉ የተገኙት ከአንድ ዛፍ ነው፣ ጠብታዎችም ሁሉ ከአንድ ውቅያኖስ፣ እንዲሁም ህላዌዎች ሁሉ ኑባሬያቸውን የሚያገኙት ከአንድ ህላዌ ነው።"[28]**

**"ያ በዚህ ዘመን እራሱን ለመላው የሰው ዘር ግልጋሎት የሚሰጥ፣ በዕርግጥ ሰው ነው።"[29]**

**"የመልካም ባህርይ ብርሃን የፀሃይ ብርሃንንና ከርሷ የሚመነጨውን አንፀባራቂነት ይልቃል። "[30]**

**"የሰው መለያው በጌጣጌጥና ሀብት ላይ አይመረኮዝም፣ ይልቁንም በመልካም ጠባይና እውነተኛ መረዳት እንጂ።"[31]**

**"ምናልባት የባዕድ አምልኮ ጣዖቶችንና የሰዎችን ምናቦች መጋረጃዎች ቀዳችሁ ትጥሉ ዘንድ በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ በፀጋው እንድትታገዙ አምላክ ያድላችሁ።"[32]**

**"ከሁሉም ሰዎች እጅግ በጣም ቸልተኛው እርሱ በከንቱ የሚከራከርና እራሱን ከወንድሙ ለማስበለጥ የሚሻው ነው።"[33]**

## ምዕራፍ 10

ከወዳጆች ጋር ስትጨዋወቱ፣ ብዙውን ግዜ ስለ ወንዶች እና ሴቶች ዕኩልነት በሚከተለው ምንባብ ውስጥ ያሉትን ሃሳቦች ለመጠቀም ትችላላችሁ።

ግዑዟ ፀሃይ፣ በብርሃኗ እና ሙቀቷ አማካኝነት፣ በምድር ላይ ያሉትን ነገሮች ሁሉ እውነታ ትገልፃለች። በዛፉ ውስጥ የተደበቀው ፍሬ በቅርንጫፎቹ ላይ የሚታየው ለፀሃዩ ኃይል

ለሚሰጠው ምላሽ ነው። እንደዚሁም፣ የእውነት ፀሃይ፣ በመንፈሳዊው ሰማይ ውስጥ በሙሉ ድምቀት ሲያበራ፣ ከዚህ በፊት ያልነበሩ እውነታዎችን፣ ገሃድ ያወጣቸዋል።

ለዚህም ነው፣ በዚህ ዘመን፣ የወንዶችና የሴቶች ዕኩልነት መርህ ሙሉ በሙሉ እውቅና የተሰጠው እና አሁን የተረጋገጠ ሀቅ የሆነው።

በአምላክ ዕይታ በወንዶችና ሴቶች መካከል ምንም ልዩነት እንደሌለ ባሃኦላህ ግልፅ በሆኑ ቃላት ገልጿል። ለዘመናት የኖረው ዕኩል ያለመሆን ሁኔታ በወንዶች የበላይነት ምክንያት አይደለም፤ ይልቁንም ሴቶች አቅማቸውን ሁሉ እንዲያሳድጉ ተመሳሳይ ዕድል ስላልተሰጣቸው ብቻ ነበር። ሆኖም፣ ከንቱ ጥላቻ ቢደርስባቸውም፣ እጅግ በጣም ታላቅ ስኬቶችን የተቀዳጁ የብዙ ሴቶችን ሕይወት ታሪክ ይዘግባል።

እንደዚህ ካሉት ሴቶች ኢራናዊዋ ገጣሚ ታሂሬህ ነበረች። የተወለደችው በ1800ዎቹ መጀመሪያ ሴቶች ሙሉለሙሉ የወንዶች የበታች በሆኑበት አገር ነበር። የአምላክን አዲስ ግልፀት እውነት ለመቀበል የመጀመሪያዋ ሴት ነበረች። የአዲስ መለኮታዊ ቀንን ጎህ መቅደድ እንደመሰከረች፣ የወንዶችና ሴቶች ዕኩልነት እውነታ እውቅና የሚያገኝበት ግዜ እንደመጣ አመነች። ጉልበቷን ይህን እውነት ለማወጅ መስዋዕት አደረገች። እውቀቷና አንደበተ ርቱዕነቷ በርሷ ዘመን የነበሩትን እጅግ የተማሩትን ግራ አጋባ። የጨቋኝ ንጉሥ እና የደነቆሩ እንዲሁም በኩራት የታበዩ ካህናት ሁሉም ኃይሎች ቢቃወሟትም፣ እውነቱን ለመናገር ለአፍታም አላመነታችም። እናም በመጨረሻ በታላቅ ፅናት ለተቀበለችው እምነት ሕይወቷን ሰጠች።

አምላክ ያልወጠነውን ማመን ድንቁርና እና ባዕድ አምልኮ ነው። በዚህ ዘመን በሰው ልጅ ጥረት መስኮች ሁሉ ሴቶች የተማሩ ለመሆን እንዲችሉ እያንዳንዱ ዕድል እና ከወንዶች ጋር የዕኩልነት ደረጃ ሊፈቀድላቸው ይገባል። በመንፈሳዊው ግዛት እንደሆነው፣ የወንዶችና ሴቶች ዕኩልነት በዚህ ዓለም ውስጥ እውን እስካልሆነ ድረስ፣ የሰው ልጅ እውነተኛ ዕድገት የማይቻል ነው።

1. እንደ ሁልጊዜው በቡድን ሆናችሁ ይህን ምንባብ በማጥናት ሃሳቦቹን መናገር ተለማመዱ። በቅርብ ግዜ ከወዳጆቻችሁ ጋር ባደረጋችሁት ማንኛውም ጭውውቶች ከሚሰጡት ጥልቅ ዕይታዎች የጠቀሙ ነበሩ? በውይይቱ ውስጥ የተነሱት ጉዳዮች ምን ነበሩ?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

2. በሁሉም የጥረት መስኮች ሴቶች ከወንዶች ጋር ዕኩል ደረጃ እንዲቀዳጁ በዚህ ዘመን ኅብረተሰብ ዘንድ መቀየር ያለባቸው ተንሰራፍተው የሚገኙ እምነቶችና አመለካከቶች ምንድን ናቸው?

3. ከሥር ከባሃኦላህ ቅዱሳን ጽሑፎች የተውጣጡ ጥቂት ጥቅሶች በቃላችሁ ለመያዝ ትፈልጉ ይሆናል።

**"በአምላክ ዘንድ ሴቶችና ወንዶች ዕኩል ነበሩ ወደፊትም ሁልግዜ ዕኩል ይሆናሉ።"[34]**

**"እኛ ለምን ከአንድ ዓይነት ትቢያ እንደፈጠርናችሁ አታውቁምን? አንዱ ከሌላው ራሱን ከፍ እንዳያደርግ ነው።"[35]**

**"በዚህ ዘመን የመለኮታዊ ፀጋ እጅ መበላለጥን ሁሉ አስወግዷል። የአምላክ አገልጋዮችና የእርሱ ሴት አገልጋዮች በአንድ ደረጃ ላይ ይታያሉ።"[36]**

## ምዕራፍ 11

እንድታጠኑ የምትጠየቁት የመጨረሻው ምንባብ ርዕስ ሁለንተናዊ ትምህርት ላይ ነው፦

ትምህርትን ማራመድ የዘመናችን እጅግ በጣም አስችኳይ መስፈርት ነው። ትምህርትን ከአሳሳቢ ጉዳቸው መሃል አንዱ ካላደረጉት በቀር ማንም አገር ብልፅግናን ሊቀዳጅ አይችልም። ለአንድ ሕዝብ ማሽቆልቆል ዋነኛው ምክንያት የዕውቀት ተደራሽነት እጦት ነው።

ትምህርት በጨቅላነት መጀመር አለበት። ልጆቻቸውን ለማስተማር የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ፣ ጠባያቸውን በመንፈሳዊና ሞራል ሕግጋት መሠረት ማረቅ፣ በስነ-ጥበቦችና በሳይንሶች እንዲሰለጥኑ ማረጋገጥ የአባትና እናት ተግባር ነው። እናቶች የሰው ልጅ የመጀመሪያ አስተማሪዎች ናቸው፤ ልጆቻቸውን በዕውቀት ጡት ይንከባከባሉ። እያንዳንዱ ልጅ መማር አለበት፤ ይህ መዘንጋት ያለበት ጉዳይ አይደለም። ወላጆች አስፈላጊውን ወጪ መሸፍን ከቻሉ፣ ያን ማድረግ አለባቸው። ካለበለዚያ ማኅበረሰቡ ለልጁ / ልጅቷ ትምህርት መፍትሔ መስጠት አለበት።

ትምህርት በእያንዳንዱ የሰው ልጅ ውስጥ ልቀትን የመቀዳጀት እሾት ሊያሳለብት ይገባል። በሰው ልጅ ፍፁምነት ልንማረክና በጥልቅ ስሜት ልናከናውን ይገባል። ለመንፈሳዊ ልቀት፣ በሰው ልጅ ዓለም በመልካም ባህርያት ማለትም ቅንነት፣ ታማኝነት፣ ለሰው ልጅ አገልግሎት፣ ፍቅርና ፍትሕ ልንታወቅበት እንደሚገባ መሻት አለብን። ሰላምንና አንድነትን ለማራመድ እንዲሁም ትምህርትን ለማስፋፋት በጥረቶቻችን ተለይተን ለመታወቅ መፈለግ አለብን። ሰዎችን በእንደዚህ ዓይነት ጎዳና ላይ ለመምራት የእውነተኛ የትምህርት ተግባር ነው።

1. ይህን ምንባብ በቡድናችሁ ውስጥ ካጠናችሁ በኋላ፣ ወዳጆቻችሁ ስለትምህርት ያላቸውን አንዳንድ ስጋቶች ለመለየት ሞክሩ። የላይኞቹ ሃሳቦች ስጋቶቻቸውን እንዴት ይዳስሣሉ?

2. ከሚከተሉት የባሃኦላህ ቅዱሳን ጽሑፎች ጥቅሶች አንድ ወይም ከዚያ በላይ በቃላችሁ እንድትይዙ ሃሳብ ቀርቧል፦

**“ሰው ያለ ዕውቀት ወይም ክህሎቶች እንዲቀር አይፈለግም፣ ምክንያቱም እንዲህ ከሆነ የመከነ ዛፍ ነውና::”**[37]

**“… አዕምሮዎቻችሁንና ፈቃዳችሁን የምድርን ሕዝቦችና ዘሮች ወደማስተማሩ ተግባር አዙሩ::”**[38]

**“ስነ-ጥበቦች፣ የእጅ ሥራዎችና ሳይንሶች የሕያውን ዓለም ከፍ ከፍ የሚያደርጉ፣ ለክብሩም የሚመጥኑ ናቸው::”**[39]

**“በእውነቱ፣ ዕውቀት ለሰው ልጅ እውነተኛ ሃብት፣ እንዲሁም የክብር፣ የቸርነት፣ የደስታ፣ የከፍተኝነት፣ የደስታና የሐሴት ምንጭ ነው::”**[40]

## ምዕራፍ 12

*ሠላም በያንዳንዱ አዕምሮ ውስጥ ያለ ጉዳይ ነው:: የሠላም መመሥረት እጅግ በጣም አስቸኳይና ወሳኝ ነው:: አሁን በቀዳሚዎቹ ምንባቦች ለተዘረዘሩት መርሆዎች አንዳንድ ሃሳቦች ስላካፈላችሁ፣ሁለንተናዊ ሠላም ጥያቄዎች ላይ ማሰላሰሉ ጠቃሚ ሆኖ ልታገኙት ትችላላችሁ::*

*በዕርግጥ፣ ጦርነትን ለማስወገድ መንግሥታት ተግባራዊ ዕርምጃዎችን መውሰድ ላይ በአብዛኛው ይመረኮዛል:: በአገራት መካከል ያሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ዓይነቶች እንደመብዛታቸው፣ ለሠላም መስፈን አለመግባባቶችን ለማስወገድና የጦር መሣሪያዎችን ለመቀነስ ፖለቲካዊ ስምምነቶች ጠቃሚ ናቸው:: ሆኖም፣ እንዲህ ያሉት ዕርምጃዎች ምንም ያህል አስፈላጊ ቢሆኑም፣ ቀደም ብለው ለውይይት የተነሱት መርሆዎች በመላው ዓለም እስካልተመሠረቱ ድረስ ወደ ዘላቂ ሠላም አይመሩም:: ሰዎች እውነታን መመርመር ካልተማሩና እውነት አንድ መሆንዋን መገንዘብ ካልቻሉ፣ ለዘመናት የዘለቁት ጥላቻዎች ባሉበት ሁኔታ አይቀጥሉም? የሚለውን እራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል:: ሁላችንም ተመሳሳይ መነሻ አለን:: አምላክ በግልፀቶቹ አማካይነት ሁላችንንም መጠበቁንና ማሠለጠኑን ይቀጥላል:: ትምህርቶቻቸው በአንድ ዓይነት ፍቅርና የወዳጅነት መሠረት ላይ ያርፋል:: የሃይማኖት አንድነት እውቅና ሲያገኝ ብቻ ሃይማኖታዊ ሁከት ይቆማል እንዲሁም የሃይማኖት ብርሃን የሠላምን ጎዳና ያበራዋል:: እያንዳንዱ ለሠላም ኃያል መሰናክል የሆነውን የድንቁርናን ደመናዎች ለማስወገድ እና ማንኛውም ዓይነት ከንቱ ጥላቻ ሐሰትነት ለማሳየት፣ ሳይንስና ሃይማኖት ተቀናጅተው መሥራታቸው አስፈላጊ አይሆንምን? ብለን ይበልጥ መጠየቅ አለብን:: የአሁኑ በሃብታምና ድሃ መካከል ያለው ገደብ የለሽ ልዩነት በእያንዳንዱ የዓለም ጥግ*

ምላሽ ካላገኘ፣ ሠላም የሠፈነበት ዓለም ሊገነባ ይችላል ወይ? የሚለው አሁንም መጠየቅ ያለበት ሌላ ጥያቄ ነው። እንዲሁም፣ በሁሉም የሰው ልጅ ጥረት መስኮች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች በዕኩል ደረጃ እንዲንቀሳቀሱ እስካልተፈቀደላቸው ድረስ በጣም አብዛኛውን ታሪክ የሚገልፀው ብጥብጥ ለሠላምና እውነተኛ ብልፅግና መንገዱን አይለቅም። መጪዎቹ ትውልዶች እንዲህ ባሉ መርሆዎች ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ መማር አለባቸው፣ ካልሆነ እያንዳንዱ ለሠላም ያለ ተስፋ ይንኮታኮታል። ለሰው ልጅ የወደፊት ዕጣ-ፈንታ ከሚቆረቆሩ ሌሎች ጋር ልታካፍሏቸው እንድትችሉ ተከታዩን የባሃኦላህ ቅዱሳን ቃላት በቃል ለመያዝ ትፈልጉ ይሆናል፦

**"አንድነቱ በጥብቅ እስካልተመሠረተና እስከሚመሠረት ድረስ፣ የሰው ልጅ ደህንነቱ፣ ሠላሙና ዋስትናው የማይደረስባቸው ናቸው።"**[41]

# ማጣቀሻዎች


1. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 1983፣2017 ኅትመት)፣ 109፣አንቀጽ 2፣ ገጽ 243።

2. ዝኒ ከማሁ፣ 132፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 325።

3. ዝኒ ከማሁ፣ 34፣ አንቀጽ 5፣ ገጽ 89።

4. *ከኪታቢ አቅዳስ በኋላ ከተገለፁት የባሃኦላህ ፅላቶች* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 1988፣ 2005 ኅትመት)፣ ቁጥር 11.1 ገጽ 161።

5. ባሃኦላህ፣ *ኪታቢ ኢቃን፦ የእርግጠኝነት መጽሐፍ* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2003፣ 2018 ኅትመት)፣አንቀጽ 151፣ ገጽ 131።

6. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት*፣28፣ አንቀጽ 2፣ ገጽ 77።

7. ዝኒ ከማሁ፣ 24፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 66።

8. ዝኒ ከማሁ፣ 111፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 246።

9. ዝኒ ከማሁ፣ 43፣ አንቀጽ 6፣ ገጽ 106።

10. ዝኒ ከማሁ፣ 110፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 244።

11. *ከኪታቢ አቅዳስ በኋላ ከተገለፁት የባሃኦላህ ፅላቶች*፣ ቁጥር፣ 15.4፣ ገጽ 220።

12. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት*፣ 95፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 219 - 20።

13. *ከኪታቢ አቅዳስ በኋላ ከተገለፁት የባሃኦላህ ፅላቶች*፣ ቁጥር፣ 9.13፣ ገጽ 141።

14. ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 5.13፣ ገጽ 51።

15. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት*፣ 112፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 247 - 48።

16. ዝኒ ከማሁ፣ 132፣ አንቀጽ 3፣ ገጽ 326።

17. ዝኒ ከማሁ፣ 111፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 246።

18. *ከኪታቢ አቅዳስ በኋላ ከተገለፁት የባሃኦላህ ፅላቶች*፣ ቁጥር፣ 7.20፣ ገጽ 90።

19. ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 6.25፣ ገጽ 66 - 67።

20. ባሃኦላህ፣ በሾጊ ኤፌንዲ የተጠቀሰ፣ *የመለኮታዊ ፍትኅ ምጽኣት* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2006፣2018 ኅትመት)፣አንቀጽ 42፣ ገጽ 41።

21. *ከኪታቢ አቅዳስ በኋላ ከተገለፁት የባሃኦላህ ፅላቶች*፣ ቁጥር፣ 3.23፣ ገጽ 27።

22. ባሃኦላህ፣ *ኅቡዓተ-ቃላት* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2003፣2012 ኅትመት)፣ፋርስኛ ቁጥር 80፣ ገጽ 51።

23. *ከኪታብ አቅዳስ በኋላ ከተገለፁት የባሃኦላህ ፅላቶች፣* ቁጥር፣ 6.19፣ ገጽ 64።

24. ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 6.37፣ ገጽ 71።

25. ባሃኦላህ፣ ከሁቁቁላህ ውስጥ - የአምላክ ድርሻ፡- በዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትኅ የጥናትና ምርምር ማዕከል ከባሃኦላህና አብዱል-ባሃ እንዲሁም በሾጊ ኤፌንዲና በእርሱ ስም ከተጻፉት ደብዳቤዎች እንዲሁም ከዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትኅ የተውጣጣ የጥንቅር ጽሑፍ (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2007)፣ ቁጥር 16፣ ገጽ 16።

26. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣* 118፣ አንቀጽ 2፣ ገጽ 283።

27. ዝኒ ከማሁ፣ 117፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 282።

28. ባሃኦላህ፣ በሾጊ ኤፌንዲ የተጠቀሰ፣ *ቃል የተገባው ቀን መጥቷል* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 1996፣2018 ኅትመት)፣አንቀጽ 279፣ ገጽ 187።

29. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣* 117፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 282።

30. *ከኪታብ አቅዳስ በኋላ ከተገለፁት የባሃኦላህ ፅላቶች፣* ቁጥር፣ 4.11፣ ገጽ 36።

31. ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር፣ 6.3፣ ገጽ 57።

32. ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር፣ 6.3፣ ገጽ 58።

33. ባሃኦላህ፣ *ኅቡዓተ-ቃላት* ፣ ፋርስኛ ቁጥር 5፣ ገጽ 23 - 24።

34. ባሃኦላህ፣ ስለ *ሴቶች፦ ከባሃላህ ጽሑፎች፣አብዱል-ባሃ፣ ሾጊ ኤፌንዲ እና ዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትኅ የተውጣጡ፣* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣1986፣1997 ኅትመት)፣ቁጥር 54፣ ገጽ 26።

35. ባሃኦላህ፣ *ኅቡዓተ-ቃላት* ፣ አረብኛ ቁጥር 68፣ ገጽ 20።

36. ባሃኦላህ፣ ስለ *ሴቶች* ጥንቅር ውስጥ ፣ ቁጥር 3፣ ገጽ 3።

37. ባሃኦላህ፣ *'ኢን ኤክሰለንስ ኢን ኦል ቲንግስ'፦ በዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትኅ የጥናትና ምርምር ማዕከል፣* ከባሃኢ ቅዱሳን ጽሑፎች የተውጣጣ የጥንቅር ጽሑፍ (ሎንዶን፡-ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣1981፣1989 ኅትመት)፣ቁጥር 5፣ ገጽ 2።

38. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣* 156፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 378።

39. ባሃኦላህ፣ *ይድረስ ለተኩላው ልጅ* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣1988፣2016 ኅትመት)፣ ገጽ 26።

40. *ከኪታብ አቅዳስ በኋላ ከተገለፁት የባሃኦላህ ፅላቶች፣* ቁጥር፣ 5.13፣ ገጽ 52።

41. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣* 131፣ አንቀጽ 2፣ ገጽ 324።



# የጥልቀት ትምህርት ጭብጦች

**ዓላማ**

**መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸው ጭብጦች ላይ ለመጨዋወት ወዳጆችን እና ጎረቤቶችን የመጎብኘት ልማድ ለማዳበር**

## ምዕራፍ 1

ልክ እንደቀዳሚው፣ ይህ ሦስተኛው ክፍል፣ ወደ ትርጉም አዘልና አነቃቂ ጭውውት ለመግባት በሚያስችሉን ችሎታዎች ላይ ያተኮረ ነው። በሁለተኛው ክፍል ውስጥ ትኩረታችን የነበረው በተለያዩ ሁኔታዎች መንፈሳዊ መርሆዎችን በማጣቀስ የጭውውት ደረጃን ከፍ ለማድረግ ራሳቸውን የሚያቀርቡበት ነበር። እዚህ ትኩረቱ ወደ ወዳጆችና ጎረቤቶች ቤቶች በምናደርጋቸው ጉብኝቶች ለማኅበረሰቡ ሕይወት ማዕከል የሆኑ ጭብጦችን በጋራ ወደመመርመር ያተኩራል።

በመላው ዓለም ባሉ መንደሮችና አጎራባች ሠፈሮች ውስጥ፣ የወዳጆች ቡድኖች የጸሎተ ሱታፌ ስብሰባዎች፣ የህፃናት መንፈሳዊ ትምህርት ክፍሎች፣ የታዳጊ ወጣት ስብሰባዎች፣ ጥናት ክበባት፣ እንዲሁም የወጣት ካምፖችና የተለያዩ ዓይነት ካምፔይኖች/ዘመቻዎችን የሚያካትቱ የተያያዙ ተግባሮች ስብስብ ውስጥ በጥብቅ ተጠምደዋል። ይህ የተግባር ዘይቤ በአንድ ውስን ስፍራ ሥር ሲሰድና ቁጥራቸው እየጨመረ የሚሄድ እራሳቸውን ለአገልግሎት ተግባሮች ሲያስገዙ፣ የወዳጆች አስኳል በመጠንና በጥንካሬ ያድጋል። አሁን ኃይል እያሰባሰበ ላለው የማኅበረሰብ ግንባታ ሂደት በመንደሮች ወይም በአጎራባች ሠፈሮች ባሉ እያደጉ በሚሄዱ ቤቶች የሚደረጉ ስልታዊ የጉብኝቶች ፕሮግራም ወሳኝ ክፍል ነው። እንዲህ ባሉ ጉብኝቶች ወቅት የተለያዩ ጭብጦች ይዳሰሳሉ። ለምሳሌ፣ የባሃኢ ህፃናት ክፍል አስተማሪው፣ የልጆቹን ወላጆች ከትምህርቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጭብጦች ላይ እንዲወያዩ በተደጋጋሚ ሊጠራቸው ይገባል። በእነዚህ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ተስፋ የሠነቁ ዓመታት ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶችና ዕድሎች ላይ ተያያዥ በሆኑ ርዕሶች ለመወያየት በእነዚያ እንደ አነቃቂዎችና አስጠኚዎች በሚያገለግሉት ወደ ታዳጊ ወጣቶች እና ወጣቶች ቤቶች ተመሳሳይ ጉብኝቶች መደረግ አለባቸው። ከአንድ የቤተሰብ አባላት ጋር ስለእምነቱ ዕውቀታቸውን በሚያጠልቅ ጭብጦች ላይ ጭውውቶች ማድረግ ዕኩል ጠቃሚ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ። በአጠቃላይ፣እንዲህ ያሉት ጉብኝቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ ብቅ እያለ ለመጣው የወዳጅነት ባህል ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ የተጋነኑ ሊሆኑ አይችሉም።

## ምዕራፍ 2

ለዚህ ክፍል ዓላማ፣ ከላይ የተገለጸው ሂደት የሚጎለብትበትን ምናባዊ አጎራባች ሠፈር እንመለከታለን፣ እንዲሁም ቤት በሚጎበኝበት ወቅት ሊጀመሩ የሚችሉትን የጭውውት ዓይነቶች ለመሞከር እንደ አውድ እንጠቀምበታለን።

አሌሃንድራ ወጣት ሴት የሦስተኛ ዓመት ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ናት። እርሷና ተማሪ የሆነ አንዱ ወንድሟ በተወለዱበትና ባደጉበት ቤት ውስጥ፣ በምናብ በሳልነው ሠፈር ከወላጆቻቸው ጋር ይኖራሉ። አራቱ እና ወደሠፈሩ በቅርብ የገቡት ወጣት ባልና ሚስት ወደ 8,000 የሚጠጋ የሕዝብ ብዛት መሃል በነርሱ ዙሪያ እየተመሠረቱ ስላሉት ዕንቅስቃሴዎች ዕድገት ላይ ለመጸለይና ለመመካከር በየሳምንቱ ይገናኛሉ። በእነዚህ ሳምንታዊ ስብሰባዎች ከግዜ ወደ ግዜ ሌሎች ሦስት ሰዎች ስለራሳቸው የአገልግሎት ተግባሮች ብቻ ሳይሆን ስለጠቅላላው የማኅበረሰብ ግንባታ ሂደትም ስልታዊ በሆነ መልኩ ለማሰብ እየጀመሩ ናቸው፦ ከስድስት ወር በፊት የጀመረው አንድ የህፃናት ክፍል አስተማሪ እና ወጣት በነበሩበት ወቅት የራሳቸው ቡድን አነቃቂ የነበረው እንዲሁም ያለማቋረጥ ወላጆቹን በሚጎበኘው በአሌሃንድራ ታላቅ ወንድም ዕገዛ የታዳጊ ወጣት ቡድን ጥረቶችን እየመሩ ያሉ ሁለት የአሥራ ሰባት ዓመት ወጣቶች እየተሳተፉ ናቸው።

የምንመለከተው የመጀመሪያው የጭውውቶች ስብስብ በአሌሃንድራና በሠፈሩ ውስጥ በደንብ በታወቁና በተከበሩ በሳንቼዝ ቤተሰብ መካከል የተደረገውን ነው፡፡ ባልና ሚስቱ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን አሳድገው፣ ከአሌሃንድራ ቤት ጥቂት ቅያሶች ራቅ ብለው ለብቻቸው የሚኖሩ በስልሳዎቹ የሚገኙ አዛውንቶች ናቸው፡፡ አቶ ሳንቼዝና ወ/ሮ ሳንቼዝ መጻፍና ማንበብ ተምረዋል ነገር ግን ብዙ መደበኛ ትምህርት አላገኙም፡፡ የሚያጣጥሙት የናኘ ክብር የተገኘው ከልግስናና ከንጹህ ተግባራት ሕይወት ውስጥ ባገኙት ተሞክሮ ጥበብ አማካይነት ነው፡፡ ለተወሰነ ግዜ የባሃኢ ትምህርቶችን ያውቁ ነበር፣ ነገር ግን በቅንነት ለመመርመር የወሰኑት በቅርብ ነው፡፡ ከሳምንት በፊት፣ ማኅበረሰቡን ለመቀላቀል ፍላጎት እንዳላቸው ለአሌሃንድራ ወላጆች ነግረዋቸዋል፡፡ እነሱን እንኳን ደህና መጣችሁ ለማለት ስብሰባ የታቀደ ሲሆን፣ በተጨማሪም፣ ስለ እምነቱ ያላቸውን ዕውቀት ለማጥለቅ ተከታታይነት ያላቸው ጭብጦች ከነሱ ጋር ለመካፈል አሌሃንድራ ለብዙ ሳምንታት በተከታታይ እንድምትጎበኛቸው ከስምምነት ተደርሷል፡፡ የጉብኝቶቹን አቀራረብ በመከታተል፣ እነዚህን ጭብጦች ለመመርመር ትችላላችሁ በተመሳሳይ ሁኔታም እንዲህ ባሉ አጋጣሚዎች ላይ የሚኖሩትን የጭውውት ፍሰት ላይ ታሰላስላላችሁ፡፡

## ምዕራፍ 3

አሌሃንድራ የመጀመሪያ ጭውውቷን ከአቶ እና ወ/ሮ ሳንቼዝ ጋር ከሥር ባለው፣ የአምላክ ዘለዓለማዊ ቃልኪዳን ጭብጥ፣ አጭር መግለጫ ላይ ለመመሥረት አቅዳለች፡፡

> አምላክ፣ የሁሉም ነገሮች ፈጣሪ፣ አንዱ፣ ተወዳዳሪ የሌለው፣ በገዛ ራሱ ነዋሪው ነው፡፡ የአምላክ ህላዌ ለሰው ልጅ አዕምሮ ለመገንዘብ የማይቻል ነው፣ ውስኑ የማይወሰነውን ሊገነዘብ አይችልምና፡፡ ሰዎች እርሱን የሚወክሉበት መንገድ የገዛ ራሳቸው ምናቦች ውጤቶች ብቻ ናቸው፡፡ አምላክ ሰው አይደለም፣ በመላው ሁለንተን ዓለም ዝም ብሎ የተንሠራፋ ኃይልም አይደለም፡፡ የህልውናችን ምንጭ ለማመላከት መጠቀም ያሉብን ቃላት፣ እንደ መንግሥተ ሰማያዊ አባት፣ መንግሥተ ሰማያዊ ኃይል፣ ታላቁ መንፈስ፣ በሰው አንደበት የእርሱን ስሞችና ባህርያት ይገልጻሉ ሆኖም እርሱን ለመግለጽ ሙሉለሙሉ በቂ አይደሉም፡፡
>
> በኅቡዓተ ቃላት ውስጥ እንዲህ እናነባለን፦
>
> **"የሰው ልጅ ሆይ! ያንተን መፈጠር ወደድኩ፣ ስለዚህም ፈጠርኩህ፡፡ እንግዲህ ስምህን እንዳነሳና ነፍስህን በሕይወት መንፈስ እሞላት ዘንድ አንተም አፍቅረኝ፡፡"[1]**
>
> በዚህ ምንባብ ውስጥ፣ አምላክ ለእኛ ያለው ፍቅር ለእኛ ህልውና ዋነኛ ምክንያት እንደሆነ ባሃኦላህ ይነግረናል፡፡ የሚጠብቀንን፣ የሚያኖረንን፣ እና በሕይወት መንፈስ የሚሞላንን ስለዚህ ፍቅር ምንግዜም ንቁ መሆን ይገባናል፡፡ በችግር ወይም በምቾት፣ በሀዘን ወይም በደስታ፣ የእርሱ ፍቅር ሁሌም እንደሚያቅፈን ማስታወስ አለብን፡፡
>
> ከባሃኢ ትምህርቶች፣ ከፍቅሩ የተነሳ ከፈጠረን በኋላ፣ አምላክ ከእኛ ጋር ቃልኪዳን እንደገባ እንማራለን፡፡ "ቃል-ኪዳን" የሚለው ቃል ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግ ውል ወይም ስምምነት ማለት ነው፡፡ በዘለዓለማዊው ቃል-ኪዳን መሠረት፣ ፍፁም ለጋሱ ፈጣሪ ፈፅሞ ለብቻችን አይተወንም እናም፣ ከግዜ ወደ ግዜ፣ ከክስተቶቹ በአንዱ አማካይነት የእርሱን ፈቃድና ዓላማ እንድናውቅ ያደርገናል፡፡

"መከሰት" የሚለው ግስ መገለጽ፣ ከዚህ በፊት የማይታወቅን አንድ ነገር ማሳየት ማለት ነው። የአምላክ ክስተቶች እነዚያ የአምላክን ቃል ለእኛ የሚገልጹ ልዩ ስብዕናዎች ናቸው። እነርሱ በአምላክ ፈቃድ መሠረት እንዴት እንደምንኖር እና እውነተኛ ደስታን እንዴት እንደምንቀዳጅ የሚያስተምሩን ሁለንተናዊ መምህራን ናቸው። ከእነዚህ ክስተቶች መካከል አብርሃም፣ ክሪሽና፣ ሙሴ፣ ዞሮአስተር፣ ቡድሃ፣ ክርስቶስ፣ ሙሐመድ እና፣ በዕርግጥም በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የዚህ ዘመን የአምላክ መንታ ክስተቶች የሆኑት ባብ እና ባሃኦላህ ናቸው።

ስለዚህ፣ በዘለዓለማዊው የአምላክ ቃል-ኪዳን፣ የእርሱ ድርሻ ሁሌም የተሟላ ነበር። ሁላችንም ራሳችንን መጠየቅ ያለብን መሠረታዊ ጥያቄ፣ "የቃል-ኪዳኑን የኔን ድርሻ እንዴት አሟላለሁ?" ነው። በሁሉም ሃይማኖታዊ መጽሐፍት ውስጥ የምናገኘው መልስ፦ የአምላክ ክስተትን በማወቅ እና የእርሱን ትምህርቶች በመታዘዝ ነው። ይህ ምላሽ የሕይወታችንን ዋነኛ ዓላማ ስለሆነው አምላክን ማወቅና ማምለክ ላይ ያነጣጥራል። በአጭሩ የግዴታ ጸሎት ውስጥ፣ እንዲህ እናውጃለን፦

**"አምላኬ ሆይ፣ አንተን እንዳውቅና እንድሰግድልህ እንደፈጠርከኝ እመሰክራለሁ። በዚህ ሰዓት፣ የእኔን ደካማነትና የአንተን ኃያልነት፣ የእኔን ምስኪንነትና የአንተን ሀብታምነት አረጋግጣለሁ።**

**"ከአንተ በአደጋ ግዜ ረዳት፣ በገዛ ራሱም ነዋሪ ከሆንከው በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።"**[2]

በእርሱ ክስተቶች አማካይነት ካልሆነ በቀር አምላክን ማወቅ ስለማንችል፣ የሕይወታችንን ዓላማ ማሳካት የምንችልበት ብቸኛው መንገድ እነርሱን በማወቅ እና ትምህርታቸውን በመከተል ነው። ዛሬ፣ ያ ሰላምና ፍትሕ በምድር ላይ ይመሠረታል የተባለው እየተሟላ ባለበት፣ በሁሉም ቅዱሳን መጽሐፍት ቃል በተገባለት ጊዜ፣ ለመኖር ለተሰጠን ፀጋ ልባችን በምሥጋና ይጥለቀለቃል። ባሃኦላህ እንዲህ ያውጃል፦

**"ይህ ቀን፣ የአምላክ እጅግ በጣም የላቁ ችሮታዎች በሰዎች ላይ የፈሰሱበት፣ የእርሱ እጅግ በጣም ታላቅ ፀጋ በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ውስጥ የተናኘበት ቀን ነው። የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ልዩነቶቻቸውን በማስወገድ፣ በእርሱ ክብካቤና ፍቅራዊ-ደግነት ጥላ ሥር፣ በፍፁም አንድነትና ሰላም መኖር አለባቸው።"**[3]

ታሪካችንን ከመቀጠላችን በፊት፣ የላይኛውን ማብራሪያ ማንበብ እና ከሌሎች የቡድናችሁ ተሳታፊዎች ጋር አንቀጽ በአንቀጽ ልታሰላስሉበት ይገባል። እያንዳንዳችሁ ሃሳቦቹን ተፈጥሮአዊ በሆነ መልኩና በቀላሉ መግለጽ እስክትችሉ ድረስ፣ ጥያቄዎችን እርስ በእርስ መጠያየቅና በጋራ መመለስ ትችላላችሁ። ጥቅሶቹን በደንብ መማር በተለይ አስፈላጊ ነው፣ የዚህ ዓይነት ውይይቶች ውስጥ ከቅዱሳን ጽሑፎች ምንባቦችን ማካፈል እጅግ ጠቃሚ ነው። የሚከተሉት መልመጃዎች በዚህ ክፍል ውስጥ ስለቀረቡት ሃሳቦች እና የተጠቀሱት ምንባቦች ትርጉሞች ላይ ለማሰብ ይረዳችኋል፦

1. አምላክ ሊታወቅ የማይችል ህላዌ እንደሆነ ለአንድ ሰው እንዴት ልትገልጹ ትችላላችሁ? በዚህ ረገድ ከላይ በተገለጸው ውስጥ የመጀመሪያው አንቀጽ ሊያግዛችሁ ይችላል።

________________________________________________________

________________________________________________________

2. አምላክ ለምን ፈጠረን? ______________________________

3. "ቃል-ኪዳን" የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? ____________________

4. ከሰው ልጅ ጋር በገባው ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳኑ አምላክ ምን ቃል ገብቷል? ________

5. የሕይወታችን ዓላማ ምንድን ነው? __________________________

6. የአምላክን ህላዌ በጭራሽ ማወቅ ካልቻልን፣ የሕይወታችን ዓላማ አምላክን ማወቅ ነው ማለት ምን ማለት ነው? ______________________________

7. "መከሰት" የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? _______________________

8. አንዳንድ የአምላክ ክስተቶችን ስም ዘርዝሩ፦ ______________________

9. በቃል-ኪዳኑ የእኛን ድርሻ ማሟላት ካለብን ከእኛ ምን ይጠበቃል? ____________

10. የሚከተሉትን ዓረፍተ-ነገሮች አሟሉ፦

ሀ. በዚህ ቀን የአምላክ ________________________________________
በሰው ልጆች ላይ ፈስሰዋል።

ለ. በዚህ ቀን፣ የአምላክ ________________________________________
በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ውስጥ የናኘበት ነው።

ሐ. በዚህ ቀን፣ ልዩነቶቻችንን ____________________፣ ________________

________________________________________፣ በፍፁም አንድነትና

ሰላም ____________________________።

11. ባሃኦላህ የዓለም ሕዝቦችን እንዲያደርጉ የሚጠይቃቸው ምንድን ነው? ________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

## ምዕራፍ 4

አሌሃንድራ ከአቶ እና ው/ሮ ሳንቼዝ ጋር ልትካፈል ያቀደችው የጭብጥ ይዘት ብቻ አልነበረም በአዕምሮዋ ውስጥ የነበረው። ከጥንዶቹ ጋር ጠንከር ያለ የውዳጅነት ትሥሥር ለመመሥረት ተስፋ ታደርጋለች። ከቀደመ ልምድ፣ የከንቱ ጥላቻና የንቀት አመለካከት የከፉ ውጤቶችን ታውቃለች። እነዚህን ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ታስወግዳቸዋለች፤ የከፍተኛ ትምህርቷ ትህትናዋን አልቀነሰውም። ለሳንቼዞች ካላት ቅን ፍቅርና አክብሮት ውጭ በልቧ ውስጥ ምንም የላትም። የመጀመሪያውን ጭብጥ እንዴት ብላ እንደምትገልጽ ስታውጠነጥን፣ ይህ ለብዙ ሳምንታት የሚዘልቅ ቀጣይነት ያለው ጭውውት መጀመሪያ እንደሆነ እራስዋን ታሳስባለች። ተከታታይነት ያላቸውን ሃሳቦች በግልጽ ማቅረብ አስፈላጊ ቢሆንም፣ የጥንዶቹን ምላሽ ለማድመጥ አንዳንድ ነጥቦች ላይ ማቆም እንዳለባት ትገነዘባለች። "ላለመረበሽ መሞከር አለብኝ፣" ስትል ለራሷ ትናገራለች፣ "ምክንያቱም እኔ ማውራቴንና መናገሬን ስቀጥል፣ ጭውውቱ ቅርፁን የሚይዝበት ዕድል አይኖረውም።" አሌሃንድራ ስለጉብኝቷ በእነዚህ መንገዶች ለተወሰነ ግዜ ማሰቧን ትቀጥላለች። በእርሷ ቦታ ብትሆኑ፣ ወደ አዕምሮአችሁ መምጣት ያለባቸው ተገቢ አስተሳሰቦች ብላችሁ የምታዩት የትኛውን ነው?

_____ ሳንቼዞችን ስለእምነቱ ማስተማር እና የማስተምራቸውን ማንኛውንም ነገር መማራቸውን ማረጋገጥ የኔ ሥራ ነው።

_____ ከእነዚህ ድንቅ ጥንዶች ትንሽ ጊዜ ማሳለፍ እና ከቅዱሳን ጽሑፎች ምንባቦችን ከእነርሱ ጋር መካፈል መቻል እንዴት መታደል ነው።

_____ ይህ ጉብኝት አስፈላጊ እንደሆነ አውቃለሁ፣ ሆኖም፣ ረጅም ጊዜ እንደማይወስድ ተስፋ አደርጋለሁ ምክንያቱም የማደርጋቸው ሌሎች ነገሮች አሉኝ።

_____ ጥቅሶቹ ለእነሱ በጣም ከባድ ይሆኑባቸዋል:: ሁለት ቀላል ሃሳቦች ብቻ መጥቀስ ይኖርብኛል:: አስፈላጊው ነገር ለእነሱ ፍቅር ማሳየት ነው::

_____ በእነሱ ዕድሜ ሳንቼዞች ብዙ ሊማሩ አይችሉም::

_____ ጉብኝቱን እንዲሁም በጭብጦቹ ላይ ስንወያይና በጥቅሶቹ ላይ ስናሰላስል ዕይታዎቻቸ ውን ለመስማት በጉጉት እየጠበቅሁ ነው::

_____ ማንበብ ይችላሉ:: ርዕሱን ብቻ አስተዋውቃቸውና ጥቅሶቹን ለራሳቸው እንዲያጠኑ እተዋቸዋለሁ::

_____ ሃሳቦችን ሳቀርብ፣ ጥቅሶቹን በጋራ እንድናጠና እና ስለእነሱ መመካከር እንድንችል ብዙ ግዜ ቆም ማለት ይኖርብኛል::

_____ ሁሉንም ጭብጥ ያለማቋረጥ ማቅረብ እንደምችል ተስፋ አለኝ በመጨረሻም ጥያቄዎች እንዳላቸው መጠየቅ::

ለእንደዚህ ዓይነት ጉብኝት ለመዘጋጀት የምትፈልጉዋቸው ወይም የማትፈልጉዋቸው ሌሎች ስሜቶችን ልታስቡ ትችላላችሁን?

## ምዕራፍ 5

ወደ ሳንቼዝ ቤት የተደረገው የአሌሃንድራ የመጀመሪያ ጉብኝት በጥሩ ሁኒታ ተካሂዷል:: ጥንዶቹ መረበሿን በመገንዘባቸው በፍቅራቸውና በደግነታቸው ቀለል እንዲላት አድርገዋል:: ለጥቅሶች ልዩ ትኩረት በመስጠት፣ በጥሞና እያዳመጡ በውይይቱ ሙሉሉ ይካፈላሉ:: አስቸጋሪ የሆነው ብቸኛ ወቅት በስተመጨረሻ ወ/ሮ ሳንቼዝ ሳይታሰብ አሌሃንድራን ሲጠይቋት ነው፦ “የባሃኢ ማኅበረሰብን በመቀላቀሌ ክርስቶስን እየዘነጋሁ ነው ማለት ነው?” አሌሃንድራ መልሱን ታውቀዋለች፣ ነገር ግን መልሱን ለማቀናጀት ግዜ ይወስዳል:: አቶ ሳንቼዝ ፈገግ ይሉና ሊያግዟት ይመጣሉ፦ “ለክርስቶስ ያለኝ ፍቅር በዕርግጥ ያደገው ስለባሃኢ ትምህርቶች ከተማርንበት ጊዜ ጀምሮ ነው::” “በመላው ዓለም በብዙዎች ዘንድ መንገዱ ያው ነው፣” በማለት ሃሳቦችዋን በጋራ ያሰባሰበችው አሌሃንድራ ታክላለች:: “ለሙሴ፣ ክርስቶስ፣ ክሪሽና፣ ቡድሃ፣ ዞሮአስተር፣ እና ሙሐመድ ያላቸው ፍቅር የተጠናከረው ባሃኦላህ ስለ አምላክ አንድነት፣ስለ ሃይማኖት አንድነት፣ እና የሰው ዘር አንድነት ባስተማረው መንስዔነት ነው::”

በአሌሃንድራ ጉብኝት ወቅት ጉብኝቱን እጅግ ውጤታማ ለማድረግ መቅረብ የነበረባቸውን አንዳንድ መልካም ባህርያትና አመለካከቶች በቡድናችሁ ውስጥ ለመወያየት ትንሽ ግዜ መውሰድ ጠቃሚ ይሆናል:: ከእነዚያ መሃል ልታተኩሩበት የሚገባው ዋነኛው ትህትና ነው:: የትህትና ሁሉ መሠረት በአምላክ ፊት ትህትና ነው:: ከዚህ በእርሱ ፍጡራን ፊት ትሁት መሆን ይመነጫል:: አንድ ሰው ስለ አምላክና የእርሱ ክስተቶች ከሚናገርበት ጊዜ የበለጠ ትህትና አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ የለም:: በተከታዩ የባሃኦላህ ቃላት ላይ ማሰላሰል እና በቃላችሁ ለመያዝ እያንዳንዱን ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፦

**“እነርሱ የአምላክ ተወዳጆች የሆኑት፣ በማንኛውም ቦታ ሲሰበሰቡና ከማንኛውም ሰው ጋር ሲገናኙ፣ ለአምላክ ባላቸው ስሜት፣ የእርሱን ምስጋናና ውዳሴ በሚያቀርቡበትም ሁኔታ ምክንያት፣ ከእግሮቻቸው በታች የሚገኘው አቧራ እያንዳንዱ አቶም፣ ስለፍቅራቸው ጥልቀት**

**ይመሰክር ዘንድ፣ በጣም ከፍተኛ ትህትናና ታዛዥነት ማሳየት አለባቸው:: እነዚህ ቅዱሳን ነፍሶች ከሰዎች ጋር የሚያደርጉት ንግግር በሚያስተላልፈው ስሜት ምክንያት፣ እነዚህኑ የአቧራ አቶሞች በጥልቅ ስሜት እንዲነኩ እንዲያደርግ በከፍተኛ ኃይል የተሞላ መሆን አለበት:: በላይዋ የሚራመዱባት ምድር፦ "እኔ ከእናንተ የተሻልኩ ነኝ፣ ምክንያቱም፣ ገበሬው የሚጭንብኝን ሸክም ለመሸከም እንዴት ትዕግስተኛ እንደሆንኩ ተመልከቱ:: እርሱ የፀጋ ሁሉ ምንጭ የሆነው አደራ የጣለብኝን ቡራኬዎች፣ ለሕያዋን ሁሉ ያለማቋረጥ የማከፋፍለው መሣሪያ እኔ ነኝ:: የተሰጠኝ ክብርና የማይቆጠር ሃብት እያለኝ - የፍጥረትን ሁሉ ፍላጎት የሚያረካ ሃብት እያለኝ - የትህትናዬን ጥልቀት አስተዉሉ፣ በምን ዓይነት ፍፁም የሆነ ተገዢነት ራሴን በሰዎች እግሮች ሥር ለመረገጥ እንደፈቀድኩ ተመልከቱ፤..." የሚሉትን ቃላት እንድትናገራቸው እንዳይፈቀድላት፤ ራሳቸውን በጣም ከፍተኛ በሆነ ሥነ ምግባር መምራት አለባቸው::[4]**

ከላይ እንደተጠቀሰው፣ ከመሰላችን የሰው ልጆች ፊት የምናሳየው ትህትና የሚመነጨው ለአምላክ ካለን ትህትና ነው:: ስለአንዳንድ ጭብጦች ግንዛቤያችን በጋራ ለማጥለቅ የአንድ ወዳጅ ወይም የጎረቤት ቤት ስንጎበኝ በዚህ ዓይነት ትህትና ነው የፀሎት አኳኋን ውስጥ የምንሆነው:: በጭውውት ወቅት፣ አዕምሮአችንና ልባችንን እንዲሁም እነዚያ የተገኙትን ሁሉ አዕምሮና ልብ እንዲያበራ እርሱን በመማፀን፣ ሃሳቦቻችንን አዘውትረን ወደ አምላክ እንመልሳለን::  ይህን ዓላማ በአዕምሮአችን በመያዝ ከፀሎቶች ውስጥ በቃላችን ልንይዛቸው የምንችላቸው ሐረጎችና ዓረፍተ-ነገሮች አሉ:: እነዚህ ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው፦

**"ልቦቻችንን አብራልን፣ አስተዋይ ዓይኖችንና ንቁ ጆሮዎችን አድለን::"[5]**

**"ጌታ ሆይ! ወሰን አልባ ችሮታዎችህን አድለን፣ እንዲሁም የመርሆህ ብርሃን እንዲበራ ፈቃድህ ይሁን::"[6]**

**"የእውነተኛ ግንዛቤ በሮችን ክፈት እንዲሁም የእምነት ብርሃን በድምቀት እንዲበራ ፈቃድህ ይሁን::"[7]**

**"ጌታ ሆይ! ብርሃንህን ማየት እንድንችል ዓይኖቻችንን አብራልን::"[8]**

**"... በዚህ፣ በመለኮታዊ አንድነት ዘመን፣ ከአንተ ፈቃድ በተቃራኒ ከሚሄድ ሁሉ እንድትከልለኝ፣ በሙሉ ልቤ፣ አዕምሮዬ እና አንደበቴ በጋለ ስሜት እየተማፀንኩ፣ ሙሉለሙሉ ወደ አንተ ዞሬአለሁ::"[9]**

## ምዕራፍ 6

የሳንቼዞችን ቤት ከጎበኘች እና ከእነርሱም ጋር በዘለዓለማዊው ቃል-ኪዳን ጭብጥ ላይ ጭውውት ካደረገች በኋላ የአሌሃንድራ ልብ በደስታ ተሞልቷል:: "ቀጣዩ ጉብኝት፣ ስለ ባሃኦላህ ሕይወት ዕውቀታቸውን ለማጥለቅ መልካም አጋጣሚ ይሆንላቸዋል፣" ብላ ታስባለች:: እርሷ የምትጠቀምበት ገለፃ የሚከተለው ነው፦

ባሃኦላህ እ.ኤ.አ. ሕዳር 12 ቀን 1817 ዓ.ም በፋርስ ዋና ከተማ፣ በቴህራን ተወለደ:: ከልጅነቱ ጀምሮ የተለየ ባህርያት ያሳይ ነበር፣ እንዲሁም ቤተሰቦቹ ለታላቅ ተልዕኮ የታጨ እንደሆነ አምነው ተቀብለው ነበር:: የንጉሡ ቤተ መንግሥት ውስጥ የተከበሩ ሚንስትር የነበሩት

የባሃኦላህ አባት ለልጃቸው ጥልቅ ፍቅር ነበራቸው። አንድ ሌሊት በሕልማቸው ባሃኦላህ በአንድ ወሰን አልባ ውቅያኖስ ውስጥ ሲዋኝ አዩ፣ አካሉም ሰፊውን ባህር ያበራና ያንፀባርቅ ነበር። በጭንቅላቱ ዙሪያ ያለው ረጅም እንደ ሐር ጥቁር ፀጉሩ በሁሉም አቅጣጭ በመንሳፈፍ ፈንጥቋል። እያንዳንዱ የፀጉሩን ጫፍ በመያዝ አያሌ አሳዎች በዙሪያው ተሰባስበዋል። እንደ አሳዎች ቁጥር ትልቅነት፣ አንዲት ፀጉር እንኳን ከባሃኦላህ ጭንቅላት ላይ አልተለየችም። በነፃነትና ያለ ምንም ገደብ ይንቀሳቀስ ነበር፣ እናም ሁሉም ይከተሉታል። የባሃኦላህ አባት አንድ በጥበቡ የታወቀ ሰው ሕልሙን እንዲፈታላቸው ጠየቁ። ያ ወሰን አልባ ውቅያኖስ የኑባሬው ዓለም እንደነበር ተነገራቸው። ብቻውን ያለማንም ዕርዳታ፣ ባሃኦላህ የበላይነትን ይቀዳጃል። በርካታዎቹ አሳዎች በዓለም ሕዝቦች መካከል የሚያነሳውን ሁከት ይወክላል። የኃያሉ የማያቋርጥ ጥበቃ ይኖረዋል፤ ይህ ሁካት እርሱን አይጎዳውም።

ባሃኦላህ አሥራ ሦስት ወይም አሥራ አራት ዓመት በነበረበት ወቅት፣ በንጉሡ ቤተ-መንግሥት ውስጥ በጥበቡና ትምህርቱ የታወቀ ነበር። አባቱ ሲሞቱ ሃያ-ሁለት ዓመቱ ነበር፣ እናም መንግሥት የአባቱን ቦታ ባሃኦላህ እንዲይዝ ጥያቄ ቀረበለት። ነገር ግን እርሱ ዓለማዊ ጉዳዮችን ለማስተዳደር ጊዜውን የሚያውለው ግዜ አልነበረውም። በአምላክ ለእርሱ የተመደበለትን መንገድ ለመከተል ቤተ-መንግሥቱንና ሚኒስትሮቹን ወደኋላ ትቶ ሄደ። ግዜውን የተጨቆኑትን፣ የታመሙና ነዳያንን ለመርዳት አዋለ፣ ወዲያውም የፍትሕ ዓላማ አራማጅ በመባል ታወቀ።

ባሃኦላህ በሃያ-ሰባት ዓመቱ፣ በአንድ ልዩ መልዕክተኛ አማካይነት፣ የአዲስ ቀን ንጋትን፣ አዲስ የአምላክ ክስተት ለረዥም ዘመናት በሰው ልጅ ሲጠበቅ የነበረው ለዓለም ሰላም አንድነትና ፍትህ የሚያመጣበትን ግዜ ሲያውጅ የነበረውን የባብን ቅዱሳን ፅሑፎች ተቀበለ። ወዲያውኑ ባሃኦላህ የባብን መልዕክት ተቀበለ፣ ከትጉህ ተከታዮቹም አንዱ ሆነ። ነገር ግን ያሳዝናል፣ የፋርስ ሕዝብ መሪዎች፣ በእኔነት ስሜቶቻቸው ታውረው የባብን ተከታዮች በአሰቃቂ ጭካኔ ማሰቃየት ጀመሩ። ምንም እንኳን ባሃኦላህ ከተከበረ ቤተሰብ መሆኑን ቢታወቅም አልማሩትም። ከባብ እወጃ ከስምንት ዓመታት በኋላ፣ ወይንም ባብ እራሱ መስዋዕት ከሆነ ከሁለት ዓመታት በኋላ፣ ባሃኦላህ ጥቁሩ ጉድጓድ በተባለ የምድር በታች እስር ቤት ተጣለ። በአንገቱ ዙሪያ አሸክመውት የነበረው የብረት ሰንሰለት በጣም ከባድ ስለነበር ጭንቅላቱን ቀና ማድረግ አይችልም ነበር። ባሃኦላህ በከፍተኛ መከራ ውስጥ አራት አሰቃቂ ወራትን አሳለፈ። ይሁንና ነፍሱን የአምላክ መንፈስ የሞላውና ለዘመናት ሲጠበቅ የነበረው እርሱ እንደሆነ የተገለጸለት በዚህ እስር ቤት ውስጥ ነበር። ከዚህ ጨለማ ወህኒ ቤት፣ የባሃኦላህ ፀሐይ ፈንጥቃ በፍጥረት ሁሉ ላይ አንፀባረቀች።

በጥቁሩ ጉድጓድ አራት ወራት ካሳለፈ በኋላ፣ ንብረቱን ሁሉ ተገፎ  እርሱና ቤተሰቡ ለስደት ተዳረገ። በጣም ቀዝቃዛ በሆነው የክረምት ወራት በምዕራባዊው የፋርስ ተራራ በኩል በዚያን ጊዜ የኦቶማን ግዛት ከተማ የአሁኗ ኢራቅ ዋና ከተማ ወደሆነችው ባግዳድ ተጓዘ። ወደዚያች በዕድል የተሞላች ከተማ በበረዶ የተሸፈነውን ምድር ለማቋረጥ  በመቶዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን ሲጓዙ  የደረሰባቸውን መከራ ቃላት ሊገልፁት አይችሉም።

ወዲያው የባሃኦላህ ዝና በባግዳድና በአካባቢው ባሉ ሌሎች ከተሞች በመሠራጨቱ፣ ወደዚህ የተጋዘ እስረኛ ቡራኬ ለመቀበል ወደ እርሱ ደጃፍ የሚመጡ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መጣ። ነገር ግን ባሃኦላህ በጣም ታዋቂ በመሆኑ ቅናት ያደረባቸውም ጥቂት ሰዎች ነበሩ። ከእነዚህ

መካከል በባሃኦላህ ፍቅራዊ ጥበቃ ሥር ይኖር የነበረው የራሱ ግማሽ ወንድም ሚርዛ ያሕያ ነበር። የሚርዛ ያሕያ ሴራ በባብ ተከታዮች ዘንድ አንድነት እንዳይኖር አደረገ እናም በባሃኦላህ ላይ ትልቅ ሃዘን አመጣ። አንድ ለሊትም ለማንም ሳይናገር፣ ባሃኦላህ ቤቱን ትቶ ወደ ኩርዲስታን ተራሮች ሄደ። በዚያም ከማንም ሳይገናኝ የፀሎትና የሰባዔ ሕይወት አሳለፈ። በትንሽ ዋሻ ውስጥ በመኖር እጅግ ቀላል ምግቦችን ይጠቀም ነበር። ማንም ከየት እንደመጣና ማን ተብሎ እንደሚጠራ አያውቅም ነበር። ይሁንና ቀስ በቀስ የአካባቢው ሰዎች በአምላክ የተቸረ ዕውቀት ስላለው አንድ ታላቅና "ስም የለሽ" ፃድቅ ሰው ማውራት ጀመሩ። የዚህ ቅዱስ ሰው ዜና የባሃኦላህ ትልቁ ልጅ አብዱል ባሃ ዘንድ ሲደርስ የተወዳጁን አባቱን ምልክቶች ወዲያው አወቀ። ከልዩ መልዕክተኞችም ጋር ወደ ባግዳድ እንዲመለስ ባሃኦላህን የሚለምኑ ደብዳቤዎች ተላኩ። ይህንን ልመና በመቀበሉ ለሁለት ዓመታት የቆየው ህመም የበዛበት መለያየት አበቃ።

ባሃኦላህ ባልነበረባቸው ግዜያት የባቢ ማኅበረሰብ ሁኔታ በፍጥነት አሽቆልቁሎ ነበር። ከተራሮቹ መመለሱን ተከትሎ በባግዳድ ውስጥ በኖረባቸው ሰባት ዓመታት፣ ባሃኦላህ የተሰቃዩትንና ግራ የተጋቡትን የባብ ተከታዮች በአዲስ መንፈስ ሞላ። ምንም እንኳ እርሱ ገና የራሱን ታላቅ ደረጃ ያላወጀ ቢሆንም የቃላቱ ኃይልና ጥበብ ብዛት ያላቸው ባቢዎችን ታማኝነትና በተለያዩ የሕይወት ጎዳና ላይ የተሰማሩ ሰዎችን አድናቆት አተረፈ። ይሁንና አክራሪ የእስልምና ቀሳውስት እንደዚያ ብዛት ባላቸው ነፍሶች ላይ የሚያሳድረውን ከፍተኛ የመለወጥ ውጤት በዝምታ መመልከት አልቻሉም። ስለዚህም በተደጋጋሚ ለባለሥልጣናት ባሃኦላህን ከሰሱ፣ በመጨረሻም የፋርስ መንግሥት ከአንዳንድ የኦቶማን ግዛት ባለሥልጣናት ጋር በማበር ከትውልድ ሐገሩ ይበልጥ እንዲርቅ ቁስጥንጥንያ ወደተባለች ከተማ አጋዙት።

ለባግዳድ ሕዝብ እ.ኤ.አ.ሚያዝያ1863 ዓ.ም ታላቅ የሀዘን ወር ነበር። ከግዜ ወደግዜ እያፈቀሩት የመጡት ወዳጃቸው ከተማቸውን ለቅቆ ወደማያውቁት ቦታ ሊሄድ ሆነ። ባሃኦላህ ከተማዋን ከመልቀቁ ጥቂት ቀናት በፊት፣ ከባግዳድ ወጣ ብሎ በሚገኘው መናፈሻ ድንኳኑን ጥሎ ሊሰናበቱት የመጡትን ብዛት ያላቸው ሰዎች ለአሥራ ሁለት ቀናት ተቀበለ። የባብ ተከታዮች ወደዚያ መናፈሻ የሚሄዱበት በከፍተኛ ሀዘን ነበር፤ ጥቂቶቹ በቀጣዩ ግዞት አብረውት ይሄዳሉ፣ አብዛኞቹ ግን እዚያው ስለሚቀሩ ከዚያ በኋላ ከእርሱ ጋር የሚኖራቸውን ቅርብ ግንኙነት ያጣሉ። ይሁንና ይህ ግዜ የሀዘን እንዲሆን አምላክ አልፈቀደም። የእርሱ ወሰን የሌለው የቸርነቱ በሮች በሰፊው ተከፈቱ ፣ ባሃኦላህም በባብ የተነገረለት - እርሱ አምላክ የሚከስተው፣ እርሱ እንደሆነ በዙሪያው ለነበሩት አወጀ። ሀዘን ወሰን በሌለው ደስታ ተተካ፤ ልቦች ተነቃቁ ነፍሶችም በእርሱ ፍቅር እሳት ተለኮሱ። ይህ በሚያዝያ ወር ውስጥ ያለ የአሥራ ሁለት - ቀናት ግዜ በሁሉም አካባቢ ባሃኦላህ ዓለምን የሚያቅፍ ተልዕውን ያወጀበት ክብረ በዓል፣ የሪዝቫን ፌስቲቫል/በዓል ይከበራል።


ቁስጥንጥንያ የኦቶማን ግዛት ዋና ከተማ ነበረች። የባሃኦላህ ጥበብና ግርማ እዚያም ቢሆን፣ በአራት ወራት ብቻ፣ ብዙ ሰዎችን መሳብ ጀመረ። "በቁስጥንጥንያ ከዚህ በላይ መቆየት የለበትም፣" ሲሉ አክራሪዎቹ የእስልምና ቀሳውስት አጉረመረሙ፣ ባለስልጣናቱን ካሳመኑት በኋላ ወደ አድርያኖጽሎስ ከተማ እንደገና አጋዙት። ለአራት ተኩል ዓመታት በቆየባት በአድርያኖጽሎስም፣ የጭቆና አሠራራቸውን ትተው ለሕዝቦቻቸው ዕድገት እራሳቸውን እንዲሰጡ ጥሪ በማድረግ ለዓለም ነገሥታትና መሪዎች ፅላቶችን ገለጸ። ከዚህ በኋላም ጠላቶቹ እጅግ በጣም ጭካኔ የተሞላው ቅጣት አውጠነጠኑ። በዚያን ግዜ በመላው በኦቶማን ግዛት

ውስጥ ካሉት ሁሉ እጅግ አስከፊ ወደነበረው የአቆር የእስር ከተማ ከነቤተሰቡ ይጋዛሉ። “የእስር ከተማውን አስከፊ ሁኔታ መቋቋም ስለማይችል በዕርግጥ እዚያው ይሞታል፣” በማለት አምላክ እራሱ ያንቀሳቀሰውን ዕቅድ እነዚህ ጠባብ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ሊያቆሙት እንደሚችሉ አስበው ነበር።

ባሃኦላህ በአቆር የደረሰበት ችግር ብዙ ከመሆኑ የተነሳ ለመግለጽ አዳጋች ናቸው። ማንኛውንም ዓይነት ምቾት የተነፈገና ቀንም ማታም በጠላቶቹ የተከበበ ነበር። ይሁንና የእስሩ ሁኔታ ቀስ በቀስ እየተለወጠ መጣ። የአቆር ነዋሪዎችና መንግሥት ወደ ከተማቸው የተጋዙት ጥቂት ባሃኢዎች ወንጀል የሌለባቸው መሆናቸውን እያመኑበት ሄዱ። ምንም እንኳን አብዛኛው ሕዝብ የባሃኦላህን ታላቅ ደረጃ ባይረዱም አሁንም ብዙ ሰዎች በእርሱ የተለየ ስብዕና ጥበብና ፍቅር መሳብ ጀመሩ። ከጥቂት ዘጠኝ ዓመታትም በኋላ የእስር ከተማው በሮች ለባሃኦላህና ለተከታዮቹ ክፍት ሆኑ። ተወዳጅ ልጁ አብዱል-ባሃ ከከተማው ግድግዳዎች ውጭ አባቱ የሚኖርበት ደረጃውን የጠበቀ ቦታ ለማግኘት ችሎ ነበር፣ በመጨረሻም ባሃኦላህ የሕይወቱን ቀሪ አሥራ ሦስት ዓመታት በተሻለ ሰላምና ዕርጋታ ሊያሳልፍ የሚችልበትን ቦታ በገጠር ውስጥ ያለ ቤት ሊከራይለት ቻለ። አሁን ይህን ቤት የባሃጂ ማንሽን/ እልፍኝ በማለት እናውቀዋለን፣ በዚያም በከፍተኛ ክብርና ግርማ እየኖረ ሳለ እ.ኤ.አ. በግንቦት ወር 1892 ዓ.ም ከዚህ ዓለም ተለየ።

ባሃኦላህ የዓለም አቀፍ ሰላምና ወንድማማችነትን ሰንደቅ ከፍ አድርጓል እንዲሁም የአምላክን ቃል ገልጿል። ምንም እንኳን ጠላቶቹ ኃይላቸውን አስተባብረው ቢነሱበትም፣ በቴህራን በሠንሠለት ታሥሮ በነበረበት ወቅት አምላክ ቃል እንደገባለት በጠላቶቹ ላይ ድልን አግኝቷል። በራሱ የሕይወት ዘመን የእርሱ መልዕክት የብዙ ሺህ ሰዎችን ልቦች አነቃቅቷል። ዛሬም የእርሱ ትምህርት በዓለም ዙሪያ መሠራጨቱን እንደቀጠለ ነው። የሰውን ዘር በአንድ ዓለም አቀፍ እምነት፣ አንድ የጋራ ሃይማኖት አንድ ማድረግ የሆነውን የመጨረሻ ግቡን ሳይቀዳጅ ምንም ሊገታው አይችልም።

ከላይ የተሰጠው የባሃኦላህ ታሪክ በንፅፅር ረዥም ነው። ከዚህ በታች ወደሚገኙት መልመጃዎች ከማለፋችሁ በፊት፣ በቡድናችሁ ውስጥ ታሪኩን አንቀጽ በአንቀጽ አንብቡና ይዘቱን በደንብ እስክትረዱ እና በቀላሉ ማቅረብ እስክትችሉ ድረስ፣ እርስ በእርስ ጥያቄዎችን መጠየቅ አለባችሁ። ተከታዩ ካርታ የባሃኦላህን የግዞት መንገድ ወደ አዕምሯችሁ እንዲመጣና በመንገዶቹ ላይ የተፈጠሩትን ክስተቶች ለማስታወስ ይረዳችኋል።




1. ከላይ ባለው ታሪክ ላይ በመመሥረት በተሠጡት ባዶ ቦታዎች ከባሃኦላህ ሕይወት ጋር የተያያዙ ዋና ዋና ክስተቶች ቅደም ተከሎችን መፃፍ ጠቃሚ ሆኖ ልታገኙት ትችላላችሁ።

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

2. የባሃኦላህ ሕይወት ጭብጦች ዙሪያ በሚደረጉ ውይይቶች ውስጥ፣ ከተከታታይ ክስተቶች በተለይ ሊሠመርባቸው/ሊተኮርባቸው የሚገቡ በርካታ ፅንሰ-ሃሳቦች አሉ። በተለይ አስፈላጊ የሆነው ለሰው ልጅ ካለው ፍቅር የተነሳ የተቋቋመው መከራ፣ እንዲሁም በተቃውሞ መሃል በእምነቱ የተቀዳጃቸው ድሎች ላይ ማሰላሰል ነው። እስቲ እነዚህ ቃላት በአዕምሯችን እና ልባችን ላይ ይቀረጹ፦

**"ጥንታዊው ውበት የሰው ልጅ ከእሥረኝነቱ ነፃ ይወጣ ዘንድ በብረት ሠንሠለት ለመታሠር ፈቀደ፣ እንዲሁም መላው ዓለም እውነተኛ ነፃነት ይቀዳጅ ዘንድ በዚህ እጅግ በጣም ብርቱ ምሽግ ውስጥ እሥረኛ መሆንን ተቀበለ። የምድር ሕዝቦች ሁሉ ዘላቂ ፍስሐን ይቀዳጁ፣ በደስታም የተሞሉ ይሆኑ ዘንድ፣ የኃዘንን ፅዋ እስከመጨረሻዋ ጠብታ ጨለጠ። ይህ ከሩህሩሁ፣ ከእጅግ በጣም መሃሪው፣ ጌታችሁ ምህረት የተነሳ ነው። በአምላክ አንድነት አማኞች ሆይ፣ እናንተ ትከበሩ ዘንድ መዋረድን፣ እናንተ ትበለጽጉና ታብቡ ዘንድ ብዙ ከባድ መከራዎችን ተቀብለናል። እርሱን መላውን ዓለም በአዲስ ይገነባ ዘንድ የመጣውን፣ እነዚያ ከአምላክ ጋር ራሳቸውን ያወዳደሩት ከከተሞች እጅግ በጣም ባድማ በሆነው ከተማ ውስጥ እንዲኖር እንዴት እንዳስገደዱት ተመልከቱ!"**[10]

3. ስለባሃኦላህ መከራ በምንናገርበት ወቅት፣ አቅመ ቢስ የጠላቶቹ ሰለባ እንደሆነ አድርገን ላለማቅረብ መጠንቀቅ ይኖርብናል። የሰው ልጅ ነፃ ይሆን ዘንድ በሠንሠለት መታሠርን በገዛ ፍቃዱ ተቀበለ። የሕይወት ታሪኩ፣ ምንም እንኳን በመከራ የተሞላ ቢሆንም፣ በመሠረቱ የድል ታሪክ ነው። ስለእርሱ ሕይወት እስከአሁን ባላችሁ ዕውቀት ላይ በመመርኮዝና በቡድናችሁ አስጠኚ ዕርዳታ በባሃኦላህ ላይ ስለደረሱት መከራዎችና ስለ ተቀደጃቸው ድሎች አጭር ንግግር አዘጋጅታችሁ ማቅረብ ትችላላችሁ? ከሥር ያሉት ጥያቄዎች ሊያግዟችሁ ይችላሉ።

ሀ. ባሃኦላህ ለምን በብረት በሠንሠለት መታሠርን ፈቀደ? ____________________

ለ. ባሃኦላህ ለምን እሥረኛ መሆንን ተቀበለ?____________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

ሐ. ባሃኦላህ ለምን የሐዘንን ፅዋ ጠጣ?________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

መ. ባሃኦላህ ለምን ውርደትን ተቀበለ?________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

ሠ. ባሃኦላህ ለምን ብዙ መከራዎች ደረሱበት?____________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

ረ. ባሃኦላህ መከራን የተቀበለው ሌላ ምንም ማድረግ የማይችል አቅመ ቢስ ስለነበረ ነውን? _

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

ሰ. ባሃኦላህ በጠላቶቹ ፊት አቅመ ቢስ ካልነበረ፣ መከራን ለምን ተቀበለ? ________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

## ምዕራፍ 7

አሌሃንድራ ወደእነ ሳንቼዝ ቤት ያደረገችው ሁለተኛ ጉብኝት እንደመጀመሪያው አስደሳች ነው፡፡ አቶ እና ወ/ሮ ሳንቼዝ ከባሃኦላህ ሕይወት ታሪክ ጋር ቀድሞውኑ በተወሰነ ደረጃ እየተዋወቁ ናቸው፣ ነገር ግን አሌሃንድራ ከምታቀርበው ይበልጥ መማር ያስደስታቸዋል በግልጽ እንደሚታየውም በመከራዎቹ ታሪክ ተነክተዋል፡፡ በአንድ ነጥብ ላይ ወ/ሮ ሳንቼዝ ስታሰላስል፣ “የአምላክ ክስተቶች ሁሌም የሚሰቃዩት በእነዚያ መሪነትና ዓለማዊ ሥልጣን በሚጠሙ እጆች ይመስላል፡፡” አሌሃንድራ በቃል የያዘችውን - እናንተም፣ ከባለፈው ምዕራፍ ጥናታችሁ የምታውቁትን - ባሃኦላህ ለሰው ልጅ ሲል፣ ማለትም ከጭቆና ነፃ እንድንወጣና ዘላቂ ደስታ እንድንቀዳጅ የቻለውን መከራ የሚናገርበትን ጥቅስ ማካፈል ተገቢ እንደሆነ ትወስናለች፡፡ ሦስቱ ጓደኛሞች በዚያ ዕለት ባደረጉት ውይይት መነቃቃት ተሰምቷቸዋል፡፡

ቀጣዩን ጉብኝትዋን ስታሰላስል፣ የአብዱል-ባሃን ደረጃ ለውይይት ማቅረብ ተፈጥሯዊ ጭብጥ እንደሚሆን አሌሃንድራ ወዲያውኑ ትደመድማለች። ልትሸፍን የምትፈልጋቸው ነጥቦች እነዚህ ናቸው፦

የባሃኦላህ የበኩር ልጅ፣ አብዱል-ባሃ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ እጅግ በጣም የተለየ ስብዕና ነው፣ እንዲሁም በማንኛውም ባላፉት ሃይማኖት እርሱን የመሰለ የተከበረ ሰው ልናገኝ አንችልም። ገና ልጅ እያለ የአባቱን መለኮታዊ ደረጃ ተገንዝቦ ነበር እናም ግዞቶቹንና መከራዎቹን ተካፍሏል። ባሃኦላህ ከእርሱ ሕልፍት በኋላ የባሃኢ ማኅበረሰብን የተወው በአብዱል-ባሃ ጥበቃና ከለላ ሥር ነበር። ባሃኦላህ እጅግ በጣም የላቀ ግልፀቱን ብቻ ሳይሆን በእርሱ ዕውቀትና ጥበብ አማካይነት ዓለም ልትመራና ልታንፀባርቅ የምትችልበትን ልጁንም ጭምር ለሰው ልጅ በመስጠቱ ምን ዓይነት ሰፊ ቸርነት እንደለገሰን ለመረዳት ፈፅሞ ያዳግተናል።

የአብዱል-ባሃን ሕይወትና ንግግሮች ስናጠና፣ በዚህ ግልፀት ዘመን እርሱ የሚይዘውን የተለየ ደረጃ ጥልቅ ዕይታ እናገኛለን። የዚህ ደረጃ ሦስት ገፅታዎች በአዕምሯችን መያዝ አስፈላጊ ናቸው።

አንደኛ፣ አብዱል-ባሃ የባሃኦላህ ቃል-ኪዳን ማዕከል ነው። ባሃኦላህ ልባቸውን ወደዚያ ማዕከል እንዲያዞሩና ሙሉለሙሉ ታማኝ እንዲሆኑለት ጥሪ በማድረግ ከተከታዮቹ ጋር ቃል-ኪዳን ገብተዋል። አብዱል-ባሃ በቃለ ኑዛዜው፣ የእምነቱ ሞግዚት፣ ሾጊ ኤፌንዲ፣ ከእርሱ ሕልፈት በኋላ ሁሉም ወደ እርሱ መዞር ያለበት ማዕከል እንዲሆን ሰይሞታል። ዛሬ፣ ይህ ማዕከል በባሃኦላህ ግልጽ ትዕዛዝ እንዲሁም በአብዱል-ባሃና ሞግዚቱ በተሰጡ ግልጽ መመሪያዎች የተመሠረተው፣ ዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትሕ ነው። የቃል-ኪዳኑ ኃይል የባሃኢ ማኅበረሰብን በጋራ ያስተሳስራል እንዲሁም ከመከፋፈልና መበታተን ይጠብቀዋል።

ሁለተኛ፣ አብዱል-ባሃ የባሃኦላህ ቃላት የማይሳሳት ተርጓሚ ነው። የባሃኦላህ ግልፀት በጣም ሰፊ ነው፣ በእርሱ ንግግሮች ውስጥ የተሸሸጉት ትርጉሞች በጣም ጥልቅ ናቸው፣ ስለሆነም እርሱ ራሱ መንፈሳዊ መነቃቃቱን የሚለግሰው ተርጓሚ ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግ አመነበት። ስለዚህ፣ ለሚመጡት ትውልዶች፣ የሰው ልጅ የባሃኦላህን ትምህርቶች ለመገንዘብ የሚችለው በእርሱ አያሌ ፅላቶችና የንግግሮቹ እውቅና የተሰጣቸው ጽሑፎች ውስጥ የሚገኙትን የአብዱል-ባሃን ትርጉሞች በማጥናት ይሆናል። ከአብዱል-ባሃ በኋላ የባሃኦላህ ትምህርቶች ተርጓሚ ሞግዚቱ ነበር፤ የመተርጎም ሥራ እርሱ ላይ ተጠናቋል፣ እናም የባሃኦላህን ቃላት በቀሪዎቹ የግልጸቱ ወቅት ለመተርጎም ማንም ሥልጣን አልተሰጠውም።

ቀደም ባሉት ግዜያት፣ እያንዳንዱ ሃይማኖት ከቅዱሳን ጽሑፋቸው ምንባቦች የተለያየ አተረጓጎም ላይ የተመሠረቱ ክፍፍሎች ሰለባ ሆነዋል። በዚህ ግልፀት ዘመን ግን፣ ስለ ባሃኦላህ ቃል ትርጉም አሻሚ ነገር ሲኖር፣ እያንዳንዱ ሰው ወደ አብዱል-ባሃና ሞግዚቱ ትርጎሞች ይዞራል። ጥርጣሬው ከቀጠለ፣ አንድ ሰው ለማብራሪያ ወደ ዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትሕ መዞር ይችላል። ስለዚህ፣ በትምህርቶቹ ትርጉም ላይ ለመጋጨት ምንም ክፍተት የለም፣ የእምነቱ አንድነትም የተጠበቀ ነው።

ሦስተኛ፣ አብዱል-ባሃ የአባቱ ትምህርቶች ፍፁም አርአያ ነው። እንዲህ ወዳለው ፍፁምነት ደረጃ ለመድረስ ፈፅሞ ተስፋ ባናደርግም፣ ከአይኖቻችን ፊት እርሱ እንዲኖርና የእርሱን አርአያነት ለመከተል ሁሌም መጣር ይኖርብናል። ስለ ፍቅር በቅዱሳን ጽሑፎቹ ውስጥ

ስናነብ፣ ወደ አብዱል-ባሃ መዞር እንችላለን ፤ የፍቅርና ደግነት ትክክለኛ ምንነት እናያለን። ስለ ንፅህና፣ ፍትኅ፣ ቀጥተኛነት፣ ደስታና ልግሥና ስናነብ፣ ወደ እርሱ በመዞር ስለሕይወቱ ልናስብ እንችላለን፣ እናም እነዚህን ባህርያት በላቀ ፍፁምነት እርሱ እንዴት እንደሚገልፃቸው እንመለከታለን።

በዕርግጥ የአብዱል-ባሃ ሕይወት ምልክት፣ አገልጋይነቱ ነበር። አብዱል-ባሃ የሚለው ስም "የባሃ አገልጋይ" ማለት ነው፣ እናም ለእርሱ ከተሰጡት ከሌሎች ማዕረጎች የመረጠው ይህን ነበር። የሚከተሉት የአብዱል-ባሃ ቃላት ለማገልገል ያለውን ፅኑ ፍላጎት የሚያብራሩ መግለጫዎች ናቸው፦

**"ስሜ አብዱል-ባሃ ነው። ብቁነቴ አብዱል-ባሃ ነው። እውነነቴ አብዱል-ባሃ ነው። ውዳሴዬ አብዱል-ባሃ ነው። ለተባረከው ፍፁምነት አገልጋይነት የኔ የተከበረና አንፀባራቂ አክሊል ነው፣ እንዲሁም መላውን የሰው ዘር ማገልገል የማያቋርጥ ሃይማኖቴ ነው... ከአብዱል-ባሃ በቀር፣ ምንም ሥም፣ ምንም ማዕረግ፣ ምንም መጠሪያ፣ ምንም ውዳሴ የለኝም፣ ወድፊትም አይኖረኝም። ይህ ነው ናፍቆቴ። ይህ ነው እጅግ በጣም ታላቁ ጉጉቴ። ይህ ነው ዘለዓለማዊ ሕይወቴ። ይህ ነው ዘለዓለማዊ ክብሬ።"**[11]

አሌሃንድራ በቀጣዩ ጉብኝቷ ከከሳንቼዞች ጋር ለመካፈል በግልፅ ያቀደችው እጅግ በጣም ልዩ ስብዕና የሆነውን ከማስተዋወቅ የዘለለ አይደለም፤ በዚህ ግልፀት ዘመን ውስጥ አብዱል-ባሃ የያዘውን ደረጃ ማድነቃቸው በመጪዎቹ ዓመታት ማደጉን ይቀጥላል። የአገልግሎት ጎዳናን ስትጓዙ፣ በራሳችሁ ሕይወት ውስጥ፣ የእርሱ ምሳሌ ወደ አዕምሯችሁ እንዲመጣና በቃላቱ ላይ እንድታሰላስሉ ብዙ ዕድሎች ይኖራችኋል። ቀድሞውኑ፣ ባለፈው ክፍል ውስጥ፣ ከእርሱ ንግግሮች ከአንዳንዶቹ ጋር ራሳችሁን እንዳስተዋወቃችሁ፣ እንዲሁም በእርሱ ፅላቶች እና ህዝባዊ መድረክ ንግግሮች ውስጥ ባንፀባረቃቸው ሃሳቦች መሠረት መግለጽ እንድትማሩ ትበረታታላችሁ። ለአሁኑ፣ የእርሱን ደረጃ አሁናዊ ግንዛቤያችሁን ለማጠናከር፣ ከላይ የተገለፁትን አብይ ነጥቦች ከቡድናችሁ ሌሎች አባላት ጋር መመካከር እና በደንብ መናገር መለማመድ ይኖርባችኋል። በተጠቀሰው ምንባብ ላይ ማሰላሰል የአገልግሎት ጎዳና ላይ ለመገስገስ በምታድርጉት ጥረቶች ውስጥ ያነቃቃችኋል።

## ምዕራፍ 8

ወደ አቶና ወ/ሮ ሳንቼዝ ጉብኝቶችን ማድረግ ከጀመረችበት ግዜ ጀምሮ በአሌሃንድራ አዕምሮ የነበረው ጥያቄ በአጎራባች ሠፈር ውስጥ የሚካሄደውን የማኅበረሰብ ግንባታ ፅኑና ንቁ አንቀሳቃሽ እንዲሆኑ ይበልጥ የሚረዳቸው የውይይት ጭብጦች ምንድን ናቸው የሚለው ነው። በአንድ በኩል፣ ከእነርሱ ጋር ለመወያየት የምታስበው እንደ ፀሎት፣ የነፍስ ዘለዓለማዊነት፣ እና በአምላክ ፍቅር መፅናት የመሳሰሉ ጭብጦች አሉ፣ ምክንያቱም የመንፈሳዊ ሕይወታቸው መሠረት ያለማቋረጥ መጠናከር አለበት። በሌላ በኩል፣ ቀስ በቀስ እየተገነባ ያለውን የማኅበረሰብ ዓይነት ራዕይ እንዲያገኙ እና ለተግባራዊነቱም ጠቃሚ የሆኑ አስተዋፅዖዎችን ሊያበረክቱ እንደሚችሉ ማወቃቸው አስፈላጊ ይሆናል። ስለ አብዱል-ባሃ ደረጃ ከአቶና ወ/ሮ ሳንቼዝ ጋር ጭውውት በምታደርግበት ወቅት፣ አሌሃንድራ የቀጣይ ጉብኝቷ ጭብጥ ምን መሆን እንደሚገባው ቀስ በቀስ መገንዘብ ትጀምራለች። "እምነቱ ስላለው ሰዎችን የማዋሃድ ዓላማ ከፍ ያለ ግንዛቤ አላቸው፣" ብላ ታስባለች። "ስለዚህ፣ ምናልባት አሁን መመርመር የሚገባን ጭብጥ የተዋሃደ ማኅበረሰብ እንዴት እንደምንገነባና እንደምናስጠብቅ ነው።"

አሌሃንድራ አራተኛ ጉብኝቷን የምትጀምረው በአጎራባች ሠፈሩ ውስጥ በአነስተኛ የወዳጆች ቡድን በአሁኑ ግዜ የሚካሄዱትን ዕንቅስቃሴዎች በመግለጽ ነው። "ቁጥራችን እየጨመረ ሲሄድ፣ ሁላችንም ልንሸከመው የሚገባን እጅግ በጣም ተገዳዳሪ ኃላፊነት በቃላቶቻችን፣ በአስተሳሰቦቻችን፣ እና በተግባሮቻችን ውስጥ ይበልጥ የተዋሃድን መሆን ነው፣ ስትል ትገልፃለች። ታዲያ፣ በዚህ ከተስማማችሁ፣ ዛሬ አንድነት የሚለውን ጭብጥ በጋራ እንፈትሻለን።"

"አንድነት ለማኅበረሰባችን ዕድገት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ማየት እችላለሁ፣" ስትል ወ/ሮ ሳንቼዝ ትመልሳለች።

"ከምንም ነገር በላይ ልባችንን ወደ ትምህርቱ የሳበው የባሃኦላህ የአንድነት መልዕክት ነበር፣" ይላል አቶ ሳንቼዝ።

"በዛ ያሉ ሃሳቦችን መርጫለሁ ለእያንዳንዱም የሚሆን ጥቅስ አግኝቻለሁ፣"ትላለች አሌሃንድራ። "ከተስማማችሁ፣ አንድ በአንድ ልንሄድባቸውና ልንወያይባቸው እንችላለን።"

የአሌሃንድራ ሃሳቦች ዝርዝር ከሥር ቀርቧል፦

- ማኅበረሰባችን በእውነት አንድ እንዲሆን፣ እያንዳንዳችን ውዝግብና ጭቅጭቅን ማስወገድ አለብን። ባሃኦላህ እንዲህ ይላል፦

  **"በዚህ ቀን፣ በአምላክ ተወዳጆች መካከል፣ እንደአለመግባባትና ውዝግብ፣ እንደጭቅጭቅ፣ እንደመቃቃርና እንደመጨካከን፣ ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ እምነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ምንም ነገር የለም። በአምላክ ኃይልና በእርሱ ሉዓላዊ ዕርዳታ ሽሹአቸው፣ በእርሱም፣ በአዋሐጁ፣ በሁሉን አዋቂው፣ በፍፁም ጠቢቡ ስም የሰዎችን ልቦች ለማስተሳሰር ተጣጣሩ።"**[12]

- በማኅበረሰቡ ውስጥ ላሉት ለእያንዳንዱ ሰው፣ ለአምላክ ያለን ፍቅር የሚንፀባረቅበት ፍቅር ሊኖረን ይገባል። አብዱል-ባሃ እንዲህ ይላል፦

  **"ፍፁም የሆነ አንድነት ይኑራችሁ። አንዱ በሌላው ፊፅሞ ቁጡ አይሁን... ፍጡሮችን ለእነርሱ ብላችሁ ሳይሆን ለአምላክ ስትሉ አፍቅሩ። ለአምላክ ብላችሁ የምታፈቅሯቸው ከሆናችሁ ልትቆጡ ወይም ትዕግሥት ልታጡ ከቶ አትችሉም። ሰው ፍፁም አይደለም። በእያንዳንዱ የሰው ልጅ ጉድለቶች አሉ፣ እና ሰዎቹን ራሳቸውን ከተመለከታችሁ ሁልግዜ ደስታ ያጣችሁ ትሆናላችሁ። ነገር ግን ወደ አምላክ ከተመለከታችሁ፣ታፈቅሯችዋላችሁ እንዲሁም ደጎች ትሆኑላችዋላችሁ፣ ምክንያቱም የአምላክ ዓለም ፍፁም የሆነና የተሟላ የምህረት ዓለም ነውና። "**[13]

- አንዳችን ለሌላችን በሚኖረን ፍቅር፣ በመካከላችን ውጥረቶች ቢፈጠሩ፣ ይህን የአብዱል-ባሃ ምክር ወዲያውኑ ማስታወስ ይኖርብናል፦

  **"እያንዳንዳችሁ የልባችሁ ሃሳቦች ሁሉ በፍቅርና በአንድነት ላይ እንዲያተኩሩ እንድታደርጉ ሁላችሁንም እጠይቃችኋለሁ። የጦርነት ሃሳብ ሲመጣባችሁ ይበልጥ ጠንካራ በሆነው የሠላም ሃሳብ ተቃወሙት። የጥላቻ ሃሳብ ይበልጥ ኃይል በተመላው የፍቅር ሃሳብ መደምሰስ አለበት። የጦርነት ሃሳቦች በስምምነት፣ በደህንነት፣ በዕረፍትና በዕርካታ ሁሉ ላይ ጥፋትን ያመጣሉ።**

**“የፍቅር ሃሳቦች ወንድማማችነትን፣ ሠላምን፣ ወዳጅነትንና ደስታን ለማጠናከር ገንቢዎች ናቸው።”[14]**

- እናም፣ እነርሱን ለመቆጣጠር እያንዳንዱን ጥረት ካደረግን በኋላ፣ ጥልቅ ስሜቶቻችን ሲያሸንፉንና ራሳችንን ከሌሎች ጋር ስንጋጭ ካገኘነው፣ እነዚህን የባሃኦላህ ቃላት ለራሳችን ማስታወስ ይኖርብናል፦

**“በመካከላችሁ ማንኛውም ልዩነት ቢነሳ፣ ከፊታችሁ እንደቆምኩ ተመልከቱኝ፣ ለእኔም ስም ብላችሁ ለግልፁና ለአንፀባራቂው እምነቴም ላላችሁ ፍቅር ምልክት ይሆን ዘንድ፣ የእርስ በርሳችሁን ስህተቶች አትመልከቱ።”[15]**

- በአስመስጋኝ ባህርያቶቻቸው ላይ በማተኮርና ከሐሜት ሙሉለሙሉ በመታቀብ፣ የሌሎችን ስህተቶች ያለመመልከት መንፈሳዊ ስነሥርዓት መከፋፈልን የሚያስወግድ እጅግ በጣም ውጤታማ እርምጃ ነው። አንዳችን ሌላችንን ስናፈቅር ለሐሜት ያለንን ዝንባሌ ለማሸነፍ ቀላል ነው። የእነዚያን የምናፈቅራቸውን ስህተቶች ላለማየት እንደምንጥር እንዲሁም ኃጢዓትን በሚሸፍን ዓይን ለመመልከት እንደማንቸገር ልናስታውስ ይገባል። አብዱል-ባሃ እንዲህ ይላል፦

**“ጉድለት ያለበት ዓይን ጉድለቶችን ያያል። ስህተቶችን የሚሸፍን ዓይን ወደነፍሶች ፈጣሪ ይመለከታል። እርሱ ፈጠራቸው፣ ያሠለጥናቸዋል፣ የሚያስፈልጋቸውንም ያድላቸዋል፣ ችሎታንና ሕይወትን፣ ማየትን እንዲሁም መስማትን ያጎናፅፋቸዋል፤ ስለዚህ፣ እነርሱ የታላቅነቱ መልክቶች ናቸው። ሁሉንም ሰው ማፍቀርና ለሁሉም ደግ መሆን፣ ድሆችን መንከባከብ፣ ደካማውን መጠበቅ፣ ለታመሙት ፈውስ መሻት፣ ዕውቀተ ቢሶችን ማስተማርና ማሠልጠን አለባችሁ።”[16]**

ባሃኦላህ እንዲህ ይመክረናል፡-

**“የዙፋኔ ጓደኛ ሆይ! እርኩስ ነገር አትስማ፣ እርኩስ ነገርም አትይ፣ ራስህን አታዋርድ፣ እንዲሁም አትዘን፣ አታልቅስ። እርኩስ ነገር አትናገር፣ በአንተም ላይ ሲነገር እንዳትሰማ፣ የሌሎችን ስህተት አታጉላ። የራስህ አይሎ እንዳይታይብህ፤ የማንንም ውርደት አትመኝ፣ የራስህ ወራዳነት እንዳይገለጽብህ። እንግዲህ በነፃነትና በዕርካታ ይህንን ሟች አካል ጥለህ ወደ ረቂቋ ገነት ተመልሰህ በማይጠፋው መንግሥት ለዘላለም ትኖር ዘንድ፣ ከመቅፅበት ከሚያልፍ ግዜ ያነሱትን የሕይወትህን ቀኖች በአፅምሮ እንክን አልባ በልብህ የልጎደፍህ፣ በሃሳብህ ንፁህ፣ በተፈጥሮህም የተቀደስክ ሆነህ ኑር።”[17]**

እንደገናም እንዲህ ይነግረናል፦

**“ስደተኞች ሆይ! እኔን እንድታነሱበት የፈጠርኩትን አንደበት በዘለፋ አትርክሱት። የእኔነት እሳት ቢያሸንፋችሁ፣እያንዳንዳችሁ ሌላውን ከማወቅ ይበልጥ ራሳችሁን በተሻለ ስለምታውቁ፣ የራሳችሁን ጉድለቶች እንጂ የፍጡራኔን ጉድለቶች አታስታውሱ።”[18]**

- አንድነት የውዝግብና የአለመግባባት አለመኖር ብቻ አይደለም። ፍቅርም የሚገለፀው በቃላት ብቻ አይደለም። በባሃኢ ማኅበረሰባችን እውነተኛ ፍቅር አለ ብለን ልንመካ የምንችለው አንዱ

ለሌላው ያለው ፍቅር በግልጋሎት ሲተረጎምና ዕንቅስቃሴዎቻችን በመተባበር እንዲሁም እርስ በእርስ በመረዳዳት መንፈስ ሲታቀፉ ነው። አብዱል-ባሃ እንዲህ ጥሪ ያቀርብልናል፦

**"ለቅጽበትም ቢሆን እንኳን አትረፍ፣ ለአፍታም ቢሆን እንኳን ድሎትን አትሻ፤ ይልቁንም ከወዳጆች መካከል ለአንዱ ብቻም ቢሆን መስዋዕትነት የተመላው ግልጋሎት ለመስጠት ትችል ዘንድ እንዲሁም ለአንድ ብሩህ ልብም ብቻ ቢሆን ደስታና ሐሴት እንድታመጣ በልብህና ነፍስህ ተጣጣር። ይህ እውነተኛ ችሮታ ነው፣ በዚያም የአብዱል-ባሃ ግንባር ይበራል። በዚህም ውስጥ የኔ አጋርና ተባባሪ ሁን።"[19]**

እንደገናም እንዲህ ይላል፦

**"ለሰው ልጅ ከሁሉም በላይ የሚያስፈልገው ትብብርና መደጋገፍ ነው። በሁሉም የሰው ዕንቅስቃሴዎች ደረጃ የወንድማማችነትና የኅብረት ትሥሥር እየጠነከረ በሄደ ቁጥር፣ የገንቢነትና የሥራ ውጤት መጠንም ይበልጥ ከፍ እያለ ይሄዳል።"[20]**

- ፍሬያማ ለሆነ የማኅበረሰብ ዕንቅስቃሴ በሁሉም ጉዳዮች ግልጽና ፍቅር የተሞላበት ምክክር ማድረግ እጅግ በጣም ወሳኝ ቁልፍ ነው። በምክክር አማካኝነት፣ አንድን ጉዳይ እያንዳንዳችን የምንመለከትበት የተለያዩ መንገዶች ይዋሃዱና በጋራ ዕንቅስቃሴዎቻችን ምን ዓይነት አቅጣጫ መከተል እንደሚገባን እናገኛለን። በምክክር አማካኝነት፣ የሃሳብ አንድነት እንቀዳጃለን፣ በሃሳቦቻችንና በዕይታዎቻችን አንድነት ደግሞ፣ ለማኅበረሰቦቻችን ዕድገት የሚበጁ ውጤታማ ዕቅዶችን እናወጣለን። ለእነዚያ ምክክር ለሚያደርጉ አብዱል-ባሃ እንዲህ ይላል፦

**"ለእነዚያ በጋራ ምክክር ለሚያደርጉ በቅድሚያ የሚያስፈልጋቸው የፍላጎት ንፅህና፣ የመንፈስ ብሩህነት፣ ከአምላክ በቀር ከሁሉም መላቀቅ፣ ወደእርሱ መለኮታዊ መዓዛዎች መሳብ፣ በእርሱ ተወዳጆች መካከል ትህትናና ዝቅተኝነት፣ በችግሮች ውስጥ ትዕግስትና ዘላቂ ፅናት እንዲሁም በእርሱ የተከበረ መንበር አገልጋይነት ናቸው። እነዚህን ባህርያት ለማግኘት በፀጋው ከታገዙ፣ ከማይታየው የባሃ መንግሥት ድል ይለገሳቸዋል።"[21]**

- የአስተሳሰብ አንድነት ወደ ተግባር አንድነት ካልተተረጎመ የተሟላ አይደለም። የተግባር አንድነት ሲባል ሁሉም ሰው አንድ ዓይነት ሥራ ይሠራል ማለት አይደለም። በአንፃሩ፣ በተዋሃደ ዕንቅስቃሴ የአንድ ማኅበረሰብ አባላት የተለያዩ ተሰጥዖዎች ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ይውላሉ። ኃይሎቻችን ይባዛሉ፣ እንዲሁም ቁጥራችን ገና ትንሽ ቢሆንም እንኳን፣ በዓለም ውስጥ በጣም ትልቅ እና ኃያላን ድርጅቶች ሊያከናውኑት ያልቻሉትን ለመቀዳጀት እንችላለን። አብዱል-ባሃ እንዲህ ይላል፦

**"ቅዱሳን ነፍሶች፣ የሰማይ ኃይሎችን በመሳብ፣ እንዲህ ባሉ የመንፈስ ባህርያት ሲነሱ እና ደረጃ በደረጃ በአንድነት ሲሰለፉ፣ እነዚያ ነፍሶች እያንዳንዳቸው እንደ አንድ ሺህ ይሆናሉ፣ እንዲሁም የዚያ ኃያል ውቅያኖስ የሚያጥለቀልቁ ሞገዶችም እንደ ሠማይ ሠራዊት ሻለቃዎች ይሆናሉ።"[22]**

ከላይ ያለውን በጥንቃቄ ካነበባችሁና በቡድናችሁ ውስጥ ካሉት ተሳታፊዎች ጋር ይዘቱን አንድ በአንድ ከተወያያችሁ በኋላ፣ ከዚህ በፊት ሦስቱን እንዳደረጋችሁት ጭብጡን ለማቅረብ ስትለማመዱ

አንዳችሁ ሌላችሁን ለማገዝ ትፈልጋላችሁ። ከሥር ያሉት መልመጃዎች ለጥረቶቻችሁ የተወሰነ ዕገዛ ሊያደርጉላችሁ ይችላሉ።

1. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች አሟሉ፦

ሀ. በዚህ ቀን፣ በአምላክ ተወዳጆች መካከል እንደ ____________________ና እንደ ውዝግብ እንደ ጭቅጭቅ፣ እንደ መቃቃርና እንደ መጨካከን ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ እምነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ምንም ነገር የለም።

ለ. በዚህ ቀን፣ በአምላክ ተወዳጆች መካከል እንደ አለመግባባትና ________________፣ እንደ ጭቅጭቅ፣ መቃቃርና እንደ መጨካከን ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ እምነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ምንም ነገር የለም።

ሐ. በዚህ ቀን፣ በአምላክ ተወዳጆች መካከል እንደ አለመግባባትና እንደ ውዝግብ፣ እንደ ጭቅጭቅ፣ እንደመቃቃርና እንደመጨካከን ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ እምነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ____________________________ ።

መ. በዚህ ቀን፣ በአምላክ ተወዳጆች መካከል እንደ አለመግባባትና እንደ ውዝግብ፣ እንደ ጭቅጭቅ፣ እንደመቃቃርና ____________________ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ እምነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ምንም ነገር የለም።

ሠ. በዚህ ቀን፣ በአምላክ ተወዳጆች መካከል እንደ አለመግባባትና እንደ ውዝግብ፣ ________________፣ እንደመቃቃርና እንደመጨካከን ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ እምነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ምንም ነገር የለም።

ረ. በዚህ ቀን፣ በአምላክ ተወዳጆች መካከል እንደ አለመግባባትና እንደ ውዝግብ፣ እንደ ጭቅጭቅ፣ ______________________ ና እንደ መጨካከን ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ እምነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ምንም ነገር የለም።

ሰ. በዚህ ቀን፣ በአምላክ ተወዳጆች መካከል እንደ አለመግባባትና እንደ ውዝግብ፣ እንደ ጭቅጭቅ፣ እንደመቃቃርና እንደመጨካከን ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ ______________ ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ምንም ነገር የለም።

2. በሁለተኛው ጥቅስ ውስጥ፣ አብዱል-ባሃ እንዲህ ይነግረናል፦

ሀ. ፍፁም በሆነ __________________________ መኖር አለብን።

ለ. ______________________________ ፈፅሞ ______________ መሆን የለብንም።

ሐ. ሰዎችን ሁሉ ለእነርሱ ብለን ሳይሆን ለ ______________________ ማፍቀር አለብን።

መ. ሰዎችን ለ ____________________________ የምናፈቅራቸው ከሆነ __________ ወይም ______________________ልናጣ ከቶ አንችልም።

ሠ. ሰው ________________________ አይደለም።

ረ. ________________ ራሳቸውን ከተመለከትን ሁልግዜ ______________________________ እንሆናለን።

ሰ. ወደ ____________________ ከተመለከትን ሰዎችን ________________________________ እንዲሁም ____________________________ እንሆንላቸዋለን።

3. በሦስተኛው ጥቅስ ውስጥ፣ አብዱል-ባሃ እንዲህ ይነግረናል፦

ሀ. እያንዳንዳችን የልባችን ሃሳቦች ሁሉ በ _________________ ና ____________________ ላይ ማተኮር አለብን።

ለ. የጦርነት ሃሳብ ሲመጣብን ____________________________________________________ ______________________________ መቃወም ይኖርብናል።

ሐ. የጥላቻ ሃሳብ ____________________________________________________________ ________________________________ መደምሰስ አለበት።

መ. የጦርነት ሃሳቦች _____________________፣ ________________________፣ __________ ና __________________________ ሁሉ ላይ ጥፋትን ያመጣሉ።

ሠ. የፍቅር ሃሳቦች ___________________________________ ፣ _______________________፣ ___________________________________ ና __________________________ ለማጠናከር ገንቢዎች ናቸው።

4. በማኅበረሰቡ ውስጥ በራሳችሁና በሌሎች መካከል ልዩነቶች ተፈጥረው ካያችሁ ምን ማድረግ ይኖርባችኋል?________________________________________________________________
__________________________________________________________________________________
__________________________________________________________________________________
__________________________________________________________________________________
__________________________________________________________________________________
__________________________________________________________________________________

5. በማኅበረሰባችሁ ውስጥ ለአንድነት አስተዋፅዖ ለማበርከት የሚረዳችሁን መንፈሳዊ ስነ-ሥርዓቶች ግለጹ፡ _________________________________________________________________
__________________________________________________________________________________
__________________________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

6. ከሚከተሉት የትኞቹ ለአንድነት አስተዋፅዖ ያበረክታሉ?

_____ የሌሎችን ጉድለቶች መመልከት

_____ የሌሎችን ስህተቶች አለመመልከት

_____ የሌላውን ሰው ጉድለቶች ለአንድ ኀደኛ አስተያየት መስጠት

_____ ሌላ ሰው መጥፎ መስሎ እንዲታይ አንድን ታሪክ ማጋነን ወይም መቀየር

_____ ስለሌሎች ስህተቶች ማሰብ

7. አንዳንድ ሰዎች አንድን ስህተት ሲሠሩ እንኮንናቸዋለን፣ ነገር ግን ሌሎች ያንኑ ተመሣሣይ ስህተት ሲሠሩ ምንም አንልም፤ ለምን? ______________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

8. ሰዎች አንዳቸው ሌላቸውን እያሙ ባለበት ሁኔታ ውስጥ አንድነት ሊኖር ይችላልን? ለምን አይሆንም? ______________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

9. ስለ አንድ ሰው ውሸት መናገር ግልጽ ስህተት ነው። ነገር ግን አንድ ሰው በዕርግጥ ስላደረገው ወይም ስላደረገችው የሆነ ነገር ለሌሎች ተቺ አስተያየቶችን መስጠት አግባብ ነው? _________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

10. ሌሎችን በማማት፣ በክፉ ማንሳት፣ እና በመተቸት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? _____

11. ሐሜት፣ ሰውን በክፉ ማንሳት፣ እና ተከታታይ ትችት በአንድ ማኅበረሰብ ላይ ምን ዓይነት ውጤቶች አላቸው? ______

12. እነዚህን ልማዶች ከሕይወታችን እንዴት ልናስወግዳቸው እንችላለን? ______

13. ስለሰዎች ልክ እንዳሉ ያህል አድርገን ብቻ ብናወራ ምን ሊሆን ይችላል? ______

14. በልጆች ፊት ስለሰው ብናማ፣ በእነርሱ ላይ ምን ተፅዕኖ ይኖረዋል? ______

15. የሐሜትና ሰዎችን በክፉ የማንሳት ዝንባሌ ከየት ይመጣል? ______

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

16. ባሃኦላህ እንዲህ ያሳስበናል፦ "የእኔነት እሳት ቢያሸንፋችሁ፣ እያንዳንዳችሁ ________________
____________________ ይበልጥ ________________________________________፣
____________________ እንጂ ________________________________________::"

17. ፍቅር በቃላት ብቻ አይገለጽም:: ሌላ ምን ያስፈልጋል? ________________________________
________________________________________________
________________________________________________

18. ከአንድነትና ፍቅር ጋር ተያይዞ፣ አብዱል-ባሃ እንዲህ ይለናል፦ "ለቅፅበትም ቢሆን እንኳን _____
________________________፣ ለአፍታም ቢሆን እንኳን _______________________________፤
ይልቁንም ከወዳጆች መካከል ለአንዱ ብቻም ቢሆን ____________________________________
____________ ለመስጠት ትችል ዘንድ እንዲሁም ለአንድ ብሩህ ልብም ብቻ ቢሆን __________
________________________________________________
____________________________________________::"

19. በተጨማሪም እንዲህ ይላል፦ "ለሰው ዘር ከሁሉም በላይ የሚያስፈልገው _________________ና
________________________ነው:: በሁሉም የሰው ዕንቅስቃሴዎች ደረጃ ___________________
_________ ና _______________________________ትስስር እየጠነከረ በሄደ ቁጥር፣ ___________
_____ ና _____________________________________ መጠንም ይበልጥ ከፍ እያለ ይሄዳል::"

20. ለተሳካ የማኅበረሰብ ተግባር እጅግ በጣም አስፈላጊው ቁልፍ ነገር ምንድን ነው? ____________
________________________________________________
________________________________________________

21. ስለ እነዚያ ምክክር ስለሚያደርጉት አብዱል-ባሃ እንዲህ ይላል፦ "ለእነዚያ በጋራ ምክክር ለሚያደርጉ በቅድሚያ የሚያስፈልጋቸው _________________________________፣___________
____________________፣____________________________________________________________
____________________፤_________________________________________________________፣
በእርሱ ተወዳጆች መካከል፣ _____________________________________፣ በችግሮች ውስጥ ____

_______________________________ እንዲሁም በእርሱ የተከበረ መንበር_______________ ናቸው። እነዚህን ባህርያት ለማግኘት በፀጋው ከታገዙ፣ ከማይታየው የባሃ መንግሥት _______ ______________________________።"

22. በአንድነት የመሥራትን ኃይል በተመለከተ፣ አብዱል-ባሃ እንዲህ ይነግረናል፦ "ቅዱሳን ነፍሶች፣ __________________________________ በመሳብ፣ እንዲህ ባሉ ____________________ ____________________ ሲነሱ እና ደረጃ በደረጃ ____________________________ሲሰለፉ፣ እነዚያ ነፍሶች ________________________ እንደ __________________________ይሆናሉ፣ እንዲሁም የዚያ ኃያል ውቅያኖስ የሚያጥለቀልቁ ሞገዶችም እንደ _____________________ ____________________________________________ይሆናሉ።"

## ምዕራፍ 9

ከአቶና ወ/ሮ ሳንቼዝ ጋር በነበራት አራተኛ ጉብኝት ወቅት፣ በአቅራቢያቸው ያለ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እየተከታተለች ከእነርሱ ጋር ለመኖር የመጣችውን ሴት የልጅ ልጃቸውን ቢየትሪስን በማግኘቷ አሌሃንድራ ደስታ ተሰምቷታል። ቢየትሪስ ስለ አንድነት ጭብጥ በጣም ጉጉ በመሆኗ በውይይቱ በጋለ ፍላጎት ትሳተፋለች። ጭውውቱ ወደ መጠናቀቂያው ሲቃረብ፣ ወ/ሮ ሳንቼዝ ለእያንዳንዱ ሰው ቡናና ኬክ ታቀርባለች። ይህ ቢየትሪስን ይበልጥ ለማወቅ ለአሌሃንድራ ዕድል ሰጣት፣ እናም በሰፈሩ ውስጥ ስለሚኖረው የማኅበረሰብ ግንባታ ጥረቶች ለመነጋገር በቀጣዩ ቀን ለመገናኘት ቀጠሮ ትይዛለች። "ዓብይ ተከታታይ ኮርሶችን ለማጥናት ፍላጎት ይኖራት ይሆናል፣" ስትል አሌሃንድራ ለራሷ ታስባለች። "የመጀመሪያዎቹን ጥቂት መጽሐፍት ፈጋ ባለ ፍጥነት እንድትሄድባቸው ላግዛት እችላለሁ። ከዚያ የሕጻናት ክፍል ትምህርት ለመጀመር ትፈልግ ይሆናል ወይም በሰፈሩ ውስጥ የታዳጊ ወጣት ቡድን በመመሥረት ትረዳኛለች። በዚያ ረገድ፣ እንደ አነቃቂ ለማገልገል ወደሚያዘጋጃት መጽሐፍ 5 ድረስ ስትዘልቅ ለቡድኑ ቀስ በቀስ የበለጠ ኃላፊነት ልትወስድ ትችላለች።" አሌሃንድራ ብዙዎቹን ወደ ተቋም ሂደቱ እንዲሳተፉ የረዳቸውን፣ በተወሰኑ የውይይት ርዕሶች ላይ ያተኮሩትን፣ ለወጣቶች የተዘጋጁትን በርካታ ስብሰባዎች ተካፍላለች። በቀጣዩ ቀን ከቢየትሪስ ጋር በሚኖራት ጭውውት ተመሳሳይ የሃሳቦች ቅደም ተከትል ለመጠቀም ትወስናለች። ጭውውቱ የሚከፈተው እንዲህ ነው፦

> *ሁላችንም ዓለም የተሻለች ሥፍራ ሆና ማየት እንፈልጋለን። መጪው ግዜ ሁሉን አቀፍ ሠላም የሚመሠረትበትና የሰው ልጅ ቤተሰብ ተስማምቶ የሚኖርበት እንዲሆን እንመኛለን። እንዲህ ያለው ግዜ ህልም አይደለም እንዲሁም ለዓለም መሻሻል አስተዋፅዖ ለማበርከት አብዛኞቻችን በምናደርገው ጥረት ላይ ሊገነባ ይችላል። እያንዳንዳችን በልቦቻችን ውስጥ ማኅበረሰቦቻችንን የማገልገል ፍላጎት አለን። የሚያስፈልገን ለጋራ ደህንነት ከእኔነት የፀዳ የአገልግሎት ተግባራትን ለማከናወን አቅማችንን ማዳበር ነው።*
>
> *ለሰው ልጅ ስለምናደርገው አገልግሎታችን በጋራ የምንጓዝበትን የአገልግሎት ጎዳና በምናብ በመሳል ልናስብ እንችላለን። ይህ ጎዳና ለሁሉም ክፍት ነው። እያንዳንዳችን ወደሱ ለመግባት ምርጫ እናደርጋለን፣ በገዛ ራሳችንም ፍጥነት ልክ እንራመዳለን። ይህን መንገድ ብቻችንን*

አንንዝም፤ በጋራ በመማር እና አንዳችን ሌላችንን በመደገፍ ከጓደኞቻችን ጎን ለጎን እናገለግላለን። የምንወስደው እያንዳንዱ እርምጃ ደስታና ዋስትናን ይፈጥራል፣ የምናደርገው እያንዳንዱ ጥረትም መለኮታዊ ማረጋገጫዎችን ያመጣል።

ቢያትሪስ እየሰማች ያለውን ትወዳለች እንዲሁም ከዚህ አጭር ንግግር በኋላ ሕይወታማ የሆነ ጭውውት ይከተላል። ወደፊት ከመራመዳችን በፊት፣ እዚህ ቆም ብለን በሁለቱ አዲስ ጓደኛሞች መካከል ስላለው የመስተጋብር ሁኔታ እናሰላስል። ቢያትሪስ በተቋሙ ሂደት ውስጥ እንድትሳተፍ ለመጋበዝ የሚያስችላትን አንኳር በሆነ የጭውውት ነጥብ ላይ ለማትኮር አሌሃንድራ ወስናለች። ለቢያትሪስ ተከታታይ ኮርሶች በተቋሙ እየተሰጡ እንደሆነና እንድትቀላቀላቸው መጋበዝ ለእርሷ በቂ ሆኖ ያላገኘችው ለምንድን ነው?

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

## ምዕራፍ 10

በአሌሃንድራና በቢያትሪስ መካከል የሚደረገው ጭውውት ለሁለት ሰዓታት ያህል ይቀጥላል። ከሥር ያሉት አሌሃንድራ ከአዲሷ ጓደኛዋ ጋር የምትካፈላቸው በዛ ያሉ ተጨማሪ ሃሳቦች ናቸው። በዕርግጥ፣ የማያቋርጥ ረዥም ገለፃ እንደማታደርግ እንረዳለን። ሁለቱ ሰዓታት በአብዛኛው የሚውለው በእነዚህ አንቀጾች ውስጥ የተዘረዘሩትን ሃሳቦች በጋራ በመከወን ነው፦

ወጣቶች ነን፣ ጉልበት አለን፣ እንዲሁም ታላቅ የጋለ ፍላጎት አለን። ሰዎች ግድ የለሾች እንደሆንን አድርገው ይገምታሉ። ነገር ግን በተቃራኒው ነው፤ የሰው ልጅ አስከፊ ሁኔታ ያገባናል እንዲሁም ለኅብረተሰብ እውነተኛ ለውጥ መጥቶ ማየት እንፈልጋለን። ስለገዛ ራሳችን ሕይወትም ጭምር ማሰብ ይኖርብናል - ትምህርት፣ሥራ፣ጓደኞች፣ ቤተሰብ። በየዓመቱ እያደግን ስንሄድ፣ራሳችንን የበለጡ ኃላፊነቶችን ተሸክመን እናገኘዋለን፤ ወላጆቻችን ከእኛ ብዙ ይጠብቃሉ። አንዳንዴ፤ ስለኃላፊነቶቼ ሳስብ፣ ከመጠን በላይ በሆነ ስሜት እዋጣለሁ። ከዚያም በቃሌ ከያዝኩት ከባሃኢ ቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ አንድ ጥቅስ አስታውሳለሁ፦ “የሰው ሕይወት የራሱ የፀደይ ወቅት አለው ድንቅ ክብርም የታደለ ነው። የወጣትነት ወቅት በብርታትና በኃይል ተለይቶ የሚታወቅ ሲሆን፣ በሰው ሕይወት ውስጥ እጅግ በጣም ምርጥ እንደሆነ ጊዜ ጎልቶ ይታያል።”

ላካፍልሽ የምፈልገው ልክ እንደኛ ማኅበረሰቦች በዓለም ዙሪያ ያሉ ብዙ ወጣት ሰዎች ጉልበታቸው በሁለት እጥፍ ዓላማ ሊመራ እንደሚችል እየተገነዘቡ ናቸው፦ ለራሳቸው አዕምሮአዊና መንፈሳዊ ዕድገት ኃላፊነት መውሰድ እና ለህብረተሰብ ለውጥ አስተዋፅዖ ማበርከት። እነዚህ ሁለት የዓላማችን ገጽታዎች የተሣሠሩ ናቸው። የገዛ ራሳችንን ችሎታዎች

ስናጎለብት፣ ሌሎችን በተሻለ ለማገልገል እንችላለን፣ እንዲሁም እርስ በርስ በመተጋገዝ እንደ ግለሰብ እናድጋለን ያሉንንም ባህርያት እናጠናክራለን።

ይህ ከዚህ በፊት የጠቀስኩት የአገልግሎት ጎዳና ሃሳብ የሚመጣበት ነው። ይህ መንገዝ ወደ ሕይወታችን ዝም ብለን የምናክለው ነገር አይደለም፤ ለምናደርገው እያንዳንዱ ነገር ትርጉም ያመጣል። ለማኅበረሰቡ አገልግሎት መስጠት የትምህርታችንን ዓላማ ይበልጥ ለመገንዘብ፣ ስለወደፊቱ አስተሳሰቦቻችንን ለማጥራት፣ ለቤተሰቦቻችን ደህንነት አስተዋፅዖ ለማበርከት የሚያስፈልጉንን መልካም ባህርያት ለማጎልበት ይረዳናል። ወዳጅነቶቻችንን ያጠናክርልናል። ኃይሎቻችንን በእርባና - ቢስ ድርጊቶች ላይ እንዳናባክን ያደርገናል።

ስለ መንፈሳዊና አዕምሮአዊ ዕድገቶቻችን ስናስብ፣ ተፅዕኖ የሚያሳድሩብንን ብዙ ኃይሎች ልናውቃቸው ይገባል። አንዳንዶቹ፣ እንደ የዕውቀት፣ የፍትኅ እና የፍቅር ኃይሎች የመሳሰሉት በትክክለኛው አቅጣጫ ያንቀሳቅሱናል፣ እናም ከነሱ ጋር እራሳችንን ማጣጣምን መማር አለብን። ሌሎች፣ እንደ ቁስ አካላዊነት እና እኔነት ያሉ ኃይሎች ደግሞ ተቃራኒውን ያደርጋሉ፣ በመሆኑም ልንቃወማቸው ይገባል። ልቀትን ለመቀዳጀት ጥረት ማድረግ  እና ጥረቶቻችን በመለኮታዊ ማረጋገጫ እንደሚባረክ እምነት ሊኖረን ይገባል።

እንዲሁም ለኅብረተሰብ ለውጥ እኛ ስለምናበረክታቸው ስናስብ - የብጥብጥ፣ ድህነት፣ እና ስቃይ ዓለምን ወደ የሠላም ዓለም፣ ብልፅግና፣ እና ስምምነት መለወጥ - ሁለቱንም ቁሳዊና መንፈሳዊ ዕድገትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለብን። እንዲሁ መንፈሳዊ ዕድገትን እስካላመጣን ለሁሉም ሰዎች ቁሳዊ ዕድገት አይደረስበትም። እነዚህ ሁለቱ አብረው ጎን ለጎን ከሄዱ ብቻ ነው የዓለም መሻሻል የሚሳካው። ለማስታወስ የቻልኩት ሌላ ጥቅስ አለ፦ " ቁሳዊ ስልጣኔ ልክ እንደ ፋኖሱ ሲሆን፣ መንፈሳዊ ስልጣኔ ደግሞ በፋኖሱ ውስጥ እንዳለው ብርሃን ነው። ቁሳዊውና መንፈሳዊው ስልጣኔዎቹ ከተዋሃዱ፣ ብርሃኑና ፋኖሱ በአንድላይ ይኖሩናል፣ ከዚያም ውጤቱ ፍፁም ይሆናል።"

የአገልግሎት ጎዳናን ስንገዝ፣ ከግለስቦች ቡድኖች ጋር መሥራት፣ በተለይም ሕፃናትና ታዳጊ ወጣቶች፣ ዕውቀት፣ ክህሎቶች፣ መንፈሳዊ ባህርያት እንዲያገኙ መርዳት እንማራለን። በተጨማሪም ለማኅበረሰቦቻችን አንድነት ትኩረት መስጠትን እንማራለን። ለማኅበረሰብ ዕድገት አስተዋፅዖ ለማበርከት የሚሹ ግለሰቦች፣ ቤተስቦች፣ እና ድርጅቶች መተባበር ይኖርባቸዋል። የጋራ ራዕይና ዓላማ መገንባት እንዲሁም የግጭትን መንገዶች እርግፍ አድርገው መተው አለባቸው።

ስለዚህም፣ እንደ ወጣት ከሌሎች ጋር የተጣጣመ የግንኙነት ልምዶችን ማዳበር አስፈላጊ ነው። ወዳጆች መሆን አለብን፦ በምንሠራቸው ሥራዎች አንዳችን ከሌላችን ጋር አብሮ መንዝ፣ የእያንዳንዳችንን አስተዋፅዖ ዕውቅና መስጠት፣ እርስ በርስ መበረታታትና መደጋገፍ፣ የእያንዳንዳችንን ጥንካሬ መመልከት፣ እርስ በርስ ጠቃሚ ምክሮችን መፈለግና መለገስን፣ እንዲሁም አንዳችን በሌላችን ስኬቶች ደስታን መጋራት። የአገልግሎት ጎዳናን ስንራመድ፣ መተግበር፣ በተግባሮቻችን ላይ ማሰላሰል፣ መመካከርና በጋራ ማጥናት አለብን።

ባለፉት ጥቂት አሥርተ ዓመታት፣ የባሃኢ ማኅበረሰብ በተግባር በእያንዳንዱ የዓለም ሀገር ውስጥ በጣም ልዩ የሆነ የመማሪያ ተቋም በመመሥረት አሳክቶታል። እንዲህ ብለን የምንገልፃቸው እነዚህ ተቋማት፣ ማኅበረሰቡን ለማገልገል አቅማችንን ለማጠናከር የሚያስችሉ

ኮርሶችን ይሰጣሉ። እነዚህን ኮርሶች በማጥናት፣ በአገልግሎት ጎዳና ላይ በጋራ ወደፊት ለመራመድ የሚያስፈልጉትን መንፈሳዊ ዕይታዎችና ተግባራዊ ክህሎቶች እናገኛለን። በነሱ ውስጥ ስናልፍ፣ እየተወሳሰቡ የሚመጡ የአገልግሎት ተግባራትን የማከናወን አቅማችን ያድጋል። በዚያ ግዜ ሁሉ፣ በእነዚያ ከኛ የበለጠ ልምድ ባላቸው ድጋፍ ይደረግልናል፣ በግዜ ሂደትም ትንሽ ልምድ ያላቸውን እኛ ድጋፍ እናደርግላቸዋለን። ከጅምሩ፣ ሁላችንም የግለሰብና የኅብረተሰብ ለውጥ አራማጆች፣ ለገዛ ራሳችን መማርና ማኅበረሰባችንን ለማገልገል ኃላፊነትን በጉጉት እንወስዳለን።

"ተዋናይ መሆን" በማስተዋል የመከወን፣በጥረቶቻችን መትጋት፣ እንዲሁም በእያንዳንዱ እርምጃ ዕውቀት ለማግኘትና ለመተግበር የፈቃደኝነት መኖር ማለት ነው። የአንድ ነገር አራማጅ ዝም ብሎ የጥቅሞች ተቀባይ ብቻ ሳይሆን ለዕድገት ዋና አስተዋፅዖ አበርካች ነው። አንድ ሰው የአንድ ነገር አራማጅ ለመሆን ፈጠራ የተሞላበትና ስነ-ሥርዓት የተላበሰ መነሳሳት መተግበርን መማር አለበት። የተቋሙ ኮርሶች የማኅበረሰብ ግንባታ ሂደቱ አራማጅ እንድንሆን አቅማችንን ለማጎልበት ይረዱናል።

ከላይ ባሉት አንቀጾች ውስጥ ያሉት ሃሳቦች ላይ ለማሰላሰል አንድ አፍታ መውሰድ ይኖርብናል። በምዕራፉ መጀመሪያ እንደተጠቀሰው፣ አሌሃንድራ ሃሳቦቹን ዝም ብላ ተራበተራ አታቀርባቸውም ይልቁንም ቢየትሪስ ስለጉዳዮቹ ለማሰብ እና ውይይቱ ላይ አስተዋፅዖ ለማበርከት ሰፊ ግዜ እንዳገኘች ታረጋግጣለች። እያንዳንዱን አንቀጽ በቡድናችሁ ውስጥ ለመወያየት እና ሃሳቦቹን እራሳችሁ በአግባቡ ለመግለጽ ከቻላችሁ በኋላ - ለማጤን ልትፈልጉ የምትችሉት - ስለ አንዳንድ የሩሂ ተቋም ኮርሶች ጥቂት ቃላት በማካፈል አሌሃንድራ በራስ የመተማመን ስሜት እስኪሰማት ድረስ እና ቢየትሪስ የመጽሐፍ 1 ጥናት እንድትቀላቀል ወደ መጋበዝ ነጥብ ጭውውቱ አድጓል ወይስ አላደገም የሚለውን ነው። በእርሷ ቦታ ብትሆኑ ኖሮ ምን ልትሉ እንደምትችሉ ከሥር ባለ ባዶ ቦታ ልትጽፉ ትችላላችሁን? መጽሐፍ 1 እና 2 ትን እንዴት ትገልጹታላችሁ? የሚጋብዙትን የአገልግሎት ተግባሮችንስ? በተከታታይ መጽሐፍት ውስጥ የተከናወኑ የአገልግሎት ተግባራት አጭር ማጣቀሻ - በተለይም የልጆች መንፈሳዊ ትምህርት ክፍሎች እና የታዳጊ ወጣት ቡድንን እንደ አነቃቂ መምራት - ቢየትሪስ ወደፊት ምን ዓይነት አገልግሎት ልታበረክት እንደምትችል ዕይታ እንድታገኝ ያለጥርጥር ይረዳታል። የቡድናችሁ አስጠኚ በእነዚህ ሁለት የአገልግሎት ተግባራት ላይ ቢየትሪስን መጽሐፍ 1 እንድታጠና ለመጋበዝ አሌሃንድራ ልታክላቸው ከምትችለው ጋር ተመሳሳይ የሆኑ፣ ጥቂት ዓረፍተ-ነገሮች እንድትጽፉ ሊያግዛችሁ ይችላል።

## ምዕራፍ 11

አሌሃንድራ ወደ ሳንቼዝ ቤት ቀጣይ ጉብኝቷን ከማድረጓ በፊት ሁለት ሳምንታት አለፉ። በዚህ ወቅት፣ ቢያትሪስ በተጠናከረ ዘመቻ /በኢንቴንሲቭ ካምፔይን/ ውስጥ ለመሳተፍ ችላ ነበር እናም የመጽሐፍ 1 የመጀመሪያዎቹን ሁለት ክፍሎች አጠናቅቃለች። እሷ አሁን በአጎራባች መንደሩ ውስጥ በሳምንት ሁለት ግዜ ከሚገናኙ አምስት ወዳጆች ጋር ሦስተኛውን ክፍል እየተሳተፈችበት ነው። አሌሃንድራ ከሳንቼዝ ቤተሰብ ጋር በጸሎት ጭብጥ ላይ ለመጨዋወት አመቺ ግዜ ነው ብላ ታስባለች እናም ቢያትሪስ ልታግዛት ትችል እንደሆነ ትጠይቃታለች። የመጽሐፍ 1 ሁለተኛው ክፍልን እናንተ ራሳችሁ አጥንታችኋል፣ ስለዚህ በጉብኝታቸው ወቅት በአሌሃንድራና ቢያትሪስ የተዳሰሰውን ይዘት ለናንተ አሳጥሮ ማቅረቡ አስፈላጊ አይደለም። ክፉሉን ከከለሳችሁ በኋላ፣ በዚህ ጭብጥ ዙሪያ በውይይት ውስጥ ለማንሳት የምትሞክሩትን ዓበይት ነጥቦች ማውጣት መቻል ይኖርባችኋል። ሃሳቦቻችሁን ለማስፈር ከሥር ባዶ ቦታ ተቀምጦላችኋል:-

## ምዕራፍ 12

አሌሃንድራ ወደ ሳንቼዝ ቤተሰብ የምታደርጋቸው ጉብኝቶች ለተወሰኑ ሳምንታት ይቀጥላሉ፣ እናም ከውይይታቸው ተፈጥሯዊ በሆነ መልኩ የሚመነጩ በዛ ያሉ ጭብጦች በፀሎት አስፈላጊነት ላይ ማለትም  የነፍስ ሕይወት፣ መንፈሳዊ ባህርያትን ማዳበር፣ ለአምላክ ሕግጋትና ድንጋጌዎች መታዘዝ እንዲሁም በፍቅሩ መፅናት ላይ ለመወያየት ዕድል አላቸው:: በአንድ አጋጣሚ፣ ስለ አስተዳደር ሥርዓቱ ተቋማት፣ በተለይም ስለ አካባቢና ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባዔዎች ትንሽ ይጨዋወታሉ:: በእያንዳንዳቸው እነዚህ ተከታታይ ጉብኝቶች የተዳሰሰውን ይዘት ከግምት ውስጥ ማስገባት አያስፈልገንም:: ሆኖም ግን፣ በተሳታፊዎች መካከል በተከታታይ ጭውውቶች ብዙ ግዜ የሚነሱ ሁለት ጥያቄዎች ልክ አሁን እንደምንተልመው ያሉ አሉ:: አንደኛው በማኅበረሰቡ የሚካሄዱ የስብሰባዎች ዓይነት እና ሁለተኛው ከፋይናንስ ሀብቶች ጋር ይያያዛል:: በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የስብሰባዎችን ርዕሰ-ጉዳይ እንመለከታለን፣ በተለይም የአሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓል፣ በቀጣዩም የፋይናንስ / መዋዕለ-ንዋይ ጥያቄን እንመለከታለን::

ከዚያ፣ ተከታዮቹ ነጥቦች፣ በአሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓል ጭብጥ ላይ ለመጨዋወት መሠረት ሊሆኑ ይችላሉ፦

- በባሃኢ ማኅበረሰብ ውስጥ፣ ስብሰባዎች ለተለያዩ ዓላማዎች ይካሄዳሉ ማለትም ለመጸለይ፣ ጽሁፎችን ለማጥናት፣ ልዩ ሁኔታዎችን/ በዓላትን ለማክበር፣ በማኅበረሰቡ ጉዳዮችና ለኅብረተሰብ አገልግሎት መስጠት ላይ ለመመካከር፣ የተግባር ዕቅዶች ላይ ለመወያየት። ባሃኦላህ ተከታዩን የተስፋ ቃል ይሰጣል፡-

**"በሕይወቴና በእምነቴ! የአምላክ ወዳጆች በሚገቡበት፣ ከውስጡም ጌታን ሲያመሰግኑና ሲያወድሱ ጩኸታቸው ከሚሰማበት በማንኛውም መኖሪያ ቤት ዙሪያ፣ የእውነተኛ አማኞች ነፍሶችና የተመረጡ መላዕክት ሁሉ ይዞራሉ።"**[23]

- በወዳጆች መካከል በሚኖር ስብሰባ የአምላክን ቃላት ማዳመጥ ለልቦች ሃሴትን ያመጣል የአንድነት ትሥሥሮችንም ያጠናክራል። ባሃኦላህ እንዲህ ያሳስበናል፡-

**"ወዳጆች በማንኛውም አገር ቢሆኑ፣ በስብሰባዎች በአንድ ላይ ለመገናኘት፣ በዚያም በጥበብና በአንደበተ ርቱዕነት መናገር፣ የአምላክንም ጥቅሶች ማንበብ አለባቸው፤ የፍቅርን እሳት የሚለኩሱትና እንዲንበለበል የሚያደርጉት የአምላክ ቃላት ናቸውና።"**[24]

አብዱል-ባሃ እንዲህ ሲል ጽፏል፡-

**"ያቺ አገር በእውነት ብርሃን እንድትበራ፣ ያም ምድር፣ በመንፈስ ቅዱስ ማረጋገጫዎች አማካኝነት ማራኪ ገነት እንዲሆን፣ ስብሰባዎች በማድረግ የመንግሥተ ሰማይን ትምህርቶች ድገሙ አዚሙአቸውም፣ምክንያቱም ይህ ዘመን የንውዱ ጌታ ዑደት ነውና፣እንዲሁም የሰው ልጅ ዓለም አንድነት ጣፋጭ ዜማ ለምሥራቁም ለምዕራቡም ጆሮዎች እየደረሰ ነው።"**[25]

- ከባሃኢ ስብሰባዎች ሁሉ፣ የአሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓል በተለይ መጠቀስ ይኖርበታል። የባሃኢ የቀን መቁጠሪያ እያንዳንዳቸው አሥራ ዘጠኝ ቀናት ያሏቸው አሥራ ዘጠኝ ወራት አሉት፣ እንዲሁም፣ በእያንዳንዱ አካባቢ፣ ባሃኢዎች ባሃኦላህ እራሱ እንዳዘዛቸው በወር አንዴ ለዚህ ስብሰባ በጋራ ይሰባሰባሉ፡-

**"የሚቀርበው ውሃ ብቻም እንኳ ቢሆን፣ በእውነቱ፣ በየወሩ አንድ ግዜ፣ ግብዣ (የአሥራ ዘጠነኛ ቀን በዓል) እንድታስተናግዱ ታዛችኋል፤ ምክንያቱም በሁለቱም በምድራዊውና በመንግሥተ ሰማያዊው ሀብት አማካይነት ቢሆንም እንኳ፣ አምላክ የሰዎችን ልቦች ለማስተሳሰር አቅዷልና።"**[26]

- የአሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓል ሦስት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው የፀሎትና የምንባብ ክፍለ ግዜ ሲሆን፣ በዚህም ግዜ ፀሎቶች ይደረጋሉ ከቅዱሳን ጽሁፎችም ምንባቦች ይነበባሉ። ሁለተኛው የአስተዳደር ክፍለ ግዜ ሲሆን፣ በዚህ ወቅት በማኅበረሰቡ ጉዳዮች ላይ ምክክር የሚካሄድበት ነው። ሦስተኛው ማኅበራዊ ክፍለ ግዜ ነው።

- የአሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓል የፀሎትና የምንባብ ክፍለ ግዜ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ከሚከተሉት የአብዱል ባሃ ቃላት ዕይታ እናገኛለን፡-

**"እናንተ የጥንታዊው ውበት ታማኝ አገልጋዮች ሆይ! በእያንዳንዱ ዑደትና የግልፀት ዘመን፣ ግብዣ የተመረጠና የተወደደ ነበር፣ ለምላክ አፍቃሪዎችም ገበታ መዘርጋት እንደሚያስመሰግን ተግባር ሲቆጠር ነበር። በተለይም በዛሬው ግዜ፣ ይህ (የአሥራ ዘጠነኛው ቀን ግብዣ) አምላክን**

**ለማምለክና ለማወደስ ከሚደረጉት ስብሰባዎች መካከል እንደ አንዱ ስለሚቆጠር፣ በዚህ ከወደር በላይ በሆነው ግልፀት ዘመን፣ በዚህ ከዘመናት ሁሉ በላይ ለጋስነት በተመላው ዘመን፣ይህ እውነት ነው። እዚህ ቅዱሳን ጥቅሶች፣መንግሥተ ሰማያዊዎቹ ቅኔዎችና ውዳሴዎች ይዜማሉ፣ ልብም ትቀሰቀሳለች ከራስዋም ትላቀቃለች።"[27]**

- በበዓሉ የአስተዳደር ክፍለ ግዜ፣ አማኞች የቅርብና የሩቅ የባሃኢ ማኅበረሰቦች ስለሚያደርጉት ዕንቅስቃሴዎች ሪፖርቶችን ያዳምጣሉ፣ በማኅበረሰባቸው ውስጥ ስላሉ የእምነቱ ጉዳዮችና ለኅበረተሰቡ ደህንነት የሚያበረክቱትን አስተዋፅዖዎች ይመካከራሉ፣ ከዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትህ ከተቀበሉት መመሪያ ጋር ራሳቸውን ያስተዋውቃሉ፣ በዕቅዶቻቸው ዕድገት ላይ ያሰላስላሉ፣ ለእምነቱ ተቋማት አስተያየቶች ያቀርባሉ። እያንዳንዱ አማኝ በዓለም አቀፍ የባሃኢ ማህበረሰብ ጉዳዮች ላይ የሚካፈለው በዚህ መንገድ ስለሆነ የአሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓል ምክክሮች በጣም አስፈላጊ ናቸው።

  የበዓሉ የማኅበራዊ ክፍለ ግዜ፣ የወዳጅነትና የግብዣ ግዜ ነው። ሙዚቃ /መዝሙር/ መጫወት ይቻላል፣አነቃቂ ንግግሮች ይደረጋሉ፣ዝግጅቶችም በሕፃናት ይቀርባሉ። በአጭሩ፣ በጥንቃቄ የተመረጡ የባህል መግለጫዎች፣ የተከበሩ እና አስደሳች የሆኑ፣ ይህንን የበዓሉን ክፍለ ግዜ ለማበልፀግ ሊያገለግሉ ይችላሉ።

- የአሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓል የእምነቱ አስተዳደራዊ ሥርዓት ጠቃሚ ገፅታ ነው። የማኅበረሰቡን ሕይወት አምልኮአዊ፣አስተዳደራዊና ማኅበራዊ ገፅታዎችን ያዋህዳል። የበዓሉ ስኬታማነት የሚወሰነው እነዚህ ሦስት ክፍሎች ሚዛናቸውን ሲጠብቁ በመሆኑ ለሁሉም ዕኩል አትኩሮት ሊሰጣቸው ይገባል። እ.ኤ.አ. በነሐሴ 1989 ዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትህ ለባሃኦላህ ተከታዮች በሙሉ በፃፉት መልዕክት እንዲህ ብለዋል፦

  **"የባሃኦላህ የዓለም ሥርዓት ሁሉን የሰው ኅብረተሰብ ክፍሎች ያጠቃልላል፤ የሕይወትን መንፈሳዊ፣ አስተዳደራዊ፣እና ማኅበራዊ ሂደቶች ያዋህዳል፤ በተለያዩ መንገዶች የሚገለፁትን የሰው አስተሳሰቦች ለአዲስ ሥልጣኔ ግንባታ በሚጠቀሙበት አቅጣጫ ይመራቸዋል። አሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓል እነዚህን ገፅታዎች ሁሉ የኅብረተሰቡ መሠረት በሆነው ደረጃ ያቅፋቸዋል። በመንደሩ፣ በአምባው፣ በከተማው የሚሠራ፣ ሁሉም የባሃ ሕዝብ አባላት አባል የሆነበት ተቋም ነው። አንድነትን ለማጎልበት፣ ዕድገትን ለማረጋገጥ፣ እና ሐሴትን ከፍ ከፍ ለማድረግ የታቀደ ነው።"[28]**

- ይህን ያህል አስፈላጊነት ያለው የአሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓል በጥድፊያ መዘጋጀት አይችልም። እያንዳንዱ የበዓሉ ተካፋይ፣ በፀሎትና በማሰላሰል በመታገዝ፣ ራሱን ወይም ራሷን ማዘጋጀት አለበት/አለባት፣ በበዓሉ ግዜም፣ እያንዳንዱ ሰው ፀሎት በማድረግም ሆነ የሚነበቡትን ቅዱሳን ጽሁፎች በማዳመጥ፤ ዘገባዎችን በማቅረብ፣ መመሪያዎችን በመቀበል፣ ወይም አስተያየቶችን በመስጠት፤ እንደ አስተናጋጅ በመሆን ወይም እንዲው በደስታና በብሩህነት መስተግንዶውን ሲካፈል ወይም ስትካፈል ከልብና አዕምሮ መሳተፍ ይኖርበርታል። የአሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓልን አስመልክቶ በተመሳሳይ ደብዳቤ ዓለም አቀፍ ቤተፍትህ እንዲህ ይላል፦

  **"የበዓሉ ዝግጅት አስፈላጊ ገፅታዎች ተስማሚ ምንባቦችን መምረጥን፣ ጥሩ አንባቢዎችን አስቀድሞ መመደብን፣ እንዲሁም በጸሎትና በምንባብ ፕሮግራም ውስጥ በአቀራረቡና በአቀባበሉ**

በሁለቱም የመልካም ባህርይ ስሜት እንዲኖር ማድረግን ያካትታል። የአሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓሉ በሚደረግበት አካባቢ፣ ቤት ውስጥም ሆነ ከቤት ውጪ፣ ትኩረት መስጠቱ ዝግጅቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ ያሳድራል። ንፅህና፣ ሥፍራውን ለአከባበሩ በሚያመችና በተዋበ ሁኔታ ማዘጋጀቱ - ሁሉም ጉልህ ሚና አላቸው። ሰዓት ማክበሩም የመልካም ዝግጅት መለኪያ ነው።"

"የበዓሉ አከባበር መሳካት፣ በአብዛኛው በግለሰቡ ዝግጅትና ተሳትፎ ጥራት ይወሰናል። ተወዳጁ ጌታ (አብዱል ባሃ) የሚከተለውን ምክር ይለግሳል፦ 'እነዚህ በዓላት በሚከበሩበት ግዜ የጌታ ተወዳጆችና የምሕረተኛው ሴት አገልጋዮች ፊታቸውን ወደ አምላክ መንግሥት እንዲያዞሩ፣ ምቁራባትን እንዲያዜሙ፣የአምላክን ዕርዳታ እንዲማፀኑ፣ በሐሴት እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱ፣ በንፅህናና በቅድስና፣ በፈሪሃ እግዚአብሔርም እንዲያድጉ፣ እንዲሁም ምድራዊ ብርቱ ስሜትንና እኔነትን በመግታት፣ ለአሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓል ስብሰባዎች ትልቅ ክብደት ስጡ። በዚህ ሁኔታ ራሳቸውን ከዚህ ቁሳዊ ዓለም በማላቀቅ፣በመንፈስ ግለቶች ውስጥ ይሰጥማሉ።"[29]

እንደተለመደው፣ ከላይ የተጠቀሱትን ሃሳቦች በተደጋጋሚ ካነበባችሁ በኋላ በቀላሉ መናገርን እንድትማሩ በቡድናችሁ ውስጥ ተወያዩበት። የሚከተሉት መልመጃዎች የአሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓል አስፈላጊነት ላይ ተጨማሪ ዕይታ ለማግኘት ይረዳችኋል፦

1. ጌታን ለማመስገን እና ለማወደስ አንድ ላይ የተሰበሰብንበትን እያንዳንዱ መኖሪያ ቤት ልዩ እንደሚሆን ባሃኦላህ ምን ያረጋግጥልናል? ______________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

2. ከላይ ባለው ሁለትኛው ጥቅስ ውስጥ፣ ባሃኦላህ እንዲህ ይነግረናል፦ በስብሰባዎች በአንድ ላይ ስንገናኝ፣ በዚያም ____________________ና______________________________

መናገር፣______________________________ማንበብ አለብን፤______________

______________________________ና______________________________

የአምላክ ቃላት ናቸውና።

3. ከላይ ባለው ሦስተኛው ጥቅስ ውስጥ፣ አብዱል-ባሃ ስብሰባዎች እንድናካሂድ እንዲሁም ሰማያዊ ትምህርቶችን እንድንደግምና እንድናዜም ይመክረናል፣ በዚያም

_ የምንኖርባት አገር ______________________________________________።

_ የምንኖርባት ምድር ______________________________________________

______________________________________________።

4. በባሃኢ የቀን አቆጣጠር ውስጥ ስንት ወራት አሉ?______________________________

5. በእያንዳንዱ ወር ውስጥ ስንት ቀናት አሉ?______________________________

6. በባሃኢዎች መካከል በወር አንዴ ምን ዓይነት ልዩ ስብሰባ ይካሄዳል? ____________________

________________________________________________________________________

7. የአሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓል ሦስት ክፍሎች ምን ምንድን ናቸው? ______________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

8. የአሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓል ክፍሎች የሚከናወኑት በማንኛውም ቅደም ተከተል ናቸውን?_____

________________________________________________________________________

9. የበዓሉ አምልኮአዊ /ፀሎተ ሱታፌ ክፍል ዓላማ ምንድን ነው?__________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

10. የበዓሉ አስተዳደራዊ ክፍል ዓላማ ምንድን ነው? ____________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

11. የበዓሉ ማህበራዊ ክፍል ዓላማ ምንድን ነው? _____________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

12. ከሚከተሉት ውስጥ በበዓሉ አስተዳደራዊ ክፍል ወቅት ለመወያየት ተገቢ የሆኑ ርዕሶች የተኞቹ ናቸው?

_____ ለማኅበረሰቡ ውጥኖች የመዋጮ / ፋይናንስ አስፈላጊነት

_____ የብሔራዊ እግር ኳስ ቡድን ውጤቶች

_____ በማኅበረሰቡ ሁለት አባላት መካከል ያለ አለመግባባት እንዴት መፍታት እንደሚቻል

_____ በማኅበረሰቡ ውስጥ የባሃኢ ሕፃናት ትምህርት ክፍሎች ዕድገት

_____ ከማኅበረሰቡ አባላት መካከል አንዱ በሳምንቱ መጀመሪያ ግዜያት ሲያጠና ስለነበረው ከቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ የአንድ ምንባብ ትርጉም

_____ በማኅበረሰቡ ውስጥ የታዳጊ ወጣት ፕሮግራም መጋጋል / ሕይወታማነት

_____ ለወጣት ሰዎች የሚከፈቱ የአካባቢ የሥራ ዕድሎች

_____ የአገልግሎት ፕሮጀክቶቻቸው ውስብስብ ለሆኑባቸው የታዳጊ ወጣት ቡድኖች ማኅበረሰቡ ሊያቀርብ የሚችለው ድጋፍ

_____ በተቋሙ በሚካሄዱት ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ውስጥ የሚካፈሉ የሕፃናትንና ታዳጊ ወጣቶችን ወላጆች ጎብኝቶች

_____ የማኅበረሰቡን አምልኮአዊ ባሕርይ ማጠናከር

_____ በቴሌቪዥን ላይ ስለሚተላለፉ ፕሮግራሞች

_____ በጥናት ክበቦች ውስጥ አስደሳችና ሥነ-ሥርዓት የተላበሰ ድባብ ስለማዳበር የተገኙ ዕይታዎች

_____ እየተቃረበ ስላለው የክብረ በዓል ቀን አከባበር

_____ ከማኅበረሰብ ግንባታው ሂደት የሚፈጠሩ የማኅበራዊ ተግባር መነሳሳቶች

13. ተከታዩን ጥያቄ በቡድናችሁ ተወያዩበት፦ በበዓሉ ሦስት ክፍሎች መካከል ሚዛን መጠበቅ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

14. አሁን ከሥር ያሉትን ሁለት ጥያቄዎች ተወያዩበት።

ሀ. አንተ/አንቺ ለምታስተናግደው/ጂው በዓል እንዴት ትዘጋጃለህ/ሽ?

ለ. በዓሉ ውስጥ ተሳታፊ ብቻ ብትሆን/ኚ እንዴት ትዘጋጃለህ/ሽ?

# ምዕራፍ 13

ስለ እምነቱ በምናደርገው ጭውውቶች ብዙ ግዜ የሚነሳው ሁለተኛ ጥያቄ የባሃኢ ማኅበረሰብ የመዋዕለ-ንዋይ/ ፋይናንስ ፍላጎቶቹን እንዴት እንደሚያሳካ ነው:: እንዲህ ላሉት ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት እንዲያስችላችሁ ጥቂት ነጥቦች እዚህ ተዘርዝረዋል፦

- የባሃኢ ማኅበረሰብ ቁሳዊ ፍላጎቶቹን ለማስተናገድ የሚጠቀምበት መሣሪያ የባሃኢ መዋጮ ነው:: በተለያዩ ዕርከኖች ባሉ የእምነቱ ተቋማት ማለትም በአካባቢያዊ፣ ብሔራዊ፣ አህጉራዊ፣ እና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት ይተዳደራል:: ባሃኢዎች እምነታቸውን ለማራመድ ለሚያደርጉዋቸው ጥረቶች ወጪዎችን እራሳቸው መወጣት እንዳለባቸው ያምናሉ፣ ስለሆነም የገንዘብ ቋቱ መዋጮ የሚቀበለው ከማኅበረሰቡ አባላት ብቻ ነው::

- ለመዋጮ ማዋጣት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ተግባር ነው:: በግለሰቡና የእምነቱ ተቋማት መካከል ያለ ጉዳይ በመሆኑ ምሥጢራዊ ነው፤ የሚያዋጡ ሰዎች ስሞችና የተሰጡ መጠኖች አይገለጹም:: የማኅበረሰቡ አባላት እንዲያዋጡ ምንም ጫና አይደረግባቸውም:: ተቋማት ለማኅበረሰቡ ጠቅላላ ጥሪዎች ያደርጋሉ፣ የመዋጮን ጠቃሚነት ያሳስባሉ፣ አስፈላጊነታቸውንም ያመላክታሉ:: ማኅበረሰቡ ለራሱ የመዋጮ ግብ አዘውትሮ ይመድባል:: ነገር ግን መጠኖች ለግለሰቦች ፈፅሞ አይመደቡላቸውም፣ እንዲሁም ገንዘብ አይጠየቅም:: ምን ያህል ማዋጣት እንዳለበት ወይም እንዳለባት ባለ የመርሆች መርዳት ላይ በመመርኮዝ እንዲወስን ወይም እንድትወስን ለእያንዳንዱ ግለሰብ የተተወ ነው::

- እኛ ለመገንባት እየሞከርን ያለነው ሥልጣኔ በቁሳዊምና ሆነ መንፈሳዊ ጎኑ የበለፀገ ይሆናል:: ሀብት ተቀባይነት ያለው የተወሰኑ ሁኔታዎች ከተሟሉ ነው:: ሀቀኛ በሆነ ሥራ አማካይነት ልናገኘው ይገባል:: ለሰው ልጅ ደህንነት ልናውለው ይገባል:: እናም መላው ማኅበረሰብ ከፍ ሊል ይገባል፤ አብዛኛው የሕይወት መሠረታዊ ነገሮች ማሟላት አቅቷቸው እያለ ጥቂቶች ከልክ በላይ ሀብታም ሲሆኑ ተቀባይነት የለውም:: ባሃኦላህ እንዲህ ይነግረናል፦

  ***"ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ ምስጉኖች ለኑሮ የሚያስፈልገውን በሙያቸው የሚያገኙና የዓለማት ሁሉ ጌታ ለሆነ አምላክ ፍቅር ሲሉ ለራሳቸውና ለዘመዶቻቸው የሚያወጡት ናቸው::"*** [30]

  ***"... እናንተ እራሳችሁና ሌሎች ከዚያ ይጠቀሙ ዘንድ፣ መልካምና ግሩም ፍሬዎችን ማፍራት አለባችሁ:: ስለዚህ በዕደ-ጥበባትና በሙያ ዘርፎች መሠማራት የእያንዳንዱ ግዴታ ነው፣ የማስተዋል ሰዎች ሆይ! የብልፅግና ምሥጢር ያለው በእነዚህ ውስጥ ነውና::"*** [31]

  አብዱል-ባሃም ሲያብራራ፦

  ***"መላው ሕዝብ ሀብታም እስከሆነ ድረስ፣ ሀብት እጅግ አስመስጋኝ ነው:: ሆኖም፣ ጥቂቶች ገደብ የለሽ ሀብት ኖሯቸው ቀሪዎቹ ከደኸዩ፣ እና ከዚያ ሀብት ምንም ፍሬ ወይም ጥቅም ካልተገኘ ሀብቱን ለያዘው ዕዳ ብቻ ነው::"*** [32]

  ከኢፍትሐዊነትና ስቃይ የፀዳ ኅብረተሰብ ለመገንባት፣ እኛ ሁላችንም ለጋሾችና ሰጪዎች መሆን አለብን:: የመዋዕለ-ንዋይ ምንጮቻችን ምንም ያህል ቢያንሱም፣ ለሰው ልጅ ዕድገት የሆነ ነገር ማበርከት ይኖርብናል፣ ምክንያቱም እውነተኛ ብልፅግና ሊደረስበት የሚችለው በመስጠት ብቻ

ነውና። ልግስና የሰው ነፍስ ባሕርይ ነው፤ ከቁሳዊ ሁኔታዎቻችን ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። በኀቡዓተ ቃላት ውስጥ ባሃኦላህ እንዲህ ይላል፦

**"መስጠትና መቸር የኔ ባሕርያት ናቸው፤ በባሕርያቴ ራሱን ያስጌጠ የበጀው ነው።"[33]**

- *ያለን ማንኛውም ሀብት እውነተኛ ምንጩ ሁሉን ለጋሱ፣ አምላክ መሆኑን ማስታወስ ይኖርብናል። ለኑሮአችን የሚያስፈልጉንን ነገሮች ያቀርብልናል፤ እንድናድግ ያስችለናል። እናም ለመዋጮ ስናዋጣ፣ እርሱ ከሰጠን ከፊሉን ለእምነቱ እያዋልን ነው። ስለዚህ፣ ለባሃኢዎች፣ ለመዋጮ መስጠት የለጋስነት ጉዳይ ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም መንፈሳዊ ችሮታና ታላቅ የግለሰብ ኃላፊነት ነው። ሞግዚቱ እንዲህ ይመክረናል፦*

***"እራሱን ካለው ነገር ሁሉ ያለማቋረጥ ባዶ እያደረገ ከማይታይ ምንጭ እንደገና እንደሚሞላ የምንጭ ውሃ መሆን አለብን። ድህነትን በመፍራት ሳናፈገፍግ እና የሁሉም ሀብትና መልካምነት ምንጭ በማያልቅ ችሮታ ላይ በመተማመን ለመሰሎቻችን ደህንነት ሳናቋርጥ መስጠት - ይህ የቀጥተኛ አኗኗር ምሥጢር ነው።"[34]***

አንዳንዶቹን እዚህ ያሉትን ሃሳቦች በዚህ ተከታታይ ጥናት/ኮርስ ተከታይ ክፍል የቁሳዊ መፍትሔን ርዕስ የሚዳስሰውን በተሻለ ጥልቀት ለመመልከት አጋጣሚው ይኖራችኋል። ለአሁን እንደሁልጊዜው ከላይ ያሉትን ይዘቶች ነጥብ በነጥብ ለመወያየት እና ሃሳቦቹን ተፈጥሮአዊ በሆነ መልኩና በቀላሉ መግለጽ እንድትማሩ፣ የሚከተሉትን መልመጃዎች እንድትሠሩ ትበረታታላችሁ፦

1. በጥቅሶቹ ላይ በመመሥረት፣ ከሥር ባሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ባዶ ቦታዎቹን ሙሉ።

ሀ. ባሃኦላህ ______________________________ በሙያችን እንድናገኝና ______________________________

________________________________________

እንድናወጣ ይነግረናል።

ለ. እኛ እራሳችንና ሌሎች ______________________________፣

____________________ ና ____________________ፍሬዎችን ማፍራት አለብን።

ሐ. እያንዳንዳችን በ ____________________ ና ____________________

____________________ አለብን፣____________________________

____________________ ያለው በእነዚህ ውስጥ ነውና።

መ. አብዱል-ባሃ ሲገልጽ ____________________ ሀብታም እስከሆነ ድረስ፣ ሀብት ______________________________ነው።

ሠ. ____________________ ገደብ የለሽ ____________________

ኖሯቸው ____________________፣ እና ከዚያ____________________

ምንም ______________ ወይም ______________ ካልተገኘ __________

____________________ብቻ ነው።

ረ. ባሃኦላህ እንዲህ ይላል፣ "____________________ና ____________________

የኔ ባሕርያት ናቸው፤ ____________________ ራሱን ____________________

የበጀው ነው።"

ሰ. ሞግዚቱም እንዲህ ያበረታታናል፣ እራሱን ካለው ነገር ሁሉ ያለማቋረጥ ______________

______________________________ እንደገና እንደሚሞላ __________

____________________ መሆን አለብን።

ሸ. ________________________________________ እና

________________________________________

____________________ ላይ በመተማመን ለመሰሎቻችን ______________

ሳናቋርጥ ____________________-ይህ የቀጥተኛ አኗኗር ምሥጢር ነው።

2. ከላይ ባለው አቀራረብ ውስጥ የተከተሉትን የሃሳቦች ቅደም ተከተል ፃፉ፦

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

## ምዕራፍ 14

ዕንቅስቃሴ በሚበራከትበት  በመንደር ወይም በሠፈር ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ የጭውውት ዓይነቶችን ዕይታ ለማግኘት፣ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ የሆነችው ወጣት፣ አሌሃንድራ ያደረገችውን ጥረቶች ተከታትለናል። ብዙ ሳምንታት በሸፈነው፣ተከታታይ ጉብኝቶች ላይ፣ ከአቶ እና ው/ሮ ሳንቼዝ ጋር የተወያየችባቸው ጭብጦች ስለ እምነቱ ያላቸውን ዕውቀት ለማጥለቅ እና ስለተቀበሉት ትምህርቶች ያላቸውን መሰጠት ለማጠናከር እንደሚረዳቸው ተስፋ ታደርጋለች። በመጨረሻ የሳንቼዞች የልጅ ልጅ የሆነችው የቢየትሪስ በትዕይንቱ ላይ መድረስ፣ ሁለቱም ማኅበረሰቦቻቸውን እንዴት ሊያገለግሉ እንደሚችሉ ለመማር በጓጉ ሁለት ወጣቶች መሃል ሌላ ዓይነት ጭውውት እንድናጤን አስችሎናል። በሃሳቦቹ ውስጥ በመቀጠልና መልመጃዎችን በመሥራት፣ በጠቃሚ ርዕሶች ላይ ዕውቀት ከማዳበር በተጨማሪ እዚህ የምንመለከታቸውን ጭውውቶች ዘላቂ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑትን የተወሰኑ መንፈሳዊ ባህርያት፣ አመለካከቶች፣ እና ክህሎቶች  ተመልክተናል።

በዚህና በሚቀጥለው የክፍሉ ምዕራፍ ውስጥ የተለያዩ ዓይነት ጭብጦችን - ማለትም በተቋሙ በሚካሄዱት ትምህርታዊ መርሃግብሮች/ ፕሮግራሞች ከሚሳተፉ ወጣቶች ቤተሰቦች ጋር ጉብኝቶች በሚደረጉበት ወቅት እነዚያ በጥቅሉ ለውይይት የሚውሉትን እንዳስሳለን። ቀደም ብሎ እንደተጠቆመው የሕፃናት ክፍሎችን ማስተማርና የታዳጊ ወጣት ቡድን እንደ አነቃቂ ሆኖ መምራት በተከታታይ ኮርሶች ውስጥ፣ በመጽሐፍት 3 እና 5 በቅደም ተከተል የሚዳሰሱ የአገልግሎት ተግባሮች ናቸው። ከሁለቱ ተያያዥ መርሃግብሮች/ ፕሮግራሞች ጋር፣ ትንሽ እያላችሁ ተሳታፊ በመሆናችሁ ወይም ባለመሆናችሁ ላይ በመመርኮዝ፣ ትውውቅ ሊኖራችሁ ወይም ላይኖራችሁ ይችላል።

በመጀመሪያ፣ ከታዳጊ ወጣት ቤተሰቦች ጋር በሂደት ላይ ባሉ ጭውውቶች ብዙ ግዜ መነሻውን ስለሚጀምርበት ይዘት እንመልከት። ታሪካችንን ከተውን የተወሰነ ግዜ እንዳለፈ እና ቢየትሪስ አሁን መጽሐፍ 2ን እያጠናች እንደሆነ በምናባችን እናስብ። አሌሃንድራ በእርሷ ዕገዛ ለምትመሠርተው ቡድን በዛ ያሉ የታዳጊ ወጣት ቤተሰቦች ስትጎበኝ አብራት ትሄድ እንደሆነ ጓደኛዋን ትጠይቃታለች። እሷ በጉጉት ትቀበላለች።

አሌሃንድራ የወጠነችውን ለቢየትሪስ ስትገልፅ፣ "እያንዳንዱን ጉብኝት ወንድና ሴት ልጆቻቸው ላይ ፍላጎት ያሳደረባቸውን መርሃግብር/ፕሮግራም ለወላጆች በማስተዋወቅ እና በሠፈሩ ውስጥ እየተካሄደ ያለው የማኅበረሰብ ግንባታ ሂደት አካል መሆኑን በመጥቀስ እንጀምራለን በማለት ታሳውቃታለች። ከዚያ ለመርሃግብሩ ማዕከላዊ የሆኑትን ጭብጦችና ሃሳቦች ከእነሱ ጋር እንዳስሳለን። ይህ ከተከታታይ ጉብኞቶች የመጀመሪያው ይሆናል፣ እናም ተስፋ የምናደርገው፣ በግዜ ሂደት ጭውውታችን ሲጎለብት፣ ቤተሰቦቹ በተለያዩ መንገዶች ቡድኑን በንቃት የሚደግፉ ብቻ ሳይሆኑ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚካሄደውን የታዳጊ ወጣት መንፈሳዊ ማጎልበቻ ፕሮግራም አራማጆች ይሆናሉ።"

አሌሃንድሮራና ቢያትሪስ ከእያንዳንዱ ቤተሰብ ጋር ለማንሳት የፈለጉትን አንዳንድ ነጥቦች መወያየት ይቀጥላሉ። በመጀመሪያ በጉብኝታቸው የሚሸፍኑት ጥቂቶቹን ብቻ እንደሆነና ቀሪዎቹን በተከታይ ጭውውቶቻቸው እንደሚዳስሱት ቢያውቁም፣ ጠቃሚ ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን ሃሳቦች ለመፃፍ ይወስናሉ። ስለ ታዳጊ ወጣቶቹ አቅሞች የዘረዘሩት ነጥቦች እዚህ ቀርበዋል፦

- በአንድ ግለሰብ ሕይወት ውስጥ፣ በ12 እና 15 ዓመት ዕድሜ መካከል ያሉት ሦስት ዓመታት ወሳኝ ወቅቶች ናቸው - ማለትም ከሕፃንነት ወደ ብስለት የመሸጋገሪያ ደረጃ በመሆኑ ነው ።

- በዚህ የዕድሜ ክልል ያሉ ወጣት ሰዎችን ብዙ ጊዜ "ታዳጊ ወጣቶች" ብለን እንጠራቸዋለን። ከዚህ ወዲያ ሕፃናት አይደሉም ነገር ግን ወደ ሙሉ ወጣትነት አልደረሱም።

- እንዳለመታደል ሆኖ፣ የታዳጊ ወጣቶች እንደ ችኩሎች፣ ዓመፀኞች፣ ስለእራሳቸው ብቻ የሚጨነቁ፣ ለማያቋርጥ ቀውስ የተጋለጡ፣ የሚባሉ የተሳሳቱ ሆኖም በስፋት የተሰራጨ ግፅታ አለ። ይሁን እንጂ እኛ እነርሱን በተለየ አቀራረብ እናያቸዋለን። በዚህ አጭር የሕይወት ግዜ በአካል፣ በስሜት፣ እና በአዕምሮ ሁላችንም ፈጣን ለውጦች እንደምናስተናግድ እውነት ነው። እንዲሁም፣ በዚህ ምክንያት፣ አንዳንድ ዓመፀኝነት ልናሳይ እንደምንችልም ዕርግጥ ነው። ነገር ግን፣ በእውነቱ፣ ይህ የታላቅ ዕምቅ ኃይልና የታላቅ ተስፋ ዕድሜ ነው።

- እኛ እራሳችን ብዙም ሳይርቅ ታዳጊ ወጣቶች ነበርን እናም በእነዚህ ለውጦች እንዴት ተጠቅተን እንደነበር እናስታውሳለን። አንዳንድ ግዜ ደፋሮች አንዳንዴም ድንጉጦች ነበርን። አንዳንዴ በፍፁም ተግባቢ ስንሆን በሌላ ጊዜ ደግሞ በጣም ዓይን አፋሮች ነበርን። ብዙ ግዜ ለብቻችን እንዲተውን ፍላጎታችንን እንገልፃለን፣ ሆኖም ትኩረት ለማግኘት ተስፋ እናደርጋለን። ጥሩ የነበርንባቸውን ነገሮች እና ምን ተሰጥዖዎች እንዲሁም ችሎታዎች እንዳሉን ለመረዳት ፈልገናል። እናም ሌሎች ሰዎች እንዴት እንደሚያዩን እና ስለሃሳቦቻችን ምን እንደሚያስቡ ይበልጥ ቦታ ይኖረዋል።

  መረዳት ያለብን አስፈላጊ ነገር እንዲህ ዓይነቱ ጠባይ ጊዜያዊ ብቻ መሆኑን ነው። በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ በእነዚህ ዓመታት ወቅት የተወሰኑ የአዕምሮ ኃይሎች በፍጥነት ያድጋሉ። ለመሠረታዊ የህልውና ጥያቄዎች መልሶች መፈለግ እንጀምራለን። በዙሪያችን ምን እንደሚካሄድ እንተነትናለን እንዲሁም የተማርናቸውን ነገሮች በአብዛኛው እንጠይቃለን። እናም በአንድ ወቅት አዋቂዎች እንድናደርግ የሚነግሩንን ወዲያውኑ እንከተል የነበርነውን ያህል ፈቃደኞች አንሆንም፣ በተለይም በቃሎቻቸውና በተግባሮቻቸው መካከል ተቃርኖዎችን ስናይ።

- ወጣቶች ብቅ እያሉ ያሉ ኃይሎቻቸውን ወጤታማ በሆነ መልኩ እንዲጠቀሙባቸው ለማገዝ፣ እነሱን እንደ ሕፃናት መመልከትን ማስወገድ ጠቃሚ ነው። አብዱል-ባሃ ይህን ወቅት እንዴት እንደገለጸው ተመልከቱ፦

**"ከተወሰነ ግዜ በኋላ የእርሱ የቀደሙ ሁኔታዎችና ፍላጎቶች በእርሱ ደረጃ ለመራመድ ተገቢ በሆኑ አዳዲስ መሥፈርቶች ሲተኩ፣ ወደ ወጣትነት ወቅት ይገባል። የማስተዋል ችሎታዎቹ**

**ይሰፋሉ ጥልቅም ይሆናሉ፤ አዕምሮአዊ ችሎታዎቹ ይሰለጥናሉ ይነቃሉም፤ የልጅነት ውስንነቶችና ሁኔታዎች ኃይሎቹንና ክንውኖቹን ከዚህ ወዲያ አይገድቡትም።"[35]**

- የባሃኢ እምነት የበላይ አካል የሆነው ዓለም አቀፍ ቤተ ፍትኅ፣ ከታዳጊ ወጣቶች ጋር ስንሠራ በሥራ ላይ ስላዋልነው አቀራረብ ይህን ይላል፦

  **"ዓለም አቀፋዊው አዝማሚያ የዚህን የዕድሜ ክልል አስቸጋሪ፣ በድብልቅልቅ የአካልና የስነ-ልቦና ለውጥ መዳፍ ውስጥ የወደቀ፣ የደነዘዘና በራሱ ዓለም የጠፋ አድርጎ ሲስለው ፣ የባሃኢ ማኅበረሰብ ግን በሚጠቀምበት ቋንቋም ሆነ በሚከተላቸው አቀራረቦች በታዳጊ ወጣቶቹ ውስጥ የላቀ ሰብዓዊነት፣ የሰላ የፍትኅ ስሜት፣ ስለ ሕዋ ለመማር የሚጓጉና ለተሻለ ዓለም ግንባታ አስተዋፅዖ ለማድረግ የሚሹ እንደሆኑ አድርጎ በመመልከት በወሳኝነት በተቃራኒው አቅጣጫ እየተጓዘ ነው።"[36]**

አሌሃንድራና ቢየትሪስ ቀጥሎ ወደ ራሱ ወደ መንፈሳዊ አቅም ማጎልበት መርሃግብር/ፕሮግራም ትኩረታቸውን በማዞር አንዳንድ መለያ ባህርያቱን ለመለየት ይሞክራሉ፦

- እነዚያ ዕድሜያቸው በ12 እና 15 ዓመት መካከል ያሉት አስተሳሰቦቻቸውን ሊያካፍሉዋቸው የሚችሉ የወዳጆች ቡድን ውስጥ እንዲካተቱ ይናፍቃሉ፣ ፕሮጀክቶች ላይ መሥራት፣ ስፖርት መጫወት፣ ወዘተ...። በዚህ ምክንያት፣ፕሮግራሙ በ"ታዳጊ ወጣቶች ቡድን" ፅንሰ ሃሳብ ዙሪያ የተገነባ ነው። እያንዳንዱ ቡድን ብዙ ግዜ ለአባላቱ እውነተኛ ወዳጅ የሆነ ተለቅ ያለ ወጣት፣ ችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ በሚያግዛቸው በ"አነቃቂ" ይመራል።

- ቡድኖቹ በቋሚነት ይገናኛሉ። በስብሰባዎቻቸው ውስጥ ታዳጊ ወጣቶች ፅንሰ-ሃሳቦችን መዳሰስ እንዲሁም ሃሳባቸውን የሳንሱር ወይም መሳለቅ ፍርሃት ሳይኖርባቸው መግለጽን ይማራሉ። ለማድመጥ፣ ለመናገር፣ ለማሰላሰል፣ ለመተንተን፣ ውሳኔዎች ለመስጠት፣ እና በእነሱ ላይ ተግባራዊ እርምጃ እንዲወስዱ ይበረታታሉ።

- ታዳጊ ወጣቶች የሚያስቡበትና መልካም ባህርይ የሚያሳዩበት መንገድ ብዙ አሉታዊ ኃይሎች ተፅዕኖ እያሳደሩበት ባለበት ወቅት ላይ እንኖራለን። አነቃቂዎች እነዚህን ኃይሎች እንዲዋጉ ያግዟቸዋል ማለትም ራሳቸውን ከኅብረተሰቡ የሞራል ዝቅጠት ለመጠበቅ ብቻ ሳይሆን ይልቁንም ለዓለም መሻሻል እንዲሠሩ ነው።

- መርሃግብሩ በሰው ነፍስ ውስጥ በተፈጥሮ የተቸሩትን ኃይሎች፣ በቅድመ ጉርምስና ወቅት እራሳቸውን ይበልጥ ትልቅ በሆነ ደረጃዎች መገለጽ በሚጀምሩ ኃይሎች ለማጎልበት ይሻል። በተለይ አስፈላጊዎቹ የማሰብ እና የመግለጽ ኃይሎቸ ናቸው። ወጣቶች ስለ ዓለም ጥልቅ ሃሳቦችን ለመግለጽ እና ለውጡን ማየት እንዴት እንደሚፈልጉ ግልፅ አድርጎ ለመናገር ሁለቱንም የሚያስፈልገውን ቋንቋ ማዳበር አለባቸው።

- ታዳጊ ወጣቶች ዓላማ ላለው ሕይወት መሠረታዊ የሆኑ ፅንሰ-ሃሳቦች ትርጉም ላይ ለማሰላሰል ጉጉዎች ናቸው። ደስታ፣ ተስፋ፣ እና ልቀት ጥቂቶቹ ምሳሌዎች ናቸው። በሚያሳዝን ሁኔታ ሰዎች ስለነዚህ ሃሳቦች የማወራት ዝንባሌያቸው ላይ ላዩን መንገዶች ነው። እንደዚህ ስላሉት ፅንሰ-ሃሳቦች ጥልቅ ግንዛቤ ማግኘት፣ በዕለት ተለት ሕይወት ውስጥ እንዴት መገለጫ

- እንደሚያገኙ መገንዘብ፣ጤናማ የሞራል መዋቅር ለመገንባት እና የኅብረተሰብን አሉታዊ ኃይሎች ለመቋቋም ወጣት አዕምሮዎችን ሊያግዝ ይችላል።

- ፅንሰ- ሃሳቦችን መረዳት ለአዕምሮአዊ ዕድገት ጠቃሚ ነው። በተለያዩ ርዕሶች ላይ ዋና ፅንሰ-ሃሳቦችን ለመጨበጥ በቂ የሆነ ዕገዛ ሳያገኙ፣ በጣም ብዙ መረጃዎችን እንዲማሩ ስለሚጠበቁ ታዳጊ ወጣቶች አንዳንዴ ችግር ሊያጋጥማቸው ይችላል። መርሃግብሩ ስለ ሃሳቦች በጥልቀት እንዲያሰላስሉ ያብረታታቸዋል - በሞራል፣ በሒሳብ፣ በሳይንሳዊ፣ እና በመሳሰሉት - እናም ይህ በትምህርት ቤት ያላቸውን ክንውን ሁልግዜ ያሻሽላል።

- ታዳጊ ወጣቶች የነገሮችን ትርጉም ያለው ነገር ለማግኘት ታላቅ ፍላጎት አላቸው። በዙሪያቸው ምን እየተፈጠረ እንዳለ ምክንያቶቹን ለመገንዘብ ይፈልጋሉ። ስኬታማ ለመሆን በአካላዊ ዓይኖቻቸው ብቻ ሳይሆን በመንፈስ ዓይንም ማየት መቻል አላባቸው። ስለሆነም፣ የመርሃግብሩ አስፈላጊ ግብ፣ መንፈሳዊ ግንዛቤን ማሳደግ- መንፈሳዊ ኃይሎችን የመረዳት ችሎታ እና በአጋጠሙ ሁኔታዎች ውስጥ መንፈሳዊ መርሆዎችን መለየት ነው።

- መርሃግብሩ የተለያዩ ግቦቹን ማለትም የሞራል ዕድገት፣ መንፈሳዊ ግንዛቤ፣ እራስን የመግለፅ ኃይሎች - በተከታታዮች መጽሐፍት ዕገዛ አማካይነት ያሳካል። መጽሐፍቱ በተለያዩ ዓለም ክፍሎች ስላሉ ወጣቶች ሕይወት ቀላል ትረካዎችን ያካትታሉ። እነዚህን መጽሐፍት በጋራ በማጥናት፣ ይዘታቸውን መወያየትና አስፈላጊ የሆኑትን መልመጃዎች በማሟላት ጎን ለጎን፣ ታዳጊ ወጣቶች በስፖርት ውስጥ ይሳተፋሉ እንዲሁም ስለ ስነ-ጥበባትና ዕደ-ጥበባት ይማራሉ።

- በአነቃቂዎቹ ዕገዛ፣ ቡድኑ በተጨማሪ የመርሃግብሩ ዋና አካል የሆነውን ተከታታይ የአገልግሎት ፕሮጀክቶችን ይቀርፃሉ ያከናውናሉም። በእነዚህ ፕሮጀክቶች አማካይነት፣ታዳጊ ወጣቶቹ ስለ ማኅበረሰቡና ፍላጎቱ ማሰብን፣ መመካከርን፣ እንዲሁም እርስ በርሳቸውና በማኅበረሰቡ ውስጥ ከሌሎች ጋር መደጋገፍን ይማራሉ።

- በመጽሐፍቱ ውስጥ የታቀፉት ርዕሰ-ጉዳዮች የተለያዩ ናቸው፤ እያንዳንዱ ለታዳጊ ወጣቶች መንፈሳዊ ማጎልበቻ ጠቃሚ የሆኑ ጭብጦች ላይ ያተኩራል። ለምሳሌ፣ የመጀመሪያው መጽሐፍ፣የ"ማረጋገጫ" ጭብጥን ይዳስሳል ማለትም የተከበሩ ግቦችን ለማሳካት የምናደርጋቸውን ጥረቶች አምላክ ማረጋገጫ ይሰጠናል። ሌላው መጽሐፍ ስለ "ተስፋ" ነው ይህም እጅግ በጣም አስቸጋሪ በሆኑበት ግዜያትም ውስጥ እንኳን ቢሆን ለወደፊቱ እንዴት በተስፋ መመልከት እንዳለብን ነው። ሌላው ስለ "ልቀት" ፅንሰ-ሃስብ ይተነትናል። "ደስታ" የአንድ ትረካ ጭብጥ ሲሆን፣ "የቃሉ ኃይል" በሌላ ውስጥ የመሰላሰያ ርዕሰ-ጉዳይ ነው። የሂሳብ ፅንሰ-ሃሳቦችን ከሚዳስሱ መጽሐፍት መካከል፣ አንዱ ስርዓት ያለው አዕምሮ ልማዶች የሚለውን ይዳስሳል። በሳይንስ ዙሪያ፣ የአንድን ሰው ጤና ማለትም አካላዊ፣ አዕምሮአዊ፣ እና መንፈሳዊ ክብካቤ ላይ የሚያተኩር መጽሐፍ አለ። እናም ታዳጊ ወጣቶቹ በሦስት ዓመታት ወቅት የሚያጠኑት ደርዘን ወይም ከዚያ በላይ መጽሐፍት አሉ።

አሌሃአንድራና ቢየትሪስ ምናልባት ወላጆች መጽሐፎቹን በጨረፍታ ለማየት ከፈለጉ በሚል ሁለት መጽሐፍት ይዘው ለመምጣት አቅደዋል። ከመጽሐፍቱ ጋር በደንብ ካልተዋወቃችሁ፣ የቻላችሁትን ያህል በዛ ያሉ ትረካዎች ለማንበብ የተወሰነ ግዜ ብትመድቡ ጠቃሚ ሆኖ

ታገኙታላችሁ - ይህ በማኅበረሰቡ ውስጥ እየተጀመረ ያሉትን የተለያዩ ጭውውቶች በተሻለ ለመከታተል ያስችላችኋል። እስከዚያው፣ በመጽሐፍ 5 ውስጥ በጥልቀት የተካሄደባቸውን፣ ከላይ የቀረቡትን ሃሳቦች በጥናት ቡድናችሁ ውስጥ ካሉ ሌሎች ተሳታፊዎች ጋር በሰፊው እንድት ወያዩበት ትበረታታላችሁ። ያንን መጽሐፍ ካጠናችሁ በኋላ፣ እንደታዳጊ ወጣት ቡድን አነቃቂ ሆናችሁ ለመሥራት ከወሰናችሁ፣ የእነዚህን አባላት ወላጆች ስልታዊ በሆነ መልኩ ትጎበኛላችሁ፣ እነዚህንና ብዙ ተመሳሳይ ሃሳቦችን ከእነርሱ ጋር ትዳስሳላችሁ። ነገር ግን አሁንም ቢሆን፣ እንደ ቢየትሪስ፣ በማኅበረሰባችሁ ውስጥ ላሉት የታዳጊ ወጣቶች ቤተሰቦች ጥቂት ጉብኝቶችን ልምድ ካለው ሰው ጋር አብራችሁ ለመሄድ ትፈልጉ ይሆናል።

## ምዕራፍ 15

በቀጣዩ ቀን፣ አሌሃንድራና ቢየትሪስ በሰፈሩ ውስጥ የሚመሠረተውን አዲሱን ቡድን የሚቀላቀሉ ሦስት ታዳጊ ወጣቶች ቤቶችን ይጎበኛሉ። ቢየትሪስ በመንፈሳዊ ማጎልበቻ መርሃግብሩ ጭውውት ላይ ከሚሳተፉ ወላጆች ጋር የሚኖረውን የጋለ ስሜት ለማየት ደስተኛ ናት። ከሰዓት በኋላ፣ ከታዳጊ ወጣት ቡድኑ ጋር አሌሃንድራን ለማገዝ እንድምትፈልግ ዕርግጠኛ ነች እንዲሁም በዓመቱ ውስጥ ራሷ እንደ አነቃቂ ሆና አዲስ ቡድን ለማገልገል እንደምትማር ተስፋ ታደርጋለች። በዕርግጥ እስከዚያው ጥቂት የተቋም መጽሐፍት ማጠናቀቅ እንዳለባት ትገነዘባለች። ነገር ግን ይህን ያህል ርቀት ባመጣት ጥናታቸው በተመሳሳይ የዘወትር ፍጥነታቸው ለመጓዝ ቁርጠኛ ነች።

ስለሆነም በአሌሃንድራ የማያሰልስ ዕገዛና ማበረታታት፣ ቢየትሪስ በአገልግሎት ጎዳና ላይ ወደፊት በመጓዝ ላይ ነች። ከዚያም ከጥቂት ወራት በኋላ፣ መጽሐፍ 3ን ልትጨርስ ስትል፣ታሪኳን እንደገና እንቀጥል። የእርሷ ጥናት ክበብ አስጠኚ፣ የሕፃናት ክፍል አስተማሪ የሆነችውን ማሪቤል፣ አዲስ የተመሠረተውን የ1ኛ ክፍል ትምህርት፣ ቢየትሪስና አብረዋት የሚሳተፉ ወዳጆች ወደ ሕፃናቱ ወላጆች በሚደረጉ ጉብኝቶች ላይ በጋራ እንዲሄዱ እንድትጋብዛቸው ጠየቀቻት። ቢየትሪስ ከመጽሐፍ 3 ጥናቷ በጣም ብዙ እንደተማረች ይሰማታል። እንዲሁም ከመጽሐፉ ያገኘቻቸው ዕይታዎች እንደ አነቃቂ ሆና ለማገልገል አቅሟን እንደሚያጎለብት፣ ለጥቂት ግዜያት ስትጠቅሰው ከነበረችው ከአሌሃንድራ አውቃለች።

አንድ ላይ ሲሆኑ የሚጎበኙት የኤማን እናት እንደሆነ ማሪቤል ለቢየትሪስ ትነግራታለች። "እሷ መማር የምትወድ ደስ የምትል ትንሽ ልጅ ናት፣" በማለት ማሪቤል ታካፍላለች። "ወላጆችዋን አንዴ ጎብኝቻቸዋለሁ እናም ስለ ባሃኢ ሕፃናት ክፍል ትምህርት ሁኔታ አብራርቼላቸዋለሁ። እነርሱ ኤማ እንድትሳተፍ ለመፍቀድ ደስተኞች ነበሩ። እናቷ ስለ ትምህርቱ የበለጠ ለመስማት ፍላጎት እንዳላት ገልፃለች፣ እናም የምናስተምረው መጽሐፍ ስለሚያተኩርበት ትምህርታዊ ሃሳቦች ትንሽ ለመናገር እንደምመለስ ቃል ገብቻለሁ። በዕርግጥ እኔ ለራሴ አንዳንድ ማስታወሻዎችን ፅፌያለሁ። ከፈለግሽ፣ አንዴ ልንሄድባቸውና ልንነጋገርባቸው እንችላለን።" ቢየትሪስ ትስማማለች። የተወያዩባቸው ማስታወሻዎች እነዚህ ናቸው፦

- በመጀመሪያ፣ ለወ/ሮ ማርቲኔዝ ኤማ በትምህርት ክፍሉ ውስጥ በመሆኗ እንዴት ደስተኛ እንደሆንኩ እና አንዳንድ የእርሷን ድንቅ ባሕርያት በመጥቀስ እነግራታለሁ።

- ውይይቱን ከባሃኦላህ ቅዱሳን ጽሑፎች ይህን ጥቅስ በማንበብ መጀመሩ እጅግ በጣም ጥሩ ይመስላል፦

**"ሰውን ዋጋው ከግምት በላይ የሆኑ የበለፀጉ ዕንቁዎች እንዳሉበት የማዕድን ሥፍራ ቁጠሩት:: ሃብቱን እንዲገልጽ ሊያደርገው የሚችለው፣ የሰውንም ዘር ከዚያ ለመጠቀም የሚያስችለው፣ ትምህርት ብቻ ነው::"[37]**

- ከዚያ ይህ ዓረፍተ ነገር እንደ አስተማሪ ምን ያህል ተፅዕኖ እንዳሳረፈብኝ ጥቂት ሃሳቦች ላካፍል እችላለሁ:: በክፍል ውስጥ ያሉትን ልጆች ስመለከት እና በዋጋ የማይተመኑ ዕንቁዎች የተሞሉ ማዕድኖች እንደሆኑ ባሰብኩ ቁጥር፣ልቤ በሐሴት ይጥለቀለቃል እላለሁ:: እያንዳንዳቸው ሰማያዊ ባሕርያትን ለማሳየት ዕምቅ ችሎታ አላቸው:: እያንዳንዳቸው ሊገኙና ሊጎለብት የሚችል ተሰጥዖዎች አላቸው:: እያንዳንዳቸው አድገው ጠቃሚ የኅብረተሰብ አባል ለመሆን እና ለዓለም መሻሻል አስተዋፅዖ ሊያበረክቱ ይችላሉ::

- ቀጥሎ፣ ምናልባት ትምህርት በእያንዳንዱ ልጅ ውስጥ ለመግለጥ መጣር ያለበትን ዕንቁዎች ጥቂት ምሳሌዎች መስጠት ይኖርብኛል:: አንዳንድ የአዕምሮ ኃይሎችን ልጠቅስ እችላለሁ፣ ማለትም፣ የተፈጥሮ ሕጎችን ለማወቅ፣ ውብ የሆኑ የስነ-ጥበብ ሥራዎችን ለመፍጠር፣ የተከበሩ አስተሳሰቦችን ለመግለጽ:: ተገቢውን ትምህርት ሲያገኙ፣ ሕፃናት እነዚህን ኃይሎች ሁሉ ማጎልበት ሊጀምሩ እንደሚችሉ እገልፃለሁ:: ነገር ግን፣ ይህ እንዲከሠት፣ ገና በልጅነት ዕድሜያቸው የተወሰኑ ባህርያትን ማግኘት አለባቸው:: ለምሳሌ፣ ትኩረት መስጠትን፣ አስፈላጊ በሚሆንበት ግዜ ጠንክሮ መሥራትን፣ እንዲሁም በሚሠሩት ነገር ላይ ማተኮርን መማር አለባቸው:: ስለ ሌሎች ደኅንነት የሚጨነቁ እና ማኅበረሰቡን ለማገልገል ወደሚፈልጉ ዓይነት ግለሰቦች ማደግ ይኖርባቸዋል:: ለዚህም ነው የባህርያቸውን ዕድገት በለጋ ዕድሜያቸው መከታተል አስፈላጊ የሚሆነው::

- ከዚያ፣ ወ/ሮ ማርቲኔዝ ሴት ልጇ ምን ዓይነት ሰው እንድትሆን እንደምትፈልግ ጥቂት ሃሳቦች እንድታካፍለን ለመጠየቅ ተገቢ ቦታ ይሆናል:: እሷ ኤማ እንዲኖራት ያስፈልጋታል ብላ የምታስባቸው አንዳንድ የባህርይ መለያዎች ምንድን ናቸው?

- እሷ ከምትጠቅሳቸው ባህርያት መካከል፣ በዕርግጠኝነት፣ አንዳንዶቹ፣ በቀጣይ የማስተዋውቀው አርዕስት በሆነው፣ በመንፈሳዊ ባህርያት ዘርፍ ውስጥ ይካተታል:: ለሰው ልጅ ሕልውና መሠረታዊ የሆኑ፣ አንድ ግለሰብ ሊኖራቸው የሚገባቸው የተወሰኑ ባህርያት አሉ፣ እላለሁ:: እነርሱ የሰው ልጅ ነፍስ አካል ናቸው:: የአምላክን ባህርያት ማንፀባረቅ እንዲችል የልባችንን መስተዋት በመወልወል እናዳብራቸዋለን:: እነዚህን መንፈሳዊ ባህርያት እንላቸዋለን፣ እናም በትምህርቶቻችን ውስጥ ለ1ኛ ክፍል የምናስተምራቸው ትምህርቶች በአብዛኛው በእነዚህ ባህርያት ላይ ያተኩራሉ::

- በመጽሐፍ 3 በ1ኛ ክፍል ትምህርቶች ውስጥ የተዳሰሱትን ጥቂት መንፈሳዊ ባህርያት ቀጥዬ እዘረዝራለሁ እንዲሁም ተያያዥ ጥቅሶቹን ከእሷ ጋር እጋራለሁ ብዬ አስባለሁ:: ኤማ እነዚህን ጥቅሶች በቃሏ እንደምትይዝ እና እርሷም ሴት ልጇን የምትማራቸውን ፀሎቶች ጭምር እንድትደግምላት ልትጠይቃት እንደምትችል እገልጽላታለሁ::

  - ፍቅር፦

    **" ወዳጅ ሆይ! በልብህ የአትክልት ሥፍራ ከፍቅር ፅጌረዳ በስተቀር ሌላ አትትከል ..."[38]**

- ፍትኅ፦

**"በፍትኅ መንገድ ተራመድ፣ ይህ በእውነቱ ቀጥተኛው መንገድ ነውና::"[39]**

- እውነተኝነት፦

**"እውነተኝነት የሰው መልካም ምግባራት ሁሉ መሠረት ነው::[40]**

- ደስታ፦

**"የሰው ልጅ ሆይ! በልብህ ደስታ ሐሴትን አድርግ፣ ከእኔ ጋር ለመገናኘትና ውበቴን ለማንፀባረቅ ትበቃ ዘንድ፦"[41]**

ማሪቤልና ቢየትሪስ የላይኞቹ ሃሳቦች ለአንድ ጉብኝት በቂ እንደሆኑ ይወስናሉ:: በቅርቡ መጽሐፍ 3ን እራሳችሁ ማጥናት ትቀጥላላችሁ እና ለሩሂ ተቋም የስድስት ዓመት መርሃ-ግብር የሆነው ለሕፃናት መንፈሳዊ ትምህርት ቅርፅ በሚሰጡት አንዳንድ መርሆዎች ላይ ለማሰላሰል ዕድሉ ይኖራችኋል:: ከዚያ በፊት፣ ከሕፃናት ክፍል አስተማሪ ጋር ጥቂት ወላጆችን የመጎብኘት አጋጣሚ ከተፈጠረላችሁ፣ እዚህ የቀረቡት ሃሳቦች እንደሚያግዟችሁ ይታመናል፣ በመሆኑም በቡድናችሁ ውስጥ አሁን ነጥብ በነጥብ ልትወያዩባቸው ይገባል::

## ምዕራፍ 16

ቀደም ብለን የሚከተሉትን የአብዱል-ባሃ ቃላት አንብበናል፦ "በሰዎች መካከል የወዳጅነትና የትብብር ትሥሥር ይበልጥ ሲጠነክር፣ በሁሉም የሰው ልጅ ዕንቅስቃሴ መስኮች የገንቢነትና ስኬት ኃይል የበለጠ ይሆናል::" ወደ ሌሎች ቤቶች ጉብኝት ስናደርግና ሌሎችን ወደእኛ ስንጋብዝ፣ "የማኅበረሰብ ስሜትን የሚገነባ የመንፈሳዊ ዝምድና ትሥሥርን እያጠበቅን ነው" ብለው ዓለም አቀፍ ቤተ ፍትኅ ይነግሩናል:: ስለዚህ፣ እያደገ ባለው ማኅበረሰባችን ባሕል ላይ የዚህን ልምድ ተፅዕኖ አቃለን ማየት የለብንም::

በቀደሙት ክፍሎች ውስጥ ከአንድ ወደሌሎች ቤቶች በምናደርጋቸው ጉብኝቶች ወቅት ሊካሄዱ ስለሚችሉ በርካታ የተለያዩ የጭውውት ዓይነቶችን ተመልክተናል:: ሁላችንም፣ የአገልግሎት ጎዳና ላይ ስንጓዝ፣ የባሃኦላህ ትምህርቶች በግለሰብና በጋራ ሕይወቶቻችን ስላሏቸው ተደራሽነት እየሰፋ በሚሄድ ጭውውት በመንደራችን፣ በከተማችን ወይም ሰፈራችን ውስጥ እንሳተፋለን:: አንዳንዴ ይህ የሚገለጸው ቁጥራቸው እየጨመረ የሚሄዱ ሰዎችን የእነዚህ ትምህርቶች ዕውቀቶቻቸውን ለማጥለቅ ለማስቻል በሚዘጋጁ ተከታታይ መደበኛ ጉብኝቶች ነው:: በሌሎች በርካታ አጋጣሚዎች፣ የተቋሙ ትምህርታዊ መርሃ-ግብሮች፣ ዓላማዎቻቸው እና ይዘታቸው፣ የውይይት ርዕሰ ጉዳይ ይሆናሉ:: በማኅበረሰቡ ግንባታ ሂደት ውስጥ ለማሳተፍ የሚደረጉ ግብዣዎች እያደጉ ወደሚሄዱ ሰፈሮችና ወዳጆች ይስፋፋሉ:: ስለዚህ፣ የወደፊቱን እና ከፊታችሁ ወደሚዘረጋው የአገልግሎት ጎዳና ስትመለከቱ፣ በዚህ ክፍል ውስጥ የቀረበውን ይዘት በደንብ ለመማር፣ በእያንዳንዱ ጭብጥ ላይ የመጨዋወት ልምድ ለማግኘት፣ እንዲሁም በዕርግጥ በባሃኦላህ ትምህርቶች የራሳችሁን ዕውቀት ለማጥለቅ እንድትቀጥሉ እያንዳንዱን ጥረት ማድረግ ይኖርባችኋል:: ስለዚህ የአምላክን ቃላት ከሌሎች ጋር የመካፈል የማያልቅ ሐሴት የእናንተ ይሆናል::

## ማጣቀሻዎች


1. ባሃኦላህ፣ *ንቡዓተ-ቃላት* ፣ (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2003፣2012 ኅትመት)፣ አረብኛ ቁጥር 4፣ ገጽ 4።

2. ባሃኦላህ፣ ከባሃኢ ፀሎቶች፡- *በባሃኦላህ፣ ባብ፣ እና አብዱል-ባሃ ከተገለፁት ፀሎቶች የተመረጡ፣* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣2002፣2017 ኅትመት)፣ገጽ 4።

3. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 1983፣2017 ኅትመት)፣4፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 5

4. ዝኒ ከማሁ፣ 5፣ አንቀጽ 2፣ ገጽ 6-7።

5. አብዱል-ባሃ፣ *ከባሃኢ ፀሎቶች፣* ገጽ 81።

6. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 111።

7. ዝኒ ከማሁ።

8. በ16 ኦገስት 1912 ከተደረገ ንግግር፣ *በሁለንተናዊ የሠላም ማስፋፋት ውስጥ የታተመ፡- በ1912፣ አብዱል-ባሃ አሜሪካንና ካናዳን በጎበኘበት ወቅት በእርሱ የተደረጉ ንግግሮች* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2012)፣ አንቀጽ 23፣ ገጽ 364።

9. አብዱል-ባሃ፣ *ከባሃኢ ፀሎቶች*፣ ገጽ 130።

10. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣* 45፣አንቀጽ 1፣ ገጽ 111-12።

11. አብዱል-ባሃ፣ በሾጊ ኤፌንዲ የተጠቀሰ፣ *የባሃኦላህ የዓለም ሥርዓት፡- የተመረጡ ደብዳቤዎች* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት፣1991፣ 2012፣ ኅትመት)፣ ገጽ 139።

12. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣* 5፣ አንቀጽ 5፣ ገጽ 8።

13. በ5 ሜይ 1912 በአብዱል-ባሃ ከተደረገ ንግግር፣ *በ'ሁለንተናዊ የሠላም ማስፋፋት'* ውስጥ የታተመ፣ አንቀጽ 4፣ ገጽ 128።

14. በ21 ኦክቶበር 1911 ከተደረገ ንግግር፣ በ'*ፓሪስ ንግግሮች' ውስጥ የታተመ፡- በ1911*፣*በአብዱል-ባሃ የተደረጉ ንግግሮች* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣2006፣2016፣ ኅትመት)፣ አንቀጽ 6.7-8፣ ገጽ 22።

15. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣* 146፣አንቀጽ 1፣ ገጽ 357።

16. በ5 ሜይ 1912 በአብዱል-ባሃ ከተደረገ ንግግር፣ በ'*ሁለንተናዊ የሠላም ማስፋፋት'* ውስጥ የታተመ፣ አንቀጽ 4፣ ገጽ 128።

17. *ንቡዓተ-ቃላት* ፣ ፋርስኛ ቁጥር 44፣ ገጽ 37።

18. ዝኒ ከማሁ፣ ፋርስኛ ቁጥር 66፣ ገጽ 45።

19. ከአብዱል-ባሃ ፅላት። (ኦቶራዝድ ትራንስሌሽ)

20. በ25 ሰፕተምበር 1912 በአብዱል-ባሃ ከተደረገ ንግግር፣ በ'*ሁለንተናዊ የሠላም ማስፋፋት'* ውስጥ የታተመ፣ አንቀጽ 2፣ ገጽ 478-79።

21. *ከአብዱል-ባሃ ጽሑፎች የተመረጡ* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት፣2010፣2015፣ ኅትመት)፣ ቁጥር 43.1፣ ገጽ 125።

22. ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 207.3፣ ገጽ 360።

23. ባሃኦላህ፣ *ስለ ባሃኢ ስብሰባዎች*፡- በዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትኅ የጥናትና ምርምር ማዕከል፣ *ከባሃኦላህ፣አብዱል-ባሃ፣ እና ሾጊ ኤፌንዲ ጽሑፎች የተውጣጡ ጥንቅሮች* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣1976፣1980 ኅትመት)፣ ገጽ 3።

24. ዝኒ ከማሁ።

25. *የአብዱል-ባሃ አባስ ፅላቶች* (ኒው ዮርክ፡- ባሃኢ ኅትመት ኮሚቴ፣ 1916፣1930 ኅትመት)፣ ቅፅ 3፣ ገጽ 631። (ኦቶራዝድ ትራንስሌሽ)

26. ባሃኦላህ፣ *ከኪታቢ አቅዳስ፣ እጅግ በጣም ቅዱስ መጽሐፍ* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 1993፣2013 ኅትመት)፣ አንቀጽ 57፣ገጽ 41።

27. *ከአብዱል-ባሃ ጽሑፎች የተመረጡ፣* ቁጥር 48.1፣ ገጽ 130።

28. በ27 ኦገስት 1989 ከተጻፈ ዳብዳቤ፣ *የዓለም ዓቀፍ ቤት ፍትኅ መልዕክቶች* ውስጥ የታተመ፣ *1986-2001:- The Fourth Epoch of the Formative Age* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2010)፣ ቁጥር 69.2፣ ገጽ 132-33።

29. ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 69.9-10፣ ገጽ 135።

30. *ኅቡዓተ-ቃላት* ፣ ፋርስኛ ቁጥር 82፣ ገጽ 51።

31. ዝኒ ከማሁ፣ ፋርስኛ ቁጥር 80፣ ገጽ 51።

32. አብዱል-ባሃ፣ *የመለኮታዊ ሥልጣኔ ምስጢር* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት፣2007፣ 2016 ኅትመት)፣ አንቀጽ 46፣ ገጽ 33።

33. *ኅቡዓተ-ቃላት* ፣ ፋርስኛ ቁጥር 49፣ ገጽ 39።

34. ሾጊ ኤፌንዲ፣ *ባሃኢ ዜና* ውስጥ የተጠቀሰ፣ ቁጥር 13 (ሰፕተምበር 1926)፣ ገጽ 1።

35. በ17 ኖቬምበር 1912 በአብዱል-ባሃ ከተደረገ ንግግር፣ በ'*ሁለንተናዊ የሠላም ማስፋፋት*' ውስጥ የታተመ፣ አንቀጽ 3፣ ገጽ 617።

36. ከ21 ኤፕሪል 2010 መልዕክት፣ *የተግባር ማዕቀፍ* ውስጥ የታተመ፦ *የዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትኅ የተመረጡ መልዕክቶችና ኢጋዥ መጽሐፍ*፣2006-2016 (ዌስት ቢች፡- ፓላብራ ኅትመቶች፣ 2017)፣ ቁጥር 14.16፣ ገጽ 82።

37. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣*122፣አንቀጽ 1፣ ገጽ 294።

38. *ኅቡዓተ-ቃላት* ፣ ፋርስኛ ቁጥር 3፣ ገጽ 23።

39. *ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣*118፣አንቀጽ 1፣ ገጽ 283።

40. አብዱል-ባሃ፣ በሾጊ ኤፌንዲ የተጠቀሰ፣ *የመለኮታዊ ፍትኅ ምፅዓት* (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣2006፣2018 ኅትመት)፣ አንቀጽ 40፣ ገጽ 39።

41. *ኅቡዓተ-ቃላት* ፣ አረብኛ ቁጥር 36፣ ገጽ 12።